# ማ ው ጫ

## ህገ መንግስትና የኢፌድሪ ህገ መንግስት በጠቅላላው---------ገጽ


I. ዝርዝር የስልጠናው ዓላማዎች---------------------------------------------------

II.መግቢያ ----------------------------------------------------------------------------

1.1. የህገ መንግስት ትርጓሜ-----------------------------------------------------

1.2.የህገ-መንግስት ዓይነቶች-----------------------------------------------------

1.3. ባህ መት ስፔ ሪካዊ አፈጣጠርና ታ ፔ ------------------------------

1.3.1.ህገ-መንግስት ታሪካዊ እድገት በኢትዮጵያ-------------------------------

1.3.1.1.የህገ መንግስት ታሪካዊ እድገት በዘውዳዊ ስርዓት፣------------

1.3.1.2.የህገ መንግስት እድገት በደርግ የስልጣን ዘመን---------------

1.3.1.3.የኢፌዲሪ ህገ መንግስት የጸደቀበት ታሪካዊ ሁኔታ---------------

1.4.የሕገ-መንግሥቱ መርሆዎች----------------------------------------------------

1.4.1.ሉአላዊነት---------------------------------------------------------------

1.4.2.ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች--------------------------------------

1.4.3.የሃይማኖትና መንገስት መለያየት---------------------------------------

1.4.4.የሕግ በላይነት----------------------------------------------------------

1.4.5.የመንነግስት አሠራርና ተጠያቂነት-------------------------------------

1.5.የሕገ-መንግሥቱ አተረጓጎም----------------------------------------------------

1.5.1.ህገ መንግስት ለምን ይተረጐማል

1.5.2.ሕገ-መንግስትን የመተርጐም ዓይነቶች

1.5.3.የህገ-መንግስት አተረጓጐም መርሆዎች/ስልቶች/

1.5.4.ህገመንግሥቱን በመተርጎም እና በማስፈጸም መካከል ስላለው ልዩነት

1.5.4.1. ህገ መንግስትን የመተርጐም ሂደትና የፍርድ ቤቶች ሚና

1.5.4.2.አተረጓጐም ሂደት የህገ- መንግስት አጣሪ ጉባኤ ሚና

1.5.4.3.አተረጓጐም ሂደት እና የፌዴሬሽን ምክር ቤት ሚና

1.6.ስለህገመንግስታዊነት ምንነትና ህገመንግስታዊነትን ስለማስረጽ---------------

1.6.1.የህገመንግስታዊነት ምንነት/ትርጉም

1.6.2.ህገመንግስታዊነትን ማስፈንን በተመለከተ የተወሰኑ አገራት ተሞክሮ

1.5.3. የኢፌዲሪ ህገ-መንግሥት ከፀደቀበት ጊዜ ጀምሮ በአገርቱ ህገ-መንግሥታዊነትን ለማስፈን የተደረጉ ጥረቶችና የተገኙ ውጤቶች

# ምራፍ አንድ

# ስለ ህገ መንግስትና የኢፌድሪ ህገ መንግስት በጠቅላላው

## I. ዝርዝር የስልጠናው ዓላማዎች

በዚህ ምዕራፍ ሥር የተካተተው ፣ፅሁፍ አንብበው ፣በፅሑፉ ላይ ገለፃ ከተደረገላቸውና የእርስ በርስ ውይይት አድርገው ሲጨርሱ ሰልጣኞቹ

1. ስለ ህገ መንግስት ትርጓሜና መሠረታዊ ባህሪያት ያስረዳሉ፡፡
2. የህገ መንግስት ታሪካዊ አፈጣጠርና እድገት ይዘረዝራሉ፡፡
3. የኢትዮጵያን ህገ መንግስት ታሪካዊ እድገትና ልዩ ባህሪያት ይገልፃሉ፡፡
4. የኢፌድሪን ህገ መንግስት የረቂቅ ዝግጅት ሒደትና የአፀዳደቅ ሂደት ያብራራሉ፡፡
5. ስለ ክልሎች ህገ መንግስት ረቂቅ ዝግጅትና የአፀዳደቅ ሂደት ይተነትናሉ፡፡
6. የኢፌድሪ ህገ መንግስት ሲፀድቅ ስለነበረው ነባራዊ ሁኔታ ያስረዳሉ፡፡
7. ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ስላለው የህገ መንግስት አፀዳደቅ ሒደት ያብራራሉ፡፡
8. ህገ መንግስት ስለሚፀድቅባቸው የተለያዩ መንገዶች ይገልፃሉ፡፡
9. የኢፌድሪን ህገ መንግስት ራዕይና ህገ መንግስታዊ ግቦች ያብራራሉ፡፡
10. የኢፌድሪን ህገ መንግስት አወቃቀርና መሰረታዊ  ገፅታዎች ይዘረዝራሉ፡፡
11. ህገ መንግስትን በመተርጎም ዙሪያ ስለ አሉ አሠራሮች ይገልፃሉ፡፡
12. ህገ መንግስት አተርጓጎም ዘዴዎችን፣ ያስረዳሉ፡፡
13. ኢፌድሪ ህገ መንግስት የአተረጓጎም፣ ሥርዓት፣ ያብራራሉ፡፡
14. ስለ ህገ መንግስት አጣሪ ጉባኤና የፌዴሬሽን ምክር ቤት የህጎችን ህገ መንግስታዊነት በማረጋገጥ በኩል ስላለባቸው ኃላፊነትና ስልጣን ይገልፃሉ፡፡
15. የህገ መንግስት ትርጉም የሚያሻቸውን ጉዳዮች ወደ ህገ መንግስት አጣሪ ጉባኤ ለመምራት ይችላሉ፡፡
16. የህገ መንግስት የማሻሻያ ሂደቶችን፣ ያብራራሉ
17. የኢፌድሪ ህገ መንግስት ስለሚሻሻልበት ሥርዓት ይገልፃሉ፡፡
18. ህገ መንግስት የበላይነት ፅንሰ ሀሳብ ይገልፃሉ፡፡

19. የህገ መንግስት የበላይነት ስለማረጋገጥባቸው መንገዶች ይዘረዝራሉ
20. የኢፌድሪ ህገ መንግስት የበላይነትና የበላይነቱን ስላረጋገጠባቸው መንገዶች ያስረዳሉ፡፡
21. የህገ መንግስቱን የበላይነት ለማረጋገጥ ያለባቸውን ኃላፊነት ይወጣሉ፡፡
22. በህገ መንግስትና በህገ መንግስታዊነት መካከል ስላለው ልዩነት ይገልፃሉ
23. የህገ መንግስታዊነት ፅንሰ ሀሳብ ምንነት ይገልፃሉ፡፡
24. በኢፌድሪ ህገ መንግስታዊነትን ለማስረፅ፣ በቁርጠኝነት ይሰለፋሉ፡፡

## II. መግቢያ

የአንድን አገር ህገ መንግስት የአፀዳደቅ ሒደት ትክክለኛነት፣ የህገ መንግስቱን፣ መሠረታዊ ግብና አወቃቀር፣ ይዘት፣ የአተረጓጎምና የማሻሻያ ሥርዓት ላይ ትክክለኛ የሆነ ግንዛቤ ለመያዝ በመጀመሪያ ስለ ህገ መንግስት መሠረታዊ ተፈጥሮና ትርጓሜ፣ ስለ ህገ መንግስት አፈጣጠርና ታሪካዊ እድገት፣ በህገ መንግስት ውስጥ መፍትሔ ሊሰጣቸው ስለሚገቡ ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ፖለቲካዊ አጀንዳዎችና መሠረታዊ የሰብዓዊ መብት ጥያቄዎች ዳሰሳ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ህገ መንግስት በባህሪው በአፀዳደቁ፣ በይዘቱ፣ በአተረጓጎሙና በሚሻሻልበት ስርዓት ከሌሎች አዎጆች (ህጎች) የሚለይባቸውን መሠረታዊ ነጥቦች መመርመርና መረዳት የግድ አስፈላጊ ነው፡፡

በመሆኑም የኢፊድሪ ህገ መንግስት አፀዳደቅ መሠረታዊ ግብና ዓላማ፤ ህገ መንግስቱ በህጎች የደረጃ አመዳደብ ሒደት ውስጥ ስላለው ሥፍራ፣ ስለ ህገ መንግስቱ የበላይነት፣ የህገ መንግስት የአተረጓጎምና የማሻሻያ ሥርዓቶች በውል ተረድቶ፣ ተገቢ የሆነ ግንዛቤ፤ ለመያዝ ከላይ በተነሱት ነጥቦች ዙሪያ የሌሎች አገሮችን ተሞክሮና አሠራር ማየቱ ሀሳቡቹን በንፅፅር ለመርመርና ለመረዳት እድል የሚሰጥ በመሆኑ ሞጁሉን በዓላማችን፣ ተቀባይነት ያላቸውን አሠራሮች በእያንዳንዱ ነጥብ በሚያሳይ መንገድ ለማዘጋጀት ተሞክሯዋል፡፡

በመሆኑም በዚህ ምዕራፍ በተሸፈኑትን ርዕስ ጉዳዮች ሲያነቡ የመጀመሪያው ክፍል ወይም ፖራግራፍ ስለሌሎች አገሮች ተሞክሮ በተሰጠው ገለፃ ላይ ግልፅ ግንዛቤ ይዘው የኢፌድሪ ህገ መንግስት ከሌሎች አገሮች ህግጋት መንግስት የሚጋራቸውንና የሚለዩባቸውን መሠረታዊ ነጥቦችና የልዩነቶቹን መሠረታዊ ምክንያት በጥንቃቄ መመዘንና መመርመር አለባቸው፡፡ እንደዚሁም ህገ መንግስት በማፅደቅና በህገ-መንግስት የሚካተቱት መርሆችና ሐሳቦችን አስመልክቶ ሁሉም አገሮች ሙሉ በሙሉ የሚስማሙበት ወጥ የሆነ ቀመር (ፎርሙላ) የሌለ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ አንፃር የእያንዳንዱ አገር ህገ መንግስት መመዘንና መታየት ያለበት ይዞት ከተነሣው አገራዊ ራዕይ፤ በአፀዳደቅ ሂደቱ የነበሩ ነባራዊ ዕውንታዎች፣ ሊፈታቸውና ሊቆጣጠራቸው ከሚፈልገው፤ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና የሰብዓዊ መብት ጥያቄቻች አንፃር መሆን እንዳለበት መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ የኢፌድሪ ህገ መንግስትን ድንጋጌዎች በይዘታቸው ከሌሎች አገሮች ህገ መንግስት የሚለዩባቸው አንዳንድ ነጥቦች በመኖራቸው ብቻ አንዳች ነገር የሚጎድለው ህገ መንግስት አድርጎው ለማቅረብ የሚሞክሩ አሉ፡፡ ይህም ተገቢ እንዳልሆነ መረዳትና የህገ መንግስቱ ድንጋጌዎች አገሪቱ ያሣለፈቻቸው ማህበራዊ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴና ችግር ውጤቶች መሆናቸው ተገቢው ግንዛቤ እንዲያዝባቸውና ተፈፃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፣ በማናቸውም ቦታና ጊዜ የተሣሣቱ አመለካከቶች ሣይንሣዊ በሆነ መንገድ ተከራክሮ ለማስተካከል በዕውቀት፣ የክህሎትና የአመለካከት ብቃት ማሳደግ ያስፈልጋል፡፡

በዚህ ምዕራፍ ስር ህገ መንግስት ትርጓሜና መሠረታዊ ባህሪያት፣ ታሪካዊ አፈጣጠርና እድገት ስለ ኢ.ፌ.ድ.ሪ ህገ መንግስት ረቂቅ ዝግጅትና አፀዳደቅ፣ እንዲሁም ህገ መንግስታዊ ራዕይና ግብ ስለ ህገ መንግስት አወጣጥ ሂደት፤ ስለህገ-መንግስት ዓይነቶች ፤ስለ ህገ-መንግስት አተረጓጐም መርህ/ስልት/፤ህገ-መንግስትን ስለሚተረጐሙ አካላት ፤ ስለ ህገ-መንግስት አተረጓጐም ሂደት ስርዓቶች፤ የኢፌዴሪ ህገ-መንግስት አተረጓጐም ፤ህገ-መንግስት በመተርጐም ሂደት የፍ/ቤቶች ሚና ፤ስለፌዴሬሽን ምክር ቤት እና የህገ-መንግስት አጣሪ ጉባኤ ሚና ፤ህገ-መንግስትን ስለማሻሻል እና የማሻሻያ ደረጃዎች፣ ስለ ህገ መንግስት የበላይነት፣ ስለ ህገ መንግስትና ህገ መንግስታዊነት እንዲሁም የህገ መንግስት የበላይነትና ህገ መንግስታዊነትን በማረጋገጥ በኩል የፍትህ አካላት ሚና አጠር ባለ መልክ መሠረታዊ ሀሳቦች ቀርበዋል፡፡

እንዲሁም ከነዚህ ጉዳዮች ውስጥ በዋና ዋናዎቹ ላይ የተወሰኑ የክልል ህገ-መንግስቶች ለመዳሰስ የሚረዱ፣ ለመወያያ የሚረዱ ሐሳቦች እና የመወያያ ጥያቄዎች በሞጁሉ ውስጥ ለማካተት ተሞክሯል፡፡

የህጐችን እና የባለሥልጣናትን ውሣኔዎች ህገ መንግስታዊነት ለማረጋገጥ እየተሠሩ ስላሉ የህገ መንግስት ትርጉም ለመረዳት የሚጠቅሙ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የህገ-መንግስት ትርጉም የሰጠባቸው ጉዳዮች በሞጁሉ ለማካተት ተሞክሯል፡፡ በመሆኑም ሰልጣኞች በሞጅሉ ውስጥ በተነሡት መሠረተ ሐሳቦችና በአባሪነት የተያያዙትን ውሣኔዎች በመመርመር እና በመተቸት ከህገ-መንግስት ፅንሰ ሐሳብ እድገትና ስለ ኢፊድሪ ህገ መንግስት አፀዳደቅ፣ ስለ ህገ መንግስት የበላይነትና ህገ መንግስታዊነት እንደዚሁም የህገ መንግስትን የበላይነት እና ህገ መንግስታዊነትን ለማስረፅ በአገራችን መከናወን ስላለባቸው ተግባራት እና ልንከተለው ስለሚገባን የአፈፃፀም ስልት ያላቸውን ዕውቀት እና ክህሎት ማሣደግና በአመለካከት ብቁ ሆነው ለመገኘት ያልተቆጠበ ጥረት ማድረግ ይገባቸዎል፡፡

## የትምህርቱ ዓላማ

ከዚህ ክፍል ትምህርት በኃላ፡

- ለህገ መንግስት ትርጉም ይሰጣሉ፡፡
- ስለህገመንግስት ታሪካዊ አመጣጥ ይገልፃሉ፡፡
- የህገ-መንግስትን ዓይነቶች፣ ጠንካራና ደካማ ጐናቸውን በማወቅ የሚሻለውን ይለያሉ፡፡
- 1923 ህገ መንግስት ምንን ዓላማ ለማሳካት ታስቦ እንደተዘጋጀና እንደወጣ ለይተው ይናገራሉ፡፡
- ደርግ የኢትዮጵያን ህዝብ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለመገደብ ስለአወጃቸው ህጎች ይገልፃሉ፡፡
- ኢህዲሪ ህገ መንግስት አካቶ የነበራቸውን ለኢትዮጵያ ባዕድ የሆኑ አስተሳሰቦችን ይለያሉ፡፡

## የህገ መንግስት ትርጓሜ

ውድ ሰልጣኞች፣ ህገ መንግስት ማለት ምን ማለት ነው? ህገ መንግስት የስነ ቃልና የህግ ትርጉም አንድ አይነት ነው ብላችሁ ታሰባላችሁ? ለምን? በዘመናችን ሰዎች ስለሚኖሩበት አገር ወይም ስለሌላው አገር ህገ መንግስት በአንዱ ወይም በሌላው መልኩ ሲገለፁ፣ ሲከራከሩና ሲወያዩ መስማት ወይም ማየት እንግዳ ነገር አይደለም፡፡ ህገ መንግስት በፅንሰ ሀሳብ ደረጃ ከዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ፣ ከመልካም አስተዳዳር፣ ከምጣኔ ሀብት እድገት ወይም ማሽቆልቆል፤ ከሰብዓዊ መብቶች አያያዝና ጥበቃ ጋር ተያይዞ የዘመናችን መነጋገሪያ አጀንዳ መሆኑ የሚያከራክር ጉዳይ አይደለም፡፡ ሆኖም ስለ ህገ መንግስት የሚወያዩ ሰዎች ሁሉ ስለ ሚወያዩበት ህገመንግስት ትክክለኛ የሆነ ግንዛቤ አላቸው ብሎ አፍን ሞልቶ መናገር አይቻልም፡፡

ምክንያቱም አንዳንዱ ሰው ከደረሰበት የትምህርት ደረጃ፣ ከኖረበት ሶሽዮ ኢኮኖሚክ እና ፖለቲካዊ ባህል፣ ከተሰማራበት የሙያ ዘርፍ እና ሌሎች ምክንያቶች ስለ ህገ መንግስት ያለው ግንዛቤ ከሌላው ሰው የተለየ ለመሆኑ ብዙ ማጣቃሻ የሚያስፈልገው አይደለም፡፡

ይኸም በመሆኑ ስለ ህገ መንግስት ትርጓሜና ተፈጠሮዊ ባህሪያት አንድ አንድ መሠረትዊ ነጥቦች ማንሣት በፅንሰ ሀሳቡ ላይ ተመሣሣይ ግንዛቤ ለመያዝ ይጠቅማል፡፡ በ1993 ዓ.ም የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል ያሳተመው መዝገበ ቃላት "ህገ መንግስት ማለት አንድ አገር የሚተዳደርበትና ሕዝቦቿ የሚያከናውኗቸው ተግባሮች ሁሉ መርህ የሚሆናቸው የሁሉም የበላይ የሆነ ህግ" በማለት ይተረጉመዋል፡፡

ሆኖም ከላይ ባነሳነው የአማርኛ መዝገበ ቃላት ለህገ መንግስት የሰጠው ፍቺ ጥቅልና የተሟላ ግንዛቤ ለመየዝ የማያስችል ነው፡፡ በመሆኑም የህገ መንግስት ፅንሰ ሐሳብ ከህግ ሙያና ከፍትህ አካላት ተልዕኮ አንፃር ለመረዳት ህገ መንግስት በህግ መዝገብ ቃላት እና በህግ መፀሐፍት ውስጥ የተሰጡት ትርጓሜዎች መመርመሩ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

ከዚህ አንፃር ስንመለከተው የኦክስፎርድ የህግ ድክሽነሪ "Constitution is the rules and practice that determine the composition and function of the organs of central Government in a state and regulate the relationship between the individual and the state" በማለት ይተረጉመዋል፡፡ ከዚህም ትርጓሜ፡-

- ✓ በመጀመሪያ ደረጃ ህገ መንግስት በፅሁፍ መልክ የተቀረፀ የህግ ድንጋጌዎችን ወይም ደንቦችን ብቻ የሚመለከት ሳይሆን በረዥም ጊዜና በተደጋጋሚ ተግባራዊ የሆኑ የአንዲት አገር መሰረታዊ እሴቶችና መርሆች በፅሁፍ ተጠቀልለው እና ህገ መንግስት ተብለው ባይታወጁም የአገሪቱ ሕገ መንግስት ድንጋጌዎች ሆነው የሚያገለግሉበት አጋጣሚ እንዳለ፡፡
- ✓ በሁለተኛ ደረጃ በህግ መልክ በፅሁፍ የታወጁት ደንቦች ወይም በልምድ የዳበሩ እሴቶች እና መርሆች የአገሪቱ ህገ መንግስት አካላት ናቸው የሚባሉት የማዕከላዊ መንግስትና አወቃቀር፣ የመንግስት አካላትን፣ ስልጣን፣ ኃላፊነትና የመንግስት ስልጣን ስለሚያዝበት ሁኔታ የሚወስኑ ገዥ መርሆዎችና ደንቦች ይዘው በተገኘው ጊዜ እንደሆነ፡፡
- ✓ በሦስተኛ ደረጃ በፅሑፉ የተደነገጉ ደንቦች ወይም በልምድ የዳበሩ እሴቶችና የመንግስትን አወቃቀር የመንግስት አካላትን አደረጃጀትን ስልጣንና ተግባር ከመወሰን በተጨማሪ በዜጎችና በመንግስት መካከል ያለውን ግንኙነት ለመቆጣጠር የሚችሉ ሊሆኑ እንደሚቻሉና ከላይ በተነሱት መሠረታዊ ጉዳዮች ገዥ የሆኑ ድንጋጌ ያለው የህግ ክፍል ህገ መንግስት ተብሎ እንደሚጠራ የሚያመለክት ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

በኦክስፎርድ የህግ መዝገበ ቃላት የሰጠውን ትርጓሜ ይዘት እንዳለ ሆኖ የብላክስ ሎው ዲክሽነሪ የሰጠውን ትርጓሜ ስንመለከት "Constitution is the fundamental and organic law of Nation or State establishing the conception, character, and organization of its government, as well as prescribing the extent of its sovereign power and the manner of its exercise" የሚል ትርጓሜ ሰጥቶት እናገኛለን፡፡ ይህን ትርጓሜ ስንመረምረው፡-

- ህገመንግስት መሰረታዊ የሆነ አንዲት አገር ወይም መንግስት የሚመራባትና የሚተዳደሩበት ህግ መሆኑን
- ይህ መሰረታዊ ህግ በዋነኛነት ስለ ህገ መንግስት አወቃቀር የመንግስት አካላት አደረጃጀት፣ የመንግስቱን ባህሪና ስለ መንግስት ስልጣን ሊያዝ የሚገባውን ገዢ አስተሳሰብ የሚያቋቁምና የሚደነግግ የህግ ክፍል መሆኑን።
- ከላይ ከገለፅናቸው በተጨማሪ ህገ መንግስት የመንግስት ሉአላዊ ስልጣን እስከምን ድረስ እንደሆነና መንግስት ሉአላዊ ስልጣኑን ሥራ ላይ ስለሚያውልበት አግባብ ወይም ስርዓት የሚደነግግ ገዢ የሆነ የህግ ክፍል እንደሆነ ይገልፃል።
- እንደዚሁም ትርጓሜው ህገ መንግስት በመንግስት ሉአላዊ ስልጣን ከፍተኛ የሆነ ወይም ዝቅተኛ ገደቦች የሚጥልና መንግስት ሉአላዊ ስልጣኑን እንዴትና በምን መንገድ መጠቀም እንዳለበት ገዢ የሆነ ደንቦች የሚያስቀምጥ የህግ ክፍል እንደሆነ ተመልክቷል።

በአጠቃላይ ስንመለከተው ህገ መንግስት በዋንኛነት አንዲት አገር ወይም አንድ መንግስት የሚተዳደርባቸው መሰረታዊ መርሆዎችና ደንቦች የሚይዝ የህግ ማዕቀፍ እንደሆነ የሚገልፅ ሲሆን ከተሰጡት ትርጓሜዎች ተነስተን የህገ መንግስት ፅንሰ ሀሳብ ስንመረምር።

- ህገ መንግስት አንዲት አገር የምትመራበትና መንግስት የሚተዳደርበት መሰረታዊ ህግ መሆኑን
- ህገ መንግስት እንደየአገሮቹ ተጨባጭ ሁኔታ በፅሁፉ ተጠቃልሎ በህገ መንግስትነት የታወጀ ወይም በረዥም ጊዜ ልምድና በህግ የዳበሩ እሴቶችና መርሆዎች ሊሆን እንደሚችል
- የተፃፈም ሆነ ያልተፃፈ ህገ መንግስት የመንግስትን አወቃቀር፣ የመንግስት አካላት አደረጃጀትና ስልጣንና ተግባር የሚወስኑ ገዢ መርሆችንና ድንጋጌዎችን የሚያካትት መሆኑንና
- ህገ መንግስት የመንግስት ሉአላዊ ስልጣን ምንጭና መሰረት እንደዚሁም የመንግስት ወሰንና ገደብ የሚወስኑ መርሆችና ድንጋጌዎችን የሚይዝና

3. የፌዴራል ህገ መንግስት ከክልል ህገ መንግስት በምን በምን ጉዳዮች ይለያል?

## 1.2.የህገ-መንግስት ዓይነቶች

የህገ-መንግስት ዓይነቶች ከስማቸው ጀምሮ የጋራ የሆነ ባህሪያት እንዳላቸው ሁሉ እንደየስማቸው ልዩነትና የራሳቸው የሆነ መለያ ባህሪያት አላቸው፡፡ ይህ ብቻም ሳይሆን እንደየአገሮች የታሪክ፣ የእድገት፣ ሪእዩተ ዓለም ወዘተ ልዩነት ህገ-መንግስታቸውም ሊለያይ ወይንም ሊመሳሰል ይችላል፡፡

ስለሆነም የህገ-መንግስትን ዓይነቶች፣ ጠንካራና ደካማ ጐናቸውን በማወቅ የሚሻለውን ለመለየትና ለመምረጥ የማይሻለውን ለመተው ስለሚረዳ እነዚህ የህገ-መንግስት ዓይነቶች ማወቅ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ህገ መንግስት አንዲት አገር የምትመራበትና የምትተዳደርበት መሠረታዊ ህግ ቢሆንም በዓለማችን ያሉ ህግጋተ መንግስት በአቀራረፃቸው በይዘታቸውና ሌሎች ሁኔታዎች የተለያዩ ናቸው፡፡ በመሆኑም የህገ መንግስቶቹን አቀራረፅ ይዘትና ሌሎች መሠረታዊ ሀሳቦችን መነሻ በማድረግ ህገ መንግስትን በሚከተሉት አኳኋን ከፋፍሎ ማስቀመጥና መግለፅ ይቻላል፡፡

- <u>የሕገ መንግስት ክፍፍል በፎርም፡</u>

የተፃፈ ህገ-መንግስት እና ያልተፃፈ ህገ-መንግስት በመባል የሚታወቅ ሲሆን ከስማቸው መረዳት እንደሚቻለው የተጻፈ ህገ መንግስት ድንጋጌዎቹ በጽሁፍ ተደርገው በግልፅ በአንድ ሰነድ መልክ ተጠቃሎ ታወጀና ታትመው ይገኛሉ፡፡ በአለም ከተወሰኑ አገሮች በስተቀር የቀሩት የተፃፈ ህገምንግስት አላቸው፡፡ ከነዚህ ውስጥ አሜሪካ፣ካናዳ፣ፈረንሳይ፣ ጀርመን፣ናይጀሪያ እና ኢትዮጵያ በምሳሌነት ሊጠቀሱ የሚችሉ ጥቅቶቹ ናቸው፡፡ ፌዴራል ሥርዓት የሚከተል መንግስት የግድ የተፃፈ ህገ መንግስት ሊኖረው ይገባል፡፡

ያልተፃፈ ህገ-መንግስት በሌላ በኩል አብዛኛው የህግ ድንጋጌዎች በፅሁፍ ያልተደረጉ ወይም ያልተሰባሰቡና በአንድ ሠነድ ያልተጠቃሉ ሲሆን ነው፡፡ ህገ-መንግስት ተብሎ የሚታወቅ አንድ ሰነድ ባይኖርም የመንግስት ስልጣን አያያዝ ፣ የመንግስት አካላት አደረጃጀትና ስልጣንና ተግባር በመንግስትና የዜጎች ግንኙነት የሚወስኑ በልምድ የዳበሩ እሴቶች እና መርሆች ያለባቸውን አገራት ለመግለፅ እንጠቀምበታለን፡፡ ያልተፃፈ ህገ መንግስት ያሰኘው በፍፁም ስላልተፃፉ ሳይሆን በአንድ ሰነድ ተጠቃለው አለመገኘታቸው ነው፡፡ ከዚህም በመነሳት ክፍፍሉ የተጻፈ ያልተጻፈ በሚል ሳይሆን ዶክመንት የተደረገና

እና ዶክመንት ተደርጎ ያልተቀመጠ በሚል መሆን እንዳለበት ብዙ ባለሙያዎች ይከራከራሉ፡፡ እንግሊዝ፣ እና እስራኤል ላልተጻፈ ህገ መንግስት ምሳሌነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

__የሕገ መንግስት ክፍፍል በሚሻሻልበት ሥነ ሥራዓት፡__

ሕገ መንግስት በሚሻሻልበት ሥነ ሥርዓት ጥብቅና ልል ህገ-መንግስት በመባል ይታወቃል፡፡ ጥብቅና ልል ህገ-መንግስት በመባል የሚታወቁት በዋነኝነት የህገ-መንግቱን የማሻሻያ ሂደት የሚመለከት ሲሆን ጥብቅ ህገ-መንግስት/rigid/ በቀላሉ የማይሻሻል ሲሆን ልል ህገ-መንግስት /Flexible/ የሚባለው ደግሞ በቀላሉ የሚሻሻል ነው፡፡

ህገ-መንግስት ማሻሻል ማለት በአጭር አነጋገር ለህገ-መንግስት ማስተካካያ የሚደረግበት ሂደት ነው ማለት ይቻላል፡፡ የህገ-መንግስት ማሻሻል ሂደት ክለሳ(Revision) ወይምንም አብዮት (revolution)ማለት አይደለም፡፡ ይልቁንም መሻሻል ማለት የለውጥ ሂደት ነው ማለት ይቻላል፡፡ ይህ ሂደት በአንድ ህገ-መንግስት ሰነድ ውስጥ የለውጥ እርምጃ ወይንም እድገት የሚታይበት ሂደት ነው፡፡

አብዛኛው ጊዜ ማሻሻያ የህገ-መንግስቱን ቃላት፣ ሐረግ፣ዓ/ነገር ወይንም አንቀጾችን ሊያጠቃልል ይችላል፡፡ በነዚህ በሚሻሻሉት ፈንታ በከፊል መጨመር፣በከፊል መቀነስ ወይንም ሙሉ በሙሉ መለወጥ ሊሆን ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ ሁሉ ለውጦች ከህገ-መንግስቱ አጠቃላይ ዓላማ፣ግብና መንፈስ ጋር በሚጣጣም መልኩ መሆን አለበት፡፡ የህገ መንግስት ማሻሻል ሂደት ህገ-መንግስቱ ህይወት ኖሮት ለረጅም ጊዜ እንዲኖር ያደርገዋል፡፡

ምክንያቱም ጊዜ በሄደና ነገሮች በተቀየሩ ቁጥር የዕድገት ደረጃም አብሮ ይቀየራል፡፡ ስለሆነም ህግም ሆነ ህገ-መንግስት አብረው ከህብረተሰብ እድገት ጋር ማደግ የግድ ይላል፡፡ ስለሆነም ህገ-መንግስት ዘላቂነት ኖሮት ገዢ ሆኖ ለመኖር መሻሻል ወይንም መለወጥ የግድ ይሆናል፡፡

ምንም እንኳን ከህገመንግስት ህገመንግስት ብለያይም ጥብቅ የማሻሻያ ሥነሥርዓት የሚከተሉ ሕገመንግስታት ሌሎች መደበኛ የአገርቱ ሕጎች በሚሻሻሉበት ሥነሥርዓት የማይሻሻሉ ናቸው፡፡ ለምሳሌ የአሜርካን ህግመንግስት ማሻሻያ ተግባራዊ የሚሆነው የማሻሻያው ፕሮፖዛል የላይኛውም ሆነ የታችኛው ምክር ቤቶች ለብቻቸው

በሚያደርጉት ስብሰባ በሁለት ሦስተኛ አብላጫ ድምፅ ስደገፍና በእያንዳንዱ የፌዴሬሽኑ አባል መንግስታት ህግ አውጪ ምክር ቤት በሦስት አራተኛ ድምፅ ማሻሻያውን ሲያጸድቁት ነው፡፡ የሕንድ 1949 ህገ መንግስት የሚሻሻለው የቀረበው የማሻሻያ ፕሮፖዛል በሁለቱም የህግ አውጪ ምክርቤት የጋራ ስብሰባ አብልጫ ድምፅ ሲጸድቅ ነው፡፡

ልል ህገ-መንግስት የተለየ የማሻሻያ ሥነ ሥርዓት ሳያስፈልገው ማናቸው የአገርቱ ተራ ህጎች በሚሻሻሉበት ስነሥርዓት ነው፡፡ ለምሳሌ፣ እንግሊዝ ህገ መንግስት የአገርቱ የበላይ ህገ መንግስት ባለመሆኑ ማናቸውም የአገርቱ ህጎች በሚሻሻሉበት ሥርዓት ይሻሻላል፡፡ ከዚህ በመነሳት በአንዳንድ የህግ ምሁራን የህጐች ሁሉ የበላይ እና የበላይ ያልሆነ የህገ-መንግስት ክፍፍል በሚልም ይታወቃል፡፡

ጥብቅ የሆነ የህገመንግስት ማሻሻያ ሥርዓት በሚከተሉ አገሮች የማሻሻል አስፈላግነት ባለበት ሁኔታ ሁሉ በቀላሉ ለማሻሻል ያስቸግራል፡፡ ለምሳሌ፣የፈረንሳይ፣ሲውዘርላንድ፣ አውስትራሊያ፣ጃፓን ህገመንግስታት የሚሻሻሉት የማሻሻያ ፕሮፖዛል በህዝበ ውሳኔ ሲደገፍ ስለሆነ በቀላሉ ማሻሻል አይቻልም፡፡ ልል የሆነ የህገመንግስት ማሻሻያ ሥርዓት በሚከተሉ አገሮች የማሻሻል አስፈላግነት በሌለበት ሁኔታ ሁሉ  የአገርቱን የመንግስት ሥልጣን የያዘ ሰው ጊዜያዊ የግል ፍላጎትን ለማሟላት ጭምር ደስ እንዳለው እንዲያሻሽል እድል የሚፈጥር ነው፡፡

ይህ ሁኔታ በተለይ በማደግ ላይ ባሉ የፍርካ አገሮች ደጋግሞ የሚታይ ተግባር ነው፡፡ የዙንባቡዌ ፕሬዝዳንት ሮበርት ሙጋበ በሥልጣን ቆይታ ጊዜውን ለማራዘም ህገ መንግስት ሲያሻሽል ታይቷል፡፡ ሮቤርት ሙጋቤ ከ27 ዓመት ስልጣን ቆይታ በኃላ በዓም አቀፍ ማህበረሰብ ግፍት ሥላጣን ለመልቀቅ ስስማማ ያደረገው ነገር ቢኖር በሕገመንግስት ማሻሻያ የሕግ አውጪውን ቁጥር ከ150 ወደ 210 ከፍ ማድረግና ሙጋቢ ከሥልጣን ከመውረዱ በፊት ተተኪውን ፕሬዚዳንት ፓርላማው እንድመርጥ የሚያስችል ነው፡፡ ይህም የራሱን ታማኝ ወራሽ ለመተካት ካላ ፍላጎት ነው፡፡ (http://jurist.law.pitt.edu/paperchase/2007/11/mugabe-signs-zimbabwe-constitutional.php)

የኢፌዴሪ ህገ-መንግስት የማሻሻያ ኃሳብ የማመንጨት ሂደት ምን እንደሚመስል በህገ-መንግስቱ በአንቀፅ 104 ስር በግልፅ ሰፍሮ ይገኛል፡፡  ይኸውም የማሻሻያ ኃሳብ

በፌዴሬሽን ምክር ቤት እና በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሁለት ሶስተኛ ድምፅ ከተደገፈ ወይንም ከፌዴሬሽኑ አባል ክልሎች ውስጥ አንድ ሶስተኛ የክልል ምክር ቤቶች በድምፅ ብልጫ የማሻሻያውን ሀሳብ የደገፉት ከሆነ ለውይይትና ለውሳኔ ለሕዝቡና ጉዳዮች ለሚመለከታቸው ክፍሎች እንደሚቀርብ ተደንግጓል፡፡

ከሰብአዊ መብቶች ድንጋጌዎች ውጭ ሌሎች የህገ-መንግስቱ ድንጋጌዎች ሊሻሻሉ የሚችሉት የፌዴሬሽኑ ምክር ቤትና የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት በጋራ ስብሰባ በሁለት ሶስተኛ ድምፅ የቀረበውን ማሻሻያ ሲያፀድቁት እና ከፌዴሬሽኑ አባል ክልሎች ምክር ቤቶች ውስጥ የሁለት ሶስተኛ ክልሎች ምክር ቤቶች በድምፅ ብልጫ ሲያፀድቁት ብቻ ነው፡፡ ሰብዓዊ መብቶችን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች እና የህገ-መንግስቱን ማሻሻያ የሚመለከቱ ድንጋጌዎች የሚሻሻሉት ሁሉም የክልል ምክር ቤቶች ማሻሻያው በድምፅ ብልጫ ሲያፀድቁት የፌዴራሉ መንግስት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሁለት ሶስተኛ ድምፅ ማሻሻያውን ሲያፀድቀው እና የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት በሁለት ሶስተኛ ድምፅ ማሻሻያውን ሲያፀድቁት ነው፡፡

ስለሆነም የኢፌድሪ ህገ-መንግስት የማሻሻል ሂደት ጥብቅ ሲሆን በተለይ ሰብዓዊ መብቶችን የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን ማሻሻሉ ደግሞ ይበልጥ ጥብቅ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ድንጋጌ በሌሎችም አገሮች ህገ-መንግስት ድንጋጌ የተለመደ ነው፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ህገ-መንግስት አይሻሻልም ማለት እንዳልሆነ ግልፅ ነው፡፡ ህገ-መንግስት በኢትዮጵያ የብሔሮች፣ብሔረሰቦችና ህዝቦች የቃል ኪዳን ሰነድ ስለሆነ በቀላሉ የሚቀየር ወይንም የሚሻሻል ሳይሆን ለማሻሻል በቂና አሳማኝ የሆነ ምክንያት ሲኖር ብቻ ነው ማሻሻል የሚቻለው፡፡
ከዚህ በመነሳት የኢፌድሪ ህገ-መንግስት ጥብቅ ህገ-መንግስት መሆኑን በቀላሉ ከማሻሻያው ስርዓት መረዳት ይቻላል፡፡

## <u>የሕገ መንግስት ክፍፍል በቅርፅ መንግሰት (በመንግስት አወቃቀር)፡</u>

በመንግስት አወቃቀር ሪፐብሊካዊ ወይም አሀዳዊ ህገ-መንግስት በመባል ይታወቃል፡፡ አሀዳዊ መንግስት ለአስተዳደር እንዲያመች በተለያዩ ክልሎች የሚከፋፈል ቢሆንም ከአንድ ማዕከል በሚፈስ አመራር ይመራሉ፡፡ ማናቸውም ሥልጣን በህገመንግስቱ ለማዕከል የተሰጠና የሥልጣን ክፍፍል የሌለበት ነው፡፡ ማዕከላዊ የመንግስት አካል

በፈለገ ጊዜ ሁሉ ህግ ማውጣትም ሆነ የመሻር ሥልጣን ይኖረዋል፡፡ እንግሊዝ፣ ፈረንሳይ፣ስፔን በምሳሌነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ እንግሊዝ የእንግላንድ፣ስኮትላንድ፣ ዋለስና አየርላንድ ድምር ውጤት ሲሆን በወስት ሚንስተር ያለው ፓርላማ ለሁሉም ህግ ሲያወጣ፣ ያለማዕከል አውቅና አናዳቸውም የራሳቸውን ህግ ማውጣት አይችሉም፡፡ ሪፐብሊካዊ የመንግስት አወቃቀር ሥልጣን በማዕከል የምንግስት አካላትና በክልል መንግስት አካላት መካከል ክፍፍል የሚደረግበት ነው፡፡

## የሕገ መንግስት ክፍፍል በመንግስት ዓይነት፡

የሕገ መንግስት ክፍፍል ኘሬዚዳንታዊ ወይም ፓርላመንታዊ ህገ መንግስት በመባል ይታወቃል፡፡ የአገርቱ ፕሬዚዳንት በቀጥታ በህዝቡ በሚመረጥበት ህገመንግስቱ ፕሬዚደንታዊ ይባላል፡፡ ህገመንግስቱም ፕሬዚዳንቱ ለፓርላማው ተጠሪ የሚሆንበትን ሳይሆን ለህዝቡ ተጠሪ የሞንበትን ሥርዓት ይዘረጋል፡፡ ከፍተኛው የህግ አስፈጻሚነት ሥልጣንንም ፕሬዚዳንቱን ያጎናፅፋል፡፡ ፕሬዚዳንቱ በህግ አውጪው ምክርቤት መቀጫ አይኖረውም፡፡ ይህም በአስፈጻሚውና በህግ አውጪው ምክርቤት መካከል ያላቸው ልዩነት መገለጫ ነው፡፡ የአሜርካ ህገመንግስት በምሳሌነት የሚጠቀስ ነው፡፡ ፓርላመንታዊ ህገ መንግስት ፓርላማው ከህግአውጪነት ሥልጣኑ በተጨማሪ አስፈፃሚውን የሚመራበትን ሥርዓት የሚዘረጋ ህገ መንግስት ነው፡፡ ጠቅላይ ሚኒስተሩ የራሱን ካቢነ ወክሎ በፓርላማው ያስፀድቃል፡፡ ይህ ሥርዓት ሚኒስተሮች በፓርላማው ውስጥ መቀመጫ እንዲኖራቸው ያስችላል፡፡ ከዚህም የተነሳ በህግ አውጪና አስፈጻሚው መካከል ግልፅ የሆነ ልዩነት ካለመታየቱም ህግ አውጪው በአስፈፃሚው ተፅኖ ሥር እንዲወድቅ ምክንያት ልሆን ይችላል፡፡

## ሥርዓተ መንግስት (ዘውዳዊ ወይም ሕዝባዊ ሕገ መንግስት)

ንጉሱ ወይም ንግሥት የአገርቱ ርዕሰ መስተዳደር የሆነበት አገር ሕገ መንግስቱ ዘውዳዊ ሕገ መንግስት ይባላል፡፡ የሥልጣን ተዋረዱ ዘርን መሠረት ያደረገ ሲሆን የመነግስት ሥልጣን ብቸኛ ባለበት ነው፡፡ በተለይ በንጉሱ ዘመን ዘውዳዊ አገዛዝ ፍፁማዊ ሥልጣን ባለበት ነበር፡፡ የእንግሊዝ እና ምዕራባዊ የአውሮፓ አገሮች ዘውዳዊ ሥርዓት ንጉሱ ወይም ንግሥት ውሱን የሆነ የግል ሥልጣን አላቸው፡፡

ማንም ሰው መያዝ እንደማይችል ዜጐች በቀጥታና በወኪሎቻቸው አማካኝነት በሚያደርጉት ተሳትፎ ሉአላዊ ህግ የማውጣት ስልጣናቸው የመጠቀም መብት እንዳላቸውና ሌሎች መብቶችን የሚዘረዝር ነው፡፡ ይኸ አዋጅ ስለ መንግስት ስልጣን አያያዝ የመንግስት ስልጣን ስራ ላይ ስለሚውልበት አግባብና በዜጐችና በመንግስት መካከል ሊኖር ስለሚገባው ግንኙነት በመደንገግ የመንግስት ስልጣን ምንጩና መሠረቱ በአምላክ መመረጥ ነው የሚለውን በሒልና አሰራር፣ መሠረተ ቢስ መሆኑን ያረጋገጠ ሰነድ ነው፡፡ በመሆኑም ህዝቡ የስልጣን ባለቤትነቱን እንዴትና በምን ሁኔታ ሊጠቀምበት እንደሚችል በአርአያነት የሚጠቀሱ መርሆዎችን የያዘ እንደሆነ የሥነ መንግስት ምሁራን ይስማሙበታል፡፡

ከላይ በአብነት የጠቀስናቸው ታሪካዊ ክስተቶች በስኬታማነታቸውና ከዚያ በኋላ በፅሁፍ መልክ ተረቅቀው በፀደቁ ህገ መንግስቶችን ዓላማና ይዘት ላይ ካሣደሩት ተጽእኖ አንጻር ጐልተው የወጡ በመሆናቸው እንጂ በሌላ ክፍለ ዓለምና አገራት የሚኖሩ ህዝቦች ሉዓላዊነታቸውን ለማረጋገጥ የመንግስታቸውን አወቃቀር ስልጣንና ተግባር በህግ ለመወሰን ያደረጉት እንቅስቃሴ የለም ለማለት እንዳልሆነ ግንዛቤ ሊያዝበት ይገባል፡፡ ከላይ በምሣሌነት ያነሳናቸው ሁኔታዎች የምንማረው አቢይ ቁም ነገር ህዝባዊ እንቅስቃሴዎቹ በህገ መንግስት ታሪካዊ አፈጣጠር ስላበረከቱት ታሪካዊ ፋይዳ አይደለም፡፡

ይልቁንም ህዝቦች በተለያየ መንገድ ተነጥቀው የነበሩትን ሉዓላዊነት በእጃቸው ለማድረግና የመንግስታቸውን አወቃቀር ስልጣንና ተግባር እንደዚሁም የዜጐችን መብትና ነጻነትና ተዛማጅ ግዴታ የሚወስንና አንዲት አገርና መንግስት የሚተዳደርበት ህግ ለማውጣትና ይህንን ህግ በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ ለረዥም ጊዜ ከፍተኛ የሆነ መስዋዕትነት እና ዋጋ የከፈሉ መሆኑን ነው፡፡ ከታሪካዊ ሒደቱ አፈጣጠሩ መገንዘብ እንደሚቻለው ህገ መንግስት በትረ ስልጣን ጨብጠው ህዝባቸውን ያስተዳድሩ የነበሩ መንግስታት በህግ ጥላ ስር መተዳደር ይገባናል፣ ስልጣናችንም በህግ ገደብ ሊበጅለት ይገባል፣ ብለው በራሳቸው ፍላጐትና ፈቃድ የደነገጉት የህግ ክፍል አለመሆኑን ነው፡፡

በተቃራኒው ህዝቦች ሉዓላዊነታቸውን ለማረጋገጥ የመንግስት ስልጣን በእነርሱ ፈቃደኝነት ብቻ እንዲያዝ ለማድረግ የመንግስታቸውን አወቃቀርና አደረጃጀት እንደዚሁም ስልጣንና ተግባር በህግ ለመቆጣጠር ይችሉ ዘንድ ያደረጉት የረዥም

ጊዜ ትግልና የከፈሉት መስዋዕትነት ውጤት መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ መሠረታዊ ነጥብ በመነሳት ነው አንድ ሰው የህገ መንግስትን ፅንሰ ሀሳብ መረዳት፣ መሠረታዊ ግቦቹን መመርመር ያለበት፡፡ ህገ መንግስቱ በታሪካዊ አፈጣጠሩ፡ አንባገነንነትን በህዝብ ጫንቃ ላይ ለመጣልና ህዝብ ያልመረጣቸው ሰዎች አምባገነንነታቸውን ህጋዊ ለማድረግ የሚገለገሉበት የህግ ክፍል ሆኖ አልተወለደም፡ ፡ ከታሪካዊ አፈጣጠሩና እድገቱ ህዝቦች የነገስታትን አንባገነን ስልጣን ለመገደብ ብሎም ሉዓላዊነታቸውንና መብታቸውን እውን ለማድረግ በአጠቃላይ መንግስት በህግ ጥላና ገደብ ስር የሚተዳደር መሆኑን ለማረጋገጥ በከፍተኛ መስዋዕትነት የፈጠሩት፣ በሒደትም ያሳደጉትንና ያዳበሩት የህዝቦች ፈቃድና ፍላጐት የጋራ መግለጫ እና መመሪያ ሆኖ የሚያገለግል የህግ ክፍል እንደሆነ ከታሪካዊ አመጣጡ በውል ለመረዳት ይቻላል፡፡

## 1.3.1.የህገ መንግስት ታሪካዊ እድገት በኢትዮጵያ፡

የኢትዮጵያን ህገ መንግስት ታሪካዊ እድገት በተለያየ ጊዜ የተለያዩ ገፅታዎተ ያሉት በመሆኑ በሦስት ምዕራፎች ከፍሎ ማየት ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ እነርሱም በዘውዳዊ ስርዓት ፣ በደርግ ዘመንና ከደርግ ውድቀት በኃላ ብለን ልንከፍላቸው እንችላለን፡፡

### 1.3.1.1. የህገ መንግስት ታሪካዊ እድገት በዘውዳዊ ስርዓት፣

**<u>የትምህርቱ ዓላማ</u>**

ከዚህ ክፍል ትምህርት በኃላ፡

- ☐ 1923 ህገ መንግስት ምንን ዓላማ ለማሳካት ታስቦ እንደተዘጋጀና እንደወጠ ለይታቸው መናገር ትችላላቸው፡፡
- ☐ ደርግ የኢትዮጵያን ህዝብ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለመገደብ ስለአወጻቸው ህጎች አንድባንድ መግለጽ ትችላላቸሁ፡፡
- ☐ ኢህዲሪ ህገ መንግስት አካቶ የነበራቸውን ለኢትዮጵያ ባዕድ የሆኑ አስተሳሰቦችን መለየት ተችላለህ፡፡

- ☐ የኢፌዴሪ ህግመንግስትን የማውጣት ሂደት ህገ መንግስት ባላቸው አገሮች ህገ መንግስትን የማውጣት ሂደት ከየሚያልፍባቸው ደረጃዎች ጋር ያለው አንድነትና ልዩነት መናገር ትችላላችሁ
- ☐ ለ1948ዓ/ም የአፄ ኃ/ሥላሴ ህገመንግስት ታሻሽሎ መውጣት ምክንያት የሆኑ ነገሮችን መግለፅ ትችላላችሁ፡፡

**ውድ ሰልጣኞች፣**

- ☐ የኢትዮጵያን ህገ መንግስት ታሪካዊ እድገት በተለያየ ጊዜ የተለያዩ ገፅታዎች እንዳሉት ታውቃላችሁ?
- ☐ በዘውዳዊ ስርዓት ፣ በደርግ ዘመንና ከደርግ ውድቀት በኃላ ያለው የኢትዮጵያ ህገ መንግስት አንዱ ለሌላው እድገት ያበረከተው ህገ መንግስታዊ ዕሰት አለ ብለው ያምናሉ?
- ☐ አፄ ኃ/ሥላሰ የ1923ን ህግ መንግስት በተሻሻለው በ1948ዓ/ም ህገመንግስት እንዲተካ ምን እንዳስገደደው ታውቃላቸው?
- ☐ የኢፌዴሪ ህግመንግስትን የማውጣት ሂደት ህገ መንግስትን ባላቸው አገሮች ህገ መንግስትን የማውጣት ሂደት ከየሚያልፍባቸው ደረጃዎች ጋር ያለው አንድነትና ልዩነት ታውቃላችሁ?

### *ሀ. 1923 ህገ መንግስት*

እንደሌሎች ህዝቦች ሁሉ የኢትዮጵያ ብሔር ብሔሮችና ህዝቦች ሉአላዊ ስልጣናቸውን አንባገነን ከሆኑ ፈላጭ ቆራጭ መንግስታት ለማስመለስ ሰፊ የሆነ እንቅስቃሴና ትግል እንዳካሔዱ የታሪክ ድርሳናት ይገልፃሉ፡፡ በኢትዮጵያ በተለያዩ ቦታዎችና በአራቱም መዓዘኖች ህዝባዊ አመፅና እንቅስቃሴ የተደረገ ቢሆንም የአፄውን ስልጣን ለመገደብም ሆነ ለመቆጣጠር የሚያስችል ህገ መንግስት ፀድቆ ሥራ ላይ እንዲውል አፄውን ለማስገደድ አልቻለም፡፡ በመሆኑም ስለ ኢትዮጵያ ህገ መንግስት ታሪካዊ እድገት ስንመለከት 1923 ዓ.ም በፊት አገሪቱ የተጻፈና በህገ መንግስትነት በይፋ የታወጀ ህገ መንግስት እንዳልነበራት

የሚያከራክር አይደለም፡፡ ስለሆነም የአገሪቱ የመጀመሪያው የተፃፈ ህገ መንግስት በ1923 ዓ.ም በቀዳማዊ ኃይለስላሴ የፀደቀው ህገ መንግስት ነው፡፡

1923 ዓ.ም ህገ መንግስት አረቃቅና አጸዳደቅ ሒደት ስንመለከት አንጼ ሀይለስላሴ በኢትዮጵያ አቆጣጠር 1922 ዓ.ም የንጉስ ነገስትነት ዙፋን ካጠለቁ በኋላ በዚያው ዓመት ተክለሀዋሪያት ተክለ ማሪያምንና ብላቴና ጌታ ሀሩይ ወልደስላሴን ፣ ህገ መንግስት አርቅቀው እንዲያቀርቡላቸው ትዕዛዝ እንደሰጡና ብላቴና ጌታ ሀሩይ ወልደስላሴ ደግሞ ጃፖንን የመጐብኘት ዕድል አግኝተው ስለነበር ፣ 1923 የኢትዮጵያ ህገ መንግስት በወቅቱ በጃፓን ሥራ ላይ በነበረው “የሚጅ ዘውዳዊ ህገ መንግስት” አይነት እንደተቀረጸና በይዘቱም በርካታ ሀሳቦች ከሚጅ ህገ መንግስት ተወስደው እንደተካተቱበት በዘርፉ ጥናት ያደረጉ ሙሁራን ይገልጻሉ፡፡

(Japan’s Meiji government promises political reform as part of its program of modernization. The new constitution gives legislative power to an elected lower house of the Imperial Diet, guarantees private property, and lays out basic rights for citizens, but it also upholds the emperor as sacred and supreme. In 1868, soon after Prince Mutsuhito became emperor, taking the name Meiji)

1923 ህገ መንግስት ከመውጣቱ በፊትና ሲወጣ በአገሪቱ ውስጥ ደም ያፋሰሱ አንገብጋቢ የማህበራዊ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጥያቄዎች የነበሩ ቢሆንም ህገ መንግስቱ ይህንን የህዝብ ጥያቄ ለመፍታት ታስቦ የተዘጋጀና የወጣ ሣይሆን በወቅቱ ስርዎ መንግስቱ ለቀዳማዊ ኃይለስላሴ ተወላጆች ብቻ እንዲተላለፍ በህግ ለመደንገግና የዘውዳዊ ስርዓት የግዛት ሉአላዊነት ህጋዊ መሰረት ለመጣልና የመኳንንቱና መሳፍንቱን ጥቅም ለማስከበር የተደነገገ ህገ መንግስት እንደሆነ የሚያከራክር አይደለም፡፡ 1923 ዓ.ም ህገ መንግስት ንጉሰ ነገስቱ በመሰላቸው መልክ ቀርፀው ለህዝቡ በስጦታ መልክ ያወጁት ህገ መንግስት እንደሆነ በመግቢያው ላይ በግልጽ አስቀምጠዋል፡፡

ህገ መንግስቱ በአስራ አንድ ምዕራፍ የተከፋፈሉ ሰማኒያ አምስት አንቀጾች አሉት፡ ይኸው ህገ መንግስት የንጉሱን ስልጣን በማጠናከር፣ ስልጣንን ወደ ማዕከል

የማሰባሰብ እና ማዕከላዊ መንግስትን አቅም የማጠናከር በየጠቅላይ ግዛቱ የነበሩ መሣፍንቶች የህግ መወሰኛ ምክር ቤት አባላት ሆነው አዲስ አበባ ተቀማጭ እንዲሆኑ ለማድረግ የሚያስችሉ ድንጋጌዎችን የያዘ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

ህገ መንግስቱ ባለሁለት ቻንበር የሆነ ምክር ቤት ማለትም በንጉሱ መራጭነት የሚሰየም የህግ መወሰኛ ምክር ቤት እና በመኳንንቶች ከየጠቅላይ ግዛት የሚመረጡ የህግ ምርመራ ምክር ቤት እንደሚኖሩት የሚደነግግ ሲሆን እነዚህ ምክር ቤቶች የንጉስ ነገስቱን ፈቃድና ስምምነት ካላገኙ ህግ ማውጣት የማይችሉ ከውሳኔ ሰጭነት ይልቅ የአማካሪነት ሀላፊነት የነበራቸው መሆኑን የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች በማንበብ ለመረዳት ይችላል፡፡ በ1923 ህገ መንግስት በንጉሱ ዕውቀትና የተሰጣቸው የዜጎች መብቶች ግዴታዎች ከአንቀፅ 18 እስከ አንቀፅ 29 የዘረዘሩ ቢሆንም መብቶች በህግ በሚደነገገው መሠረት ተግባር ላይ የሚውሉ መሆናቸውን የሚደነግጉ አሳሪ ደንቦች የሉባቸው ናቸው፡፡

ህገ መንግስቱ ጠቅላይ ሚኒስቴርና የሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚቋቋሙ ድንጋጌዎችን ከአንቀፅ 64 እስከ 73 የያዘ ሲሆን ጠቅላይ ሚኒስትሩም ሆነ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ህግ የማስፈፀም ተግባራቸውን የሚያከናውኑት በንጉሱ እያፀደቁ መሆን እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ 1923 ዓ.ም ህገ መንግስት ስለ ዳኝነት አካል ከአንቀፅ 54 የሚደነግግ ቢሆንም የዳኝነት ስልጣን የፍርድ ቤቶች ብቻ እንደሆነ አያረጋግጥም፡፡ በአጠቃላይ ዳኝነትን የሚመለከቱ የህግ ምርመራ ምክር ቤት ውሳኔ ተፈፃሚ የሚሆነው በንጉሱ ሲፀድቅ ብቻ እንደሆነ በዳኝነት መሾም ያለባቸው የዳኝነት አሰራር ልምድ ያላቸው መሆን እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አገሪቱ አስራ አራት ጠቅላይ ግዛት እንደተከፋፈለች ያስቀምጣል፡፡

1923 ህገ መንግስት በንጉሰ ነገስቱ ፀድቆ ሥራ ላይ ከዋለ ከአምስት ዓመት በኋላ ፋሽስት ኢጣሊያ በኢትዮጵያ ላይ በፈጸማቸው ጦርነት እና ወረራ ምክንያት ለጊዜው ተፈጻሚነቱ የተቋረጠ ቢሆንም ከድል ማግስት ንጉሱ ሲመለሱ ይህንኑ ህገ መንግስት መሠረት በማድረግ መንግስታቸውን ለማደራጀት እንደሞከሩና ከእያንዳንዱ ጠቅላይ ግዛት ስንት ተወካዮች እንደሚኖሩት የሚደነግግ አዋጅ

በማውጣት የህግ መወሰኛና የህግ ምርመራ ምክር ቤቶች  እንዲቋቋሙ ተደረገ፡፡ ሆኖም እነዚህ ምክር ቤቶች ቢኖሩም ፍፁማዊ፣  ህግን የማውጣትና የማስፈፀምና የመጨረሻ ፍርድ የመስጠትና የመወሰን ስልጣን የንጉሱ ሆኖ ምክር ቤቶቹ የተለመደውን የማማከር ሥራቸውን እንዲቀጥሉ በማድረግ እንዲወስኑ እንዳደረጉ በዘርፉ ጥናት ያካሄዱ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡

## ለ. 1948 ዓ.ም የተሻሻለው ህገ መንግስት

የጠላት ጦር ከአገራችን ከተባረረ በኋላ 1923 ህገ መንግስት የማሻሻል አስፈላጊነት ምክንያት የሚሆኑ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁኔታዎች ነበሩ፡፡ ሆኖም በመንግስት ትኩረት የተሰጠው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ኤርትራ በፌዴሬሽን ወደ ኢትዮጵያ እንድትቀላቀል በመወሰኑና ከነፃነት በኃላ በተባበሩት መንግስታት የኤርትራ ኮሚሽኔር ሆኖ በተሸመ የቦሊቪያዊ እቶ አንዜ አንትንዞ በመረቀቁ የኤርትራ ህገ መንግስት በሕዝብ የተመረጠ መንግስት፣የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚሳተፉበት እና የመሳሰሉ  ዘመናዊ የሚባሉ የዴሞክራሲ አስተሳሰቦችን ያካተተ መሆኑ ለጊዜውም ቢሆን፣  አለም አቀፍ ተቀባይነት ለማግኘት ሲባል 1923 ህገ መንግስትን በኤርትራ ህገ መንግስት ከተደነገጉት ጉዳዮች ውስጥ የተወሰኑትን (ለሥልጣኑ አደጋ እስካልፈጠሩ) በአካተተ መንገድ ከማሻሻል ውጪ ሌላ አማራጭ አልነበረም፡፡ በመሆኑም የህገ መንግስት ማሻሻያ አርቃቂ ኮሚሽን በንጉሰ ነገስቱ ትዕዛዝ ከተቋቋመ በኋላ ለስድስት ዓመት ያህል የማሻሻያ ረቂቁን ሲሰራ ቆይቶ፣ 1948 ዓ.ም የተሻሻለው ህገ መንግስት በንጉሰ ነገስቱ ታወጀ፡፡

በወቅቱ በነበረው የህግ ምርመራ እና የህግ አውጪ ምክር ቤት ምክክር እንደተደረገበት የሚገለጸው 1948 የተሻሻለው ህገ መንግስት ስምንት ምዕራፎችንና አንድ መቶ ሰላሳ አንድ አንቀጾች የነበሩት ሲሆን ከዚህ ውስጥ ከአንቀጽ 1 እስከ አንቀጽ 25  ስርዎ መንግስቱ ለአጼ ኃይለስላሴ ትውልዶች ስለሚተላለፍበት ስርዓት ከአንቀጽ 26 እስከ አንቀጽ 36 ደግሞ ስለ ንጉሰ ነገስቱ የህግ አውጪነት፣ የህግ አስፈጻሚነት እና የህግ ተርጓሚነት ተግባር የሚዘረዝሩ  ድንጋጌዎች የያዘ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡  1948 ዓ.ም የተሻሻለው ህገ መንግስት 1923 ዓ.ም ከወጣው ህገ

መንግስት በተሻለ ሁኔታ ሰብአዊ መብቶችን ይዘረዝራል፡፡ ሆኖም ይኸ ህገ መንግስት እንደ 1923 ዓ.ም ህገ መንግስት የንጉሱን ፍፁማዊ የሆነ የህግ ማውጣት የህግ ማስፈፀም የዳኝነት ስልጣን የሚያረጋግጥ ነው፡፡

1948 የተሻሻለው ህገ መንግስት በሚሻሻልበት ወቅት ህዝቡ ያልመከረበትና ያልተሳተፈበት በወቅቱም መሠረታዊና ቁልፉ ጥያቄ የሆነውን የብሔር ብሔረሰቦችና የመሬት ለአራሹ ጥያቄና ሌሎች የህዝብ ጥያቄዎች በአግባቡ ያልፈታ በመሆኑ በአገሪቱ ውስጥ የተቀጣጠለው ህዝባዊ ትግል ለማብረድና ህገ መንግስታዊ መፍትሔ ለመስጠት የማይችል ነበር፡፡ በመሆኑም የተሻሻለው ህገ መንግስት በፀደቀ ከሰባት ዓመት በኋላ 1953 ዓ.ም በመፈንቅለ መንግስት ንጉሰ ነገስቱን ለማስወገድና በአገሪቱ መሠረታዊ ለውጥ ለማምጣት የተሞከረ ሲሆን በተለያዩ ቦታዎች ህዝባዊ አመፅና እንቅስቃሴ ተደረገ፡፡ የገጠሩ አርሶ አደርም ለእኩልነት ካደረጉት ተጋድሎ ውስጥ የጎጃም አርሶ አደር ኢ-ፍታዊ ግብር አጣጣልን በመቃወም፣የባሌ አርሶ አደርም በተመሳሳይ ሁኔታ የማዕከለዊ መንግስት በመሬትና በእንስሳት ላይ ይጥል በነበረው ኢ-ፍታዊ ግብር መነሻ፣ በተመሳሳይ ሁኔታ ሌሎችም የእልከሬ፣ የዋቢ፣ የደሎ እና ትግራይ አከባቢ አርሶ አደሮች በተለያዩ ጊዜያት የራስን አስተዳደር በመሻት ያካሄዷቸው አመፆች ተጠቃሾች ናቸው፡፡
ይኸ በእዚህ ሁኔታ ላይ እንዳለ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት እንደ አውሮፖ አቆጣጠር ዲሴንበር 2 ቀን 1990 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ መሰረት ሉአላዊነቷን ጠብቃ ከኢትዮጵያ ጋር በተዋሃደችው ኤርትራ የራሰዎን ህገ መንግስት ከሁለት አመት በኋላ አፅድቃ ስራ ላይ አዋለች፡፡ ንጉሱንም በፌዴሬሽን የተዋሐደችውን ኤርትራና የኢትዮጲያን ግንኙነት የተመለከቱ የተለያዩ አዋጆች ካወጡ በኋላ በመጀመሪያ በኤርትራ ውስጥ የነበሩ የፖለቲካ ፖርቲዎች እንዲፈርሱ በማድረግ ግለሰቦች ብቻ ተወዳዳሪ የሆኑበት የአርትራ ፖርላማ ምርጫ 1949 ተከናወነ፡፡ ከዚያም ይህ ፖርላማ የተለያዩ ውሳኔዎችን እንዲወስን ከተደረገ በኃላ በህዳር ወር 1952 ዓ.ም ፌዴሪሽኑ እንዲፈርስ ወሰነ፡፡ ከዚህ በኃላ በንጉሱ ትዕዛዝ ቁጥር 27/1952 የኤርትራ ፌዴሬሽን ፈርሶ አንደ አንድ ጠቅላይ ግዛት በአህዳዊ መንግስት ስር ተጠቃለለች፡፡ የኤርትራ ፌዴሬሽን እንዲፈርስና በአህዳዊ ሥርዓት ከኢትዮጵያ ጋር እንድትዋኸድ አፄ ኃይለሰላሴ ያወጡት ንጉሳዊ ትዕዛዝ የብጥብጥ መነሻ ሆነ፡፡ ይህንን ድርጊት

የሚቃወሙ ወገኖች የትጥቅ ትግል ማካሔድ ጀመሩ፣ በአገር ውስጥም የነበረው ኢኮኖሚያዊ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ችግር በአግባቡ ለማስተናገድና የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች ለሚያቀርቡት የሉዓላዊነት ፣ የስልጣንና የማንነት ጥያቄ ምላሽ የሚሰጥ ህገ መንግስታዊ ሥርዓት ባለመፈጠሩ ህዝባዊ አመጽና አብዮት በመቀጣጠል መስከረም 2 ቀን 1967 ዓ.ም ንጉሰ ነገስቱ በህዝብ አመፅና ትግል ከስልጣን ሲወርዱ 1948 ዓ.ም የተሻሻለው ህገ መንግስትም ለአንደና ለመጨረሻ ጊዜ ህልውናው ከስርዓቱ ጋር አብሮ አከተመ፡፡

በኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት ያሉ አንዳንድ መረጃዎች እንደሚያሳዩት 1948 ዓ.ም የተሻሻለውን ህገ መንግስት ለማሻሻል 1960 ዓ.ም አርቃቂ ኮሚሽን ተቋቁሞ የንጉሰ ነገስቱን ስልጣን የሚገድብ አንድ ረቂቅ ተዘጋጅቶ ቀርቦ እንደነበረ፡፡ ንጉሱ ግን ስላልተደሰቱበት ረቂቁን ለህግ ምርመራና ህግ መወሰኛ ምክር ቤት ሳያቀርቡት የህዝቡ ቁጣና አመፅ ገንፍሎ ከስልጣን እንደወረዱ መረጃዎቹ ያሣያሉ፡፡ ሆኖም ለህዝብ ይፋ ያልሆነው ይኸ ረቂቅ ለኢትዮያ ችግር የተሟላ መፍትሔ የያዘ መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጠ አልተቻለም፡፡

በአጠቃላይ ሲታይ 1923 ዓ.ም የፀደቀው ህገ መንግስትም ሆነ 1948 የተሻሻለው ህገ መንግስት ህዝቡ ያልመከረበት፣ የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች መሠረታዊ የሉዓላዊነት ጥያቄ መልስ የማይሰጥና የንጉሰ ነገስቱን ስልጣን ህጋዊ ለማድረግና ለማጠናከር የንጉሱን ፈቃድ እና ፍላጐት ማዕከል አድርገው የተቀረጸና የፀደቁ መሆናቸው የሚያከራክር አይደለም፡፡ ይኸም ከላይ ካየነው የሌሎች አገሮች ህገ መንግስት ታሪካዊ አፈጣጠርና እድገት በተለየ መንገድና ሁኔታ ህገ መንግስትን፣ አምባገነናዊ የሆነውን የዘውዳዊ ሥልጣኑን ዘውዳዊው ሥርዓት ህጋዊ ለማድረግና የንጉሱን ስልጣን በሚያጠናከር መንገድ ለመጠቀም እና የህዝቡን የሉዓላዊነትና የስልጣን ባለቤትነት ጥያቄን ለመጨፍለቅ በሚያመች መንገድ ህገ መንግስቱን ለመጠቀም በመሞከራቸው የህዝቡ አመጽ የበለጠ በመቀጣጠል ንጉሱንም ሆነ ያፀደቁትን ህገ መንግስት መቀመቅ እንዳወረዳቸው የሚያስገነዝበን ነው፡፡

## የመወያያ ነጥቦች

- ህገ መንግስት  የመንግስት ስልጣን ለመገደብና መንግስትን ከህግ የተገዥ ለማድረግ በህዝብ ትግል የተፈጠረ ህግ ነው፡፡ በዚህ አይነት መንግድ በተፈጠረ ህገ መንግስት ተገዥ ሆነው፡፡ ህዝብን የሚያስተዳድሩ መንግስታት ህገ መንግስታዊ መንግስት ይባላል፡፡ በሌላ በኩል በንጉሱ ጊዜ እንደታየው ህገ መንግስትን ስልጣናቸውን ለማጠናከር ህጋዊ ለማድረግ አስበው በሚስማማቸውና በሚፈልጉት መንገድ ህገ መንግስት ያፀድቃሉ፡፡ የእዚህ አይነት ሁኔታ ሲያጋጥም መንግስታዊ ህገ መንግስት በማለት ይገልፃሉ፡፡

  ለመሆኑ በህገ መንግስታዊ መንግስትና በመንግስታዊ ህገ መንግስት መካከል ያለው መሰረታዊ ልዩነት ምንድን ነው፡፡

### 1.3.1.2. የህገ መንግስት እድገት በደርግ የስልጣን ዘመን

ህዝቡ መሠረታዊ የሆኑ ጥያቄዎች ባለመፈታታቸው በቁጣ ገንፍሎ በአፄው ሥርዓት ላይ በሚያምጽበት ወቅት ህዝባዊ እንቅስቃሴውን የሚመራ የተደራጀ ብቃት ያለው የፖለቲካ ሀይል አልነበረም፡፡ በመሆኑም በዝቅተኛ እርከን ላይ የነበሩት ወታደራዊ መኮንኖች በመሰባሰብ በወቅቱ የነበረውን ክፍተት በመጠቀምና የህዝቡን ትግል እንመራለን በሚል ሽፋን “የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ” በሚል መጠሪያ የሚጠራ ወታደራዊ አንባገነንነት መንግስት ራሳቸው በአወጁት አዋጅ በማቋቋም የመሰላቸውን ህግ እያወጡ፣ በርካታ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች፣ በስብዕናና በሰብዓዊ ፍጡር ላይ ወንጀሎችን በመፈፀምና የጦርነትን ህግጋት ሚጥሱ ወንጀሎችንና የዘር ማጥፋት ወንጀል እንደፈጸሙ ብዙ ማጣቀሻና ማስረጃ የሚያስፈልገው አይደለም፡፡ ደርግ በወቅቱ አንገብጋቢ የነበረውን የመሬት ለአራሹ ጥያቄ ስር ነቀል መፍትሔ የሰጠው ቢሆንም በሌላ በኩል የአርሶ አደሩን የምርት ተጠቃሚነት የሚገድብ አሰራርዘግቷል፡፡ ነጋዴው ማህረሰብም የመስራት ነፃነት  በአዋጆች ገድቫል፡፡ የአገር ውስጥ ንግድ ሥራ መቆጣጠሪያ አዋጅ 335/1979 አንቀጽ 14 ላይ ማናቸውም ነጋዴ የንግድ ዕቃ ሚኒስቴሩ ባስታወቀው ተመን የመሸጥ ወይም ማናቸውንም አገልግሎት ሚኒስቴሩ ባስታወቀው ተመን የመሰጠት ግዴታ አለበት፡፡

በዚው አዋጅ አንቀጽ 34(1)(ሐ) ላይ ከተመለከተው ዋጋ በላይ የንግድ ዕቃ የሸጠ ወይም አገልግሎት የጠየቀ ከብር 5ሺህ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ወይም ከሁለት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ወይም በሁለቱም ያስቀጣል፡፡

በሌላ በኩል ደርግ እራሱን በአዋጅ ካቋቋመበት ቀን ጀምሮ የህዝቡን ሉዐላዊነትና ስልጣን ባለቤትነት በመንጠቅ፣ የዜጐችን የመናገርና ሀሳብን በነጻ የመግለጽ፣ የአመለካከት ነፃነትን የመደራጀትና ማህበር የመመሥረት ነፃነት፣ በህይወት የመኖርና ኢሰብአዊ ከሆነ አያያዝ የመጠበቅ ነፃነትን፣ በግልጽ የሚጥሱ በርካታ አዋጆችን አውጥቷል፡፡ የተወሰኑትን ለአብነት መጥቀስ ቢያስፈልግ፤ የግለሰቦችን ንብረት ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ መፈተሽና ማገድ፣በሚያደርገው ምርመራ ተጠያቂ የሆነውን ሰው ማሰር ሥልጣን ያለው የሠርቶ አደሩ ቁጥጥር ኮሚቴ  በወጣ አዋጅ ቁጥር 213/1974፣ የተጠርጣሪዎችን በነፃ ፍርድ ቤት የመዳኘት መብታቸውን የሚጥስ ልዩ ፍርድ ቤት በአዋጅ ቁጥር 215/1974ዓ/ም  በማቋቋም በወቅቱ የነበረውን ትውልድ ያለፍርድ በመግደል ፣ ኢ ሰብአዊ ለሆነ እስር በመዳረግ፣ አስገድዶ በመሰወርና ሌሎች ተደራራቢ ወንጀሎችን በመፈጸም ግማሾቹ በስደት ግማሾቹ ስርዓቱን በትጥቅ ትግል ለመጣል በሚደረገው እንቅስቃሴ እንዲቀላቀሉ በማድረግ በአንዱ ወይም በሌላው መልኩ አንድ ትውልድና አገርን የሚያጠፋ ተግባራትን ፈጽሟል፡፡

1967 መስከረም ወር ጀምሮ ይህንን የመሰለ ዘግናኝ ወንጀል ሲፈጽም የቆየው ወታደራዊ መንግስት 1977 ዓ.ም ኢሠፓ የሚለውን ፓርቲ ካዋቀረ በኋላ 1979 ዓ.ም የህገ መንግስት አርቃቂ ኮሚሽን በማቋቋም በረቂቁ ላይ ህዝቡ እንዲወያያበት ለማድረግ ሞክሯል፡፡ በወቅቱ ሀሳቡን በነጻ የመግለጽ ነፃነት በሌለበት ሁኔታና ሰዎች በአፋቸው መንግስትን የሚቃወም ነገር ሲናገሩ መሰማታቸው ቀርቶ በጥርጣሬ ተይዘው በሚታሰሩበት ወይም በሚገደሉበት ሁኔታ ህዝቡ ነፃ ሆኖ ህገ መንግስቱን ረቂቅ ትችት ሊሰጥ እንደማይችል የሚታወቅ ቢሆንም ይኸ አልበቃ ብሎ በረቂቁ የመጨረሻ ሰነድ ላይ ህዝቡ የይስሙላ ህዝበ ውሳኔ እንዲሰጥበት በማድረግ ፤ 1980 ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 1/1980 **"የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ህገ መንግስት"** በሚል ስያሜ በአስራ ሰባት ምዕራፍ የተከፋፈለ አንድ መቶ አስራ ዘጠኝ አንቀጾች ያሉት ህገ መንግስት አውጇል፡፡ በህገ መንግስቱ የራስ

ገዝ አስተዳደር እንደሚመሰርት የተመለከተና "ራስ ገዝ አከባቢዎችንና የአስተዳደር አከባቢዎችን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር 14/1980 አንቀጽ 2" መሠረት የኤርትራ፣ትግራይ፣የአሰብ፣የድሬዳዋ እና የኦጋዴን ራስ ገዝ አከባቢ፣በአንቀጽ 3 ደግሞ የሰሜን ጎንደር፣ደቡብ ጎንደር፣ሰሜን ወሎ፣ደቡብ ወሎ፣ምሥራቅ ጎጃም፣ምራብ ጎጃም፣መተከል፣አሶሳ፣ወለጋ፣ሰሜን ሸዋ፣አዲስ አበባ፣ምራብ ሸዋ፣ ደቡብ ሸዋ፣ምዕራብ ሐረርጌ፣ምሥራቅ ሐረርጌ፣አርሲ፣ባሌ፣ጋምቤላ፣ኢሊባቦር፣ከፋ፣ጋሞጎፋ፣ሲዳሞ፣ኦሞ እና ቦረና አስተዳደር አከባቢዎች አቋቁሟል፡፡ በዲሞክራሲያዊ መዕከላዊነት መርህ ወሠረት የአከባቢ ሀሳብ አመንጭነትን፣ተግባራዊ የሚያደርጉ ለልማት፣ሥራና ለአስተዳደር ቅልጥፍና አመች ሁኔታን የሚፈጥሩ ክፍሎችና እርከኖች መኖር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ራስ ገዝ እና አስተዳደር አከባቢዎችን ለማቋቋም እንደተቻለ በአዋጁ መግቢያ ላይ ጠቁሞ አልፏል፡፡ ቢሆንም ይኽ ከሚመለከታቸው ብሔር ብሔረሰቦች ጋር ሣይመከርበት የፀደቀ በመሆኑ የነበረውን ጦርነት አላስቆመም፡፡

ህገ መንግስቱ ኢሠፖ ብቸኛ የፖለቲካ ፖርቲ መሆኑን፣ የዳኞች የስራ ዘመን የሻንጐ የስራ ዘመን እንደሆነ እና በየወቅቱ የሚሾሙ መሆኑን ተመልክቷል፡፡ የአገሪቱ ኢኮኖሚ በመንግስት የሚመራ ሶሻሊስት ፖለቲካ ኢኮኖሚያዊ ስርዓት እንደሆነ ተደንግጓል፡፡ ህገ መንግስቱ በርካታ ለኢትዮጵያ ባዕድ የሆነ አስተሳሰቦችን ያካተተ ነው፡፡ሠርቶ አደሩ የሥልጣን ባለቤተነት፣አገርቱ የሚትከተለው ሶሻሊዝም ሪዮተ ዓለም መሆኑን፣ከሕዝብ የሚመረጡ እማኝ ዳኞች በፍርድ ቤቶች በዳኝነት እንዲሠሩ እንደሚደረግ፣እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡
ይኸም ህገ መንግስት የወታደራዊ መንግስት ስልጣን ፣ ህጋዊ ለማድረግ የሲቪል አስተዳደር ቅርጽ የሚሰጥ ካልሆነ በስተቀር በአገሪቱ በሁሉም ጫፍ ደም እያፋሰሰ የነበረው የህዝብ ሉዓላዊነት የብሔር ብሔረሰቦች የማንነትና የራስን እድል በራስ የመወሰን ጥያቄ መሠረታዊ መልስ የሚሰጥ ህገ መንግስት አልነበረም፡፡ በመሆኑም የተጀመረው የትጥቅ ትግል ተጠናክሮ በኢህአዲግ፣ አሸናፊነት ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ.ም የደርግ መንግስት ሲገረሰስ የህገ መንግስቱም ህልውና አክትሟል፡፡

## የመወያያ ጥያቄ

1. የደርግ ህገ መንግስት ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት ያስተላለፈው ህገ መንግስታዊ ዕሴት አለ ብለው ያስባሉ?
2. የደርግ ህገ መንግስት ከደርግ ጋር ህልውናው ያከተመው መንግስታዊ ህገ መንግስት ስለነበር ነው የሚለው አባባል እውን ነው ብለው ያስባሉ? ለምን?

### 1.3.1.3. .የኢፌዲሪ ህገ መንግስት የጸደቀበት ታሪካዊ ሁኔታ

### 1. የኢትዮጵያ የሽግግር ወቅት ቻርተር

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በአፄ ሀይለስላሴ ዘመነ መንግስትም ሆነ በደርግ ዘመን የፀደቁት ህገ መንግስቶች የህዝቡን መሠረታዊ ጥያቄና መብት ለማረጋገጥ የወጡ ሣይሆኑ በወቅቱ በትረ መንግስት ይዘው የነበሩትን ንጉሰ ነገስትና በኂላም ወታደራዊ ደርግ ስልጣን ህጋዊ ለማድረግና ለማጠናከር ታስበው የተቀረጸና የፀደቁ ናቸው፡፡ ስለሆነም በአገሪቱ ውስጥ ለነበረው የህዝብ የሉዓላዊነትና የብሔር ብሔረሰቦች የራስን እድል በራስ የመወሰን ጥያቄ ለመፍታት የሚችሉ አልነበሩም ፡፡ በመሆኑም በመጀመሪያ አምባገነን ፈላጭ ቆራጭ የነበረውን ዘውዳዊ አገዛዝ ለማስወገድ ከዚያም በኂላ የህዝቡን ንቅናቄ ውጤት በአቋራጭ በመንጠቅ ወታደራዊ አንባገነናዊ አስተዳደር የመሠረተውን ደርግ ለመገርሰስ በተካሄደው ተጋድሎ በአገሪቱ ከፍተኛ የሆነ ሰብአዊ እልቂት ደርሷል፡፡ ከፍተኛ ግምት ያለው ቁሣዊ ሀብት ወድሟል፡፡ ኢኮኖሚያዊ እድገቷ ወድቆ ህዝቦችዋ ከድህነት ወለል በታች የሚኖሩበት በምግብ ራሳቸውን መቻል አቅቷቸው በእርሀብና በእርዛት ያለቁበትና ለእርዳታና ልመና የተዳረጉበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡

“የሕዝቡን ፈቃድና ይሁንታ ያላገኘ መንግስት ህዝብን በጉልበትና በሀይል ለማስተዳደር የሚያደርገው ሙከራ ከፍተኛ የሆነ ሰብአዊና ቁሣዊ ውድመት ከማድረስና ማህበራዊ ቀውስ ከማስፋፋት ውጪ ሌላ ውጤት እንደማያስገኝ” በ18ኛው ምዕተ ዓመት አሜሪካዎች ነፃነታቸውን ሲያውጁ ያራምዱት የነበረው ሀሳብ በእኛ ሁኔታ በተግባር የተሞከረና ከበቂ በላይ ዕውነት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ የደርግ መንግስት ማናቸውንም ፖለቲካዊ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጥያቄ በሀይል እና በጉልበት ለመፍታት ያደረገው ሙከራ ከፍተኛ የሆነ ሰብአዊና እልቂት ቁሣዊ ሀብት ውድመት ከማስከተሉ በስተቀር መሠረታዊ የሆነውን የህዝቡን ሉዓላዊነትና የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት ጥያቄ

ለማዳፈን ባለመቻሉ በኢህአዲግ ግንባር ቀደም መሪነት በተደረገው ትግል ደርግ ለመገርሰስ ችሏል፡፡

ኢህአዲግ የደርግን ግዙፍ ሰራዊት በመደምሰስ መላ አገሪቱን ከተቆጣጠረ በኋላ ያገኘውን የህዝብ ተቀባይነት የፖለቲካ ድጋፍና ባለው ወታደራዊ አቅም ተኩራርቶ አገሪቱን ለብቻው ለማስተዳደር አልሞከረም፡፡ ይልቁንም በአገሪቱ ውስጥ የደርግን መንግስት በመቃወም የጦር መሣሪያ አንስተው ይፋለሙ የነበሩ ከሀያ በላይ የሚሆኑ የብሔር ብሔረሰብ የነጻ አውጪ ድርጅቶች ታዋቂ ግለሰቦች ጋር በመመካከር በሁሉም ሰላማዊ የፖለቲካ ሀይሎች ሙሉ ተሣትፎ የኢትዮጵያ የሽግግር ወቅት ቻርተር በኢትዮጵያ ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ሽግግር ጉባኤ እንድታውጅ አድርጓል፡፡ ይህ ቻርተር የአገሪቱ ህገ መንግስት ባይሆንም አገሪቱን ወደ ሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ ሂደት እስክትሸጋገር የተተዳደረችበት ጠቃሚ ህግ ሆኖ አገልግሏል፡፡
የኢትዮጵያ የሽግግር ወቅት ቻርተር የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች አንባገነናዊ ሥርዓትን በማስወገድ የራሳቸውን ዕድል በራሳቸው ለመወሰንና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታና ልማት ለማሸጋገር በድልድይነት ያገለገለና ከቀደምት ህግጋተ መንግስታት በአቀራረጽ በይዘቱና በአተገባበሩ መሠረታዊ ልዩነት ያለው ሰነድ ነው፡፡
የሽግግር ወቅት ቻርተር የሽግግሩ መንግስት በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰብአዊ መብት መግለጫ የተዘረዘሩትን የግለሰብ መብቶች ያለ አንዳች ገደብ የማክበር እና የማስከበር ግዴታ እንዳለበት በአንቀጽ አንድ  ከመደንገጉም በተጨማሪ በተለይ በደርግ ጊዜ እንደ ከባድ የአገር ክደት ወንጀል ተደርገው ያለ ፍርድ የሚያሳስሩና የሚያስገድሉ የነበሩትን ፤የእምነት፣ ሀሳብን የመግለጽ፣ የመደራጀት የመሰብሰብና የመቃወም መብትና የሌሎችን መብት በማይጋፋ መንገድ በማንኛውም የፖለቲካ እንቅስቃሴ ያለገደብ የመሣተፍና የፖለቲካ ፓርቲዎችን የማደራጀት መብትን ያረጋገጠ በአገሪቱ ታሪክ ውስጥ የፖለቲካ ፓርቲዎች በይፋ እንዲመሠረቱ ህጋዊ ማረጋገጫና ዋስትና የሰጠ ህግ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ቻርተሩ ለዘመናት መልስ ያላገኘውን የህዝቦች ሉዓላዊነትና የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት እስከ መገንጠል ማለትም የእያንዳንዱን ብሔር ብሔረሰብና ህዝብ ፡-

- የራሱን ማንነት የመጠበቅ የማስከበር ባህሉንና ታሪኩን የማበልጸግ እንዲሁም በማዕከላዊ መንግስት ውስጥ በነፃና አድሎ በሌለበት ሁኔታ የመወከል
- ከላይ የተጠቀሱት መብቶች ታገዱ ተረገጡ ወይም ተሸራረፉ ብሎ በሚያምንበት ጊዜ የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት እስከ ነፃነት ድረስ የማረጋገጥ መብት እንዳለው በግልጽና የተደነገገ የመጀመሪያው የህግ ሰነድ ነው፡፡

ቻርተሩ አምስት ክፍሎች ያሉት ሲሆን የሽግግር ወቅት መንግስት ሊመራባቸው የሚገቡ የውጪ ጉዳይ ፖሊሲና መርሆዎች የሽግግሩ መንግስት አወቃቀር ተዋጽኦ እና ስልጣንና ተግባር የሚደነገጉ ደንቦችን የያዘ የህግ ሰነድ መሆኑን ቻርተሩን በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡ ቻርተሩ ለአጭር ጊዜ አገሪቱ የምትመራበትና መንግስት የሚተዳደርበት የህግ ሰነድ እንጂ ለዘላቂነት እንዲያገለግል ታስቦ የፀደቀ ህገ መንግስት ባለመሆኑ በሽግግር ወቅት ለነበረው የተወካዮች ምክር ቤት የህገ መንግስት አርቃቂ ኮሚሽን የማቋቋም ግዴታ እንዳለበት በአንቀጽ 9 (ሰ) ይደነገጋል፡፡

የሽግግር ወቅት ቻርተር የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች የራሳቸውን ጉዳይ በራሳቸው የመወሰንና የማስተዳደር መብት ያረጋገጠ የህግ ሰነድ መሆኑን ከላይ ተገልጿል፡፡ የሽግግሩ መንግስት ይኸ በቻርተሩ የተረጋገጠው የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት ተግባራዊ ለማድረግ ይችል ዘንድ የብሔራዊ ክልላዊ የሽግግር መስተዳድሮችን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 7/1984 በማወጅ የራሳቸው የህግ አውጪ የህግ አስፈጻሚና  የህግ ተርጓሚ አካል ያላቸው <u>አስራ አራት</u> የሽግግር ወቅት ክልላዊ መስተዳድሮችን(ሐረር እና አዲስ አበባ ሁለት የከተማ ክልሎችን ጨምሮ) በማቋቋም  እና ክልላዊ የህግ አውጪ የህግ አስፈጻሚና የዳኝነትና የፍትህ አካላት ስልጣንና ተግባር ከክልል በታች በወረዳ ደረጃ በሚደራጀው የወረዳ ምክር ቤት፣ የወረዳ ህግ አስፈጻሚና የወረዳ የዳኝነትና የፍትህ አካላት ስልጣንና ተግባር በአዋጁ በማስቀመጥ የፌዴራላዊ የመንግስት አወቃቀርንና ስልጣንን ወደታችኛው የመንግስት እርከን በማውረድ በመንግስት አደረጃጀት ሥልጣን፣ ተግባር ክፍፍል ላይ የአብዛኛውን ህዝብ ጥያቄ ለመመለስ የሚያስችል ተግባራዊ እርምጃ ወስዷል፡፡

የሽግግሩ መንግስት የብሔር ብሔረሰቦችንና ህዝቦችን የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት ዕውን ለማድረግ በአዋጅ ቁጥር 7/1984 የብሔራዊ ክልላዊ የሽግግር መስተዳድሮችን ማቋቋሙ ብቻውን በቂ አልነበረም፡፡ ምክንያቱም በተቋቋሙት ክልሎችና በወረዳ ደረጃ ህግ የማውጣት ስልጣኑንና ህግ የማስፈጸም ሀላፊነቱን የሚሸከመው አካል በዲሞክራሲያዊ መንገድ የተመረጠና የህዝቡን ይሁንታና ፈቃድ ያገኘ መሆኑ ሌላው መሠረታዊ የህዝብ ጥያቄ ነበር፡፡ በሽግግር ወቅት የተቋቋመው በክልል ምክር ቤት እና የወረዳ ምክር ቤት አባላት ምርጫ በዴሞክራሲያዊ መንገድ ለማካሄድ ይቻል ዘንድ የሽግግር ወቅት  የተወካዮች ምክር ቤት የክልልና የወረዳ ምክር ቤት ምርጫ ማስፈፀሚያ አዋጅ በማውጣት የክልልና የወረዳ ምክር ቤት ምርጫ በማካሄድ ህዝቡ በመረጣቸው ተወካዮች የሚመራበት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመገንባት የሽግግሩ መንግስት ወደኋላ የማይልና የቻርተሩ ድንጋጌዎች በወረቀት ላይ ብቻ ተፅፈውና ተደንግገው የሚቀሩ የቃላት ስብስቦች ሣይሆኑ የአገሪቱ የወደፊት አቅጣጫ የሚወስኑ ገዥ ድንጋጌዎች መሆናቸውን በተግባር ለማረጋገጥ ችሏል፡፡

በአጠቃላይ የኢትዮጵያ የሽግግር ወቅት ቻርተር በአገሪቱ የነበረውን ፖለቲካዊ ውጥረት በማርገብ ለሚወክሉት ብሔር ብሔረሰብ ነፃነት እና ራሱን የቻለ መንግስት ለማድረግ ጦር ሰብቀው ከመንግስት ጋር ሲፋለሙ የነበሩ ከሃያ በላይ የሚሆኑ የነጻ አውጪ ድርጅቶች የጦርነት አማራጭን ትተው በጠረጴዛ ዙሪያ በመወያየት የእያንዳንዱ ብሔር ብሔረሰብና ህዝብ ማንነት ተከብሮና ክልላዊ መስተዳድር አቋቁሞ የራሱን ጉዳይ በራሱ የሚፈታ ፣ የጋራ የሆኑ ጉዳዮች ደግሞ ሁሉም ሚዛናዊ በሆነ መንገድ በተወከለበት በማዕከላዊ መንግስት በጋራ የሚወሰኑበትን ፌዴራላዊ ቅርፀ መንግስትና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓተ መንግስት በአገሪቱ እንዲቋቋም ለማድረግ የህግ ጥርጊያ መንገድ የከፈተና በሽግግር ወቅት የህገ መንግስት ያህል የአገሪቱ የበላይ ህግ ሆኖ ያገለገለ ሰነድ ነው፡፡

እዚህ ላይ መታየት ያለበት ቻርተሩ ተጨባጭ ለሆኑና አፍጥጠው ለመጡ የህዝብ ሉዓላዊነትና የፖለቲካ ስልጣን ጥያቄ ለብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች የማንነትና የራስን እድል በራስ የመወሰን ጥያቄ ለዜጐች መብትና የዴሞክራሲ ጥያቄ መሠረታዊ መፍትሔ ለመስጠት ባይችል ኖሮ ዛሬ ያለችው ዲሞክራሲያዊና ፌዴራላዊ ሪፑብሊክ

ኢትዮጵያ ከዓለም ካርታ ላለመጥፋቷ እርግጠኛ ሆኖና አፍን ሞልቶ ለመናገር አይችልም፡፡

የሽግግር ወቅት ቻርተር በወቅቱ ምላሽ ሊሰጣቸው ለሚገቡ መሠረታዊ የሆኑ የሰብዓዊ መብት የብሔር ብሔረሰቦችና የህዝቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት እና የዴሞክራሲ ጥያቄዎች ትክክለኛ የሆነ ምላሽ ሰጥቷል፡፡ ከሽግግሩ ቻርተር በኋላ ፀድቆ ሥራ ላይ የዋለው የኢፊዲሪ ህገ መንግስት መመዘን ያለበት በቻርተሩ መሠረታዊ የሆነ ምላሽ ያገኙ የህዝብ ጥያቄዎች በዘላቂነት ሰላም ዴሞክራሲና ልማት ለማረጋገጥ በሚችሉበት መንገድ ምን ያህል የትኩረት ማዕከል አድርጐ ለአፈጻጸማቸው የሚበጅ መርሆዎችንና ድንጋጌዎችን አቅፎ ይዟል ከሚለው ነጥብ አንጻር ካልተመዘነ በስተቀር የኢፊድሪ ህገ መንግስት አወቃቀር ፣ መርሆችና ሌሎች ድንጋጌዎች ፋይዳና ትርጉም በአግባቡ መገንዘብ የሚቻል አልሆነም፡፡

## *2. 1987 ኢፌዲሪ ህገ መንግስት*

## 1. <u>የሕገ መንግስት አወጣጥ ሒደት</u>

የኢፌድሪ ህገ መንግስት የረቂቅ ዝግጅትና አፀዳደቅ  በዝርዝር ከመመልከታችን በፊት የኢፌዲሪ ህገ መንግስት አረቃቅና አፀዳደቅ ሂደት አለም አቀፍ ተቀባይነት ካላቸው አሠራሮችን የተከተለ መሆኑን ለመመዘን ተቀባይነት ያላቸውን የህገ መንግስት አወጣጥ ሂደት መመርመር ያስፈልጋል፡፡  ከዚህ አንፃር ከላይየተጻፈ ህገ መንግስትን ባላቸው አገሮች ህገ መንግስት የማውጣት ሂደት በአራት ደረጃዎች ይከፈላል፡፡
 እነሱም፡- የማርቀቅ (Drafting) ፣ የመወያየት (Deliberation) ፣የመቀበል (Adoption) እና የማጽደቅ (Ratification) ደረጃዎች ናቸው፡፡

### ሀ/ <u>ማርቀቅ (Drafting )</u>

በአጭሩ ህገ መንግስት ማርቀቅ ማለት የተለያዩ የሙያ ዘርፎች ማለትም የቋንቋ ፣ የህግ፣ የታሪክ፣የፖለቲካል ሳይንስ፣ ወዘተ ባለሙያዎች በጋራ ኮሚቴ የመጀመሪያ ለውይይት መነሻ የሚሆን ሰነድ የሚያዘጋጁትን የሚመለከት ነው፡፡  ህገ መንግስትን

በማርቀቅ ደረጃ ሰነዱ ግልጽ የሚሆንበት፣ ከተለያዩ አቅጣጫ በተለይም ከማህበራዊ፣ ከኢኮኖሚያዊና ከፖለቲካዊ ለውጦች አንጻር ታይቶ የመጀመሪያ ወሳኝ መሠረት የሚጣልበት ደረጃ ነው፡፡

ይህ ደረጃ አብዛኛውን ጊዜ መነሻ የሚያደርገው የለውጥን መፈክር፣ የፖለቲካ ድርጅቶች ኘሮግራም ፣ የህዝቡን ፍላጐት ፣ ታሪክ ወዘተ ነው፡፡ ለምሣሌ ፡- የደቡብ አፍሪካ ከአፓርታይድ ነፃ መውጣት በኋላ የተረቀቀውና የወጣው ህገ መንግስት በዋነኝነት የሚያተኩረው በደቡብ አፍሪካ ብሔራዊ ኮንግረስ ("ANC") የድርጅት ኘሮግራም ላይ ነው፡፡

ለዚህም ነው አብዛኛውን ጊዜ እንደሌሎች ህጐች ህገ መንግሥትን በውጪ አገር ዜጐች ማርቀቅ የማይደገፈው፡፡ በዚህ ደረጃ አርቃቂው ኮሚቴ በርካታ ነገሮችን ከግምት ማስገባት ይጠበቅበታል፡፡

ለምሣሌ ፡- የአገሪቱን የውጪና የውስጥ ጉዳይ ፖሊሲ ፣የመከላከያ እና የአገር ሉአላዊነት ጉዳይ ፖሊሲን ፣ የኢኮኖሚ ፖሊሲ እና የመሳሰሉትን በማርቀቅ ደረጃ በጥንቃቄ መቃኘት ይጠይቃል፡፡

ለ/ <u>ውይይት ( Deliberation )</u>

በዚህ መልክ በባለሙያ የተረቀቀው ሰነድ ለሰነዱ ባለቤት ለሆነው ለአገሪቷ ዜጐች ለውይይት ይቀርባል፡፡ ይህ የውይይት ደረጃ እራሱን የቻለ ደረጃ ሲሆን የውይይት (Deliberation) ደረጃ ይባላል፡፡ በዚህ ደረጃ የዜጐች በሰነዱ ላይ ያላቸው አስተያየት በጥንቃቄና በዝርዝር ተሰብስቦ በሰነዱ ውስጥ እንዲካተት ይደረጋል፡፡

ይህ ደረጃ በጣም ጥንቃቄን ይጠይቃል የሚባለው በዚህ ደረጃ ሰነዱ የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦችን ማለትም የብዙኃኑንና የአናሳው ዜጐች መብትን መጠበቅን ስለሚያጠቃልል ነው፡፡

ሐ/ <u>የመቀበል ( Adoption )</u>

ይህ ከውይይት ቀጥሎ የሚመጣ ወሳኝ ደረጃ ነው፡፡ በዚህ ደረጃ ህዝቡ የተወያየበት ለተወካዮቻቸው እንዲካተቱ የተሰጡት ዋና ዋና ጉዳዮች መካተትና ያለመካተታቸው የሚረጋገጥበት ነው፡፡ በዚህ ደረጃ ሰነዱ ገዥ ሰነድ ፣ የበላይ ሰነድ ሆኖ ከመጽደቁ በፊት የሰነዱ ባለቤት ሰነዱን መቀበልና ያለመቀበሉን የሚያሳይበት ወሳኝ ደረጃ ነው፡፡

በዚህ ደረጃም ቢሆን ህብረተሰቡ መካተት ያለበትን መሠረታዊ ጉዳዮች በማጣራት እንዲካተት ማድረግ ወይንም የመጨመርም ሆነ የመቀነስ ሙሉ መብት አለው፡፡

*መ/* <u>*የማጽደቅ* ( Ratification )</u>

ህገ መንግስትን የማጽደቅ ደረጃ ህግ ሆኖ ከመውጣቱ በፊት ያለው ሌላ ወሳኝ ደረጃ ነው፡፡ ይህ ደረጃ ከመቀበል ቀጥሎ የሚመጣ ደረጃ ሲሆን የሰነዱ ባለቤት የሆነው በወከላቸው ሰዎች የተዘጋጀውን ሰነድ መቀበል አለመቀበሉን የሚያሳይበት ደረጃ ነው፡፡ በዚህ ደረጃ እንደ ተራ ወካይና ተወካይ ግንኙነት ሳይሆን ውክልናው ከተራ ውክልና የተሻገረ ኃላፊነት ያለው ተግባር መፈጸሙ የሚረጋገጥበት ደረጃ ነው፡፡

በዚህ ደረጃ ሂደቱን ጠብቆ ለረጅም ዘመን መስራት የሚችል እና በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት ያለው ሰነድ የሚጸድቅበት ነው፡፡ ስለዚህም የማጽደቅ ደረጃ ከላይ የተጠቀሱትን ተከታታይ ደረጃዎችን ማለትም የማርቀቅ፣ የውይይትና የመቀበል ደረጃዎችን አልፎ የሚመጣ የመጨረሻ ደረጃ ነው፡፡ ይህን ደረጃ አልፎ ሰነዱ ከፀደቀ ወደ ገዥና የበላይነት ያለው ሰነድ የሚያድግበት ደረጃ ነው፡፡ በአጭሩ ህገ መንግስቱ እድገቱን በመጨረስ እንደሙሉ ሰነድ የሚቆጠርበት ነው፡፡

በአጠቃላይ አሁን በአለውና ተቀባይነት ባለው የአለም ተሞክሮ አንድ ህገ-መንግስት በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጪ ተቀባይነት ያለው ሰነድ ለመሆን እነዚህ ደረጃዎችን በጥንቃቄ ማለፉ በተቀባይነቱ (Legitimacy) ላይ ከፍተኛ ስፍራ አለው፡፡
እነዚህን ሂደቶች በግልጽና በአግባቡ ያለፈ ሰነድ ወይንም ህገ-መንግስት ከፍተኛ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

ከዚህ አንጻር ለአብነት ያህል የኢፌዲሪ ሕገ-መንግስትን ብንወስድ በውይይቱ ደረጃ መሠረታዊ ጉዳዮች በውይይት ደረጃ ሊካተቱ ችለዋል፡፡ በዚህ ደረጃ ግልጽ ፣ አሳታፊ፣ ሁሉ አቀፍ፣ መግባባት የተደረሰበት፣ የሚፈለገውን ሥርዓተ መንግስትና ቅርጸ መንግስት መያዙ የተረጋገጠበት ወሳኝ ደረጃ ነው፡፡ የውይይት ሂደቱ የተካሄደው በህዝቡ በተወከሉ የህገ መንግስት ጉባኤ አባላት ነው፡፡ ይህ ብቻም ሳይሆን ህብረተሰቡ ባለበት አካባቢ ሕገ መንግስቱ ውስጥ መካተት ባለባቸው ጉዳዮች ላይ በመወያየት በቀጥታም ሆነ በተወካዮቻቸው በኩል በህገ መንግስቱ ውስጥ ፍላጎቱ ተካቷል፡፡

በአጠቃላይ የኢፌዲሪ ህገ መንግስት ከተለያዩ ሙያ በተውጣጡ የሕገ መንግስት አርቃቂ ኮሚቴ ተረቀ በህገ መንግስት ጉባኤ እና በህብረተሰቡ ውይይት ተካሂዶ በህዝቡ ተቀባይነት ከአገኘ በኂላ በህገ መንግስት ጉባኤ ህዳር 29 ቀን 1987 ዓ.ም ስራ ላይ እንደዋለ በህገ-መንግስት መግቢያ ላይ ሰፍሯል፡፡

## *2. ህገ መንግስት ስለሚፀድቅበት ሁኔታ*

ከላይ በተገለጸው መሠረት የኢፌዲሪ ህገ መንግስት የፀደቀ መሆኑ ማንም ሊቀለብሰው የማይችል ሀቅ ቢሆንም የኢፌዲሪ ህገ መንግስት በህዝበ ውሣኔ ሣይሆን በህገ መንግስት ጉባኤ የፀደቀ በመሆኑ በህዝቡ ፍላጐት እና ስምምነት የፀደቀ ህገ መንግስት አይደለም በማለት ሰዎች ሲከራከሩ የሚሰሙበት ሁኔታ አለ፡፡ በመሆኑም እነዚህ ሰዎች የሚያነሱትን የመከራከሪያ ነጥብ ትክክለኛነት ለመመዘን በመጀመሪያ በዓለም ላይ ህገ መንግስት የሚፀድቅባቸውን መንገዶች ማየትና መመርመር ያስፈልጋል፡፡
በዓለማችን ተቀባይነት ያላቸው ለህገ መንግስት መፅደቅ ውሣኔ የሚሰጥባቸው አራትመንገዶች እንዳሉ የሚያከራክር አይደለም፡፡
የመጀመሪያው ህገ መንግስቱ በሚጸድቅበት ወቅት ህግ የማወጅና የመደንገግ ስልጣን ባለው አካል በህግ በሚወጣበት ሥርዓት ወይም ህግ ከሚወጣበት ጠበቅ ባለ የድምጽ አሰጣጥ ሥርዓት ህገ መንግስት የሚታወጅ መሆኑ ነው፡፡ ይኸም ማለት በወቅቱ ስራ ላይ ያለው የህግ አውጪ ምክር ቤት በአብላጫ ድምጽ ወይም በሁለት ሶስተኛ ድምጽ በህገ መንግስቱ ረቂቅ ላይ ከመከረ በኂላ ህገ መንግስቱን የሚያጸድቅበት አሰራር እንዳለ እንኳንስ ለዓለማችን ለእኛም አገር አዲስ አይደለም፡፡  በዓለማችን እንግሊዝ፣ እስራኤል፣ የህንድናሌሎች አገሮች ህገ መንግስት በዚህ አይነት የፀደቁ ናቸው፡፡  በመሆኑም የኢፌድሪ ህገ መንግስት  በሽግግር ወቅት በነበረው የተወካዮች ምክር ቤት ፀድቆ ቢሆን እንኳ ተቀባይነት ያለው አሰራር ሊሆን ይችል እንደነበርና በዚህ ምክንያት ገዢና የህጐች ሁሉ የበላይ ህግ መሆኑ እንደማይቀር ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ተቀባይነት ያለው የህገ መንግስት የማፅደቂያ መንገድ የህገ መንግስቱን ረቂቅ ላይ በህዝበ ውሣኔ ድምጽ እንዲሰጥበት ማድረግ ነው፡፡ ህዝበ ውሣኔ አንደኛው

የህገ መንግስት ማፅደቂያ መንገድ እንጂ ብቸኛውና ተቀባይነት ያለው የህገ መንግስት ማፅደቂያ መንገድ አይደለም፡፡ በተቃራኒው ህዝበ ውሣኔ የሚሰጠው በእያንዳንዷ የህገ መንግስት ክፍልና የህግ ድንጋጌ ሣይሆን በሰነዱ ላይ በአጠቃላይ በመሆኑ ይኸ አሰራር መስተካከል የሚገባቸውን ህገ መንግስታዊ ድንጋጌዎች ተመካክሮና ተከራክሮ አስተካክሎ ለማጽደቅ የማያስችል ፣ ከቀረበው ረቂቅ አብዛኛው ድንጋጌ የተስማማው ድምጽ ሰጪ የማይስማማባቸው ሀሳቦችና ድንጋጌዎች ቢኖሩ እንኳን ተስማምቻለሁ በማለት ህገ መንግስቱን ከነችግሮቹ የሚያፀድቅበት ሁኔታ መኖሩን አንስተው ህዝበ ውሣኔ ህገ መንግስት ለማፅደቅ ተመራጭ እና ውጤታማ የሆነ አሰራር እንዳልሆነ የሚከራከሩ ሰዎች አሉ፡፡

በሶሶተኛ ደጃ ተቀባይነት ያለው የህገ መንግስት ማፅደቂያ መንገድ ህዝቡ በህገ መንግስቱ ረቂቅ ላይ በሰፊው መክረው እና በሰከነ ሁኔታ የተለያዩ አማራጮችን አይተው ለአገሪቱ የሚበጅ ህገ መንግስት እንዲያጸድቁ በሚወክላቸው የህገ መንግስት ጉባኤ አባላት ህገ መንግስቱ የሚፀድቅበት ሁኔታ ነው፡፡ የህገ መንግስት ጉባኤ አባላት በህገ መንግስቱ ረቂቅ ላይ መክረው ተከራክረውና ጥልቅ ውይይት አድርገው ህገ መንግስቱን እንዲያፀድቁ ህዝቡ በድምጽ የወከላቸውና ውክልናቸውም ይህንን ከፍተኛና ልዩ ሀላፊነት እንዲወጡ ነው፡፡ በዚህ ዓይነት መንገድ የፈረንሣይና የሌሎች በርካታ አገሮች ህግጋት መንግስታት ፀድቀው ሥራ ላይ እንዲውሉ ለመረዳት ይቻላል፡፡ የኢፌዲሪ ህገ መንግስት በህገ መንግስት ጉባኤ አባላት ተመክሮበት መጽደቁ ህገ መንግስት ለማጽደቅ ተቀባይነት ካላቸው አሰራሮች በአንደኛው መንገድ የፀደቀ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ በመሆኑም ይህንን እንደ ጉድለት አንስተው የሚከራከሩ ሰዎች በዓለማችን ህገ መንግስትን ለማፅደቅ አንድ ወጥ የሆነ አሰራር (ፎርሙላ) የሌለ መሆኑን የአንዲት አገር ህገ መንግስት እንደአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ አንደኛው አማራጭ ተጠቅሞ ማፅደቅ የሚቻል መሆኑም በተለይም የበርካታ ብሔር ብሔረሰብ እና ህዝቦች አገር በሆነችው ኢትዮጵያ የሁሉንም ሀሳብና ፍላጐት የሚያካትት ህገ መንግስት ለማውጣት እያንዳንዱ ብሔር ብሔረሰብ ሀሳቡን በነፃ አቅርቦ የሚወያይበትን መንገድ መምረጥ አስፈላጊ መሆኑን መገንዘብና የህገ መንግስቱ በህገ መንግስት ጉባኤ መጽደቅ ተገቢና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያለው አሰራር መሆኑን እንዲገነዘቡት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

በአራተኛ ደረጃ ህገ መንግስት የሚፀድቅበት መንገድ በመንግስታት መካከል የሚደረግ ስምምነት ነው፡፡ ይህም የሚሆነው የተለያዩ ሉዓላዊ አገሮች በፌዴሬሽን አንድ መንግስት ለመመስረት ሲስማሙ የፌዴራል ህገ መንግስት ሆኖ በሚያገለግለው ሰነድ ላይ መንግስታቱ ከተወያዩ ከተደራደሩ በኂላ የፌዴራሉ ህገ መንግስት በፊርማቸው በማፅደቅ የፌዴራል መንግስቱን የሚመሰርቱበት አሰራር እንዳለ የሰሜን አሜሪካ መንግስታት ህብረት (USA) ህገ መንግስት አፀዳደቅና በአሁኑ ሰዓት ደግሞ የአውሮፓ ህብረት ህገ መንግስት ለማጽደቅ የሚደረገውን ውይይትና ድርድር በአብነት አንስቶ ለማየት ይቻላል፡፡

ከላይ የተገለጹት የህገ መንግስት ማፅደቂያ መንገዶች እንዳሉ ሆኖ በአንድ ታሪካዊ ክስተት ህገ መንግስታቸው በሌሎች አገሮች ተረቅቀው ፀድቆ ተሰጥቷቸው እስከአሁን ይኸ ነው የተባለ መሠረታዊ ለውጥ ሣያደርጉበት በህገ መንግስቱ የሚተዳደሩ አገሮች እንዳሉ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ እነዚህም  በአላይድ መንግስታት ጦር ከተሸነፉ በኂላ ምዕራብ ጀርመንንና ጃፓንን የማስተደደር ሀላፊነት የነበረባቸው አገሮች ለእነዚህ አገሮች የሚሆን መሰረታዊ ህጎች ያፀደቁ መሆኑንና አገሮቹም ይኸ ነው የሚባል መሠረታዊ ለውጥ ሣያደርጉ ከግማሽ ምዕተ ዓመት በላይ እንደተዳደሩባቸው የሥነ ህገ መንግስት ምሁራን ይገልጻሉ፡፡

በአጠቃላይ ስለ ህገ መንግስት ሲነሳ የረቂቁ ሒደትና አፀዳደቁ ዲሞክራሲያዊ የመሆኑ ሁኔታ አስፈላጊ ሆኖ ይኸ ብቻውን በቂ አይደለም፡፡ በህዝብ ተሣትፎ የፀደቀው ህገ መንግስት ለአገሪቱ መሠረታዊና ቁልፍ  የፖለቲካ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት የማይችል ከሆነ በአገሪቱ ሰላምና መረጋጋትን ለማረጋገጥና የልማት መሣሪያ ሆኖ ለማገልገል እንደማይቻለው ግንዛቤ ሊያዝበት ይገባል፡፡ ከዚህ አንጻር ህገ መንግስት በሒደቱ ዲሞክራሲያዊነትና በይዘቱ ችግር ፈቺ ሆኖ ከመገኘቱ አንጻር መመዘን አለበት፡፡ የኢፌዲሪ ህገ መንግስት እነዚህን መሠረታዊ ነጥቦች የሚያሟላ ህገ መንግስት እንደሆነ የፀደቀበትን ሒደትም ሆነ ይዘቱን በመመርመር ለመረዳት ይቻላል፡፡

## *የመወያያ ጥያቄዎች*

1. የክልል ህገ መንግስት ያፀደቁት በክልሉ ህግ አውጪ ሁለት ሶስተኛ ድምፅ እንደሆነ በዚህ ዙሪያ ጥናት ያደረጉ ምሁራን ይገልፃሉ፡፡ ለመሆኑ ይኸ የአፀዳደቅ ሂደት ተገቢ ነው ብለው ያምናሉ? ለምን ?

2. የኢፌድሪ ህገ መንግስት አወቃቀርና አፀዳደቅ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያላቸው አሰራሮች ያሟላ ነው ብለው ያስባሉ? ለምን ?

## *3 የኢፊድሪ ህገ መንግስት ረቂቅ ዝግጅትና አፀዳደቅ*

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ህገ መንግስት የሽግግር ወቅት ቻርተር የደርግ መንግስት ሲወድቅ አገሪቱን በጊዜያዊነት ለመምራት የተመሠረተው የሽግግር ወቅት መንግስት የሚመራባቸውን መርሆዎች የመንግስትን አወቃቀር ተዋጽኦና ስልጣንና ተግባር እንደዚሁም የሽግግር መንግስቱ ሊያከብራቸውና ሊያስፈጽማቸው የሚገቡ የዜጐች መብትና የብሔር ብሔሰቦችን መብት የሚደነግግ ለሽግግር ወቅት ብቻ የሚያገለግል ህግ እንደነበር ከላይ ተገልጿል፡፡ ለብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን ጥያቄ ዘላቂ መፍትሔ ለመስጠትና የተሟላ ዲሞክራሲያዊ አስተዳደር ለመመሥረት ለእነዚህ ቁልፍ ችግሮች የተሟላና ዘላቂ የሆነ ምላሽ የሚሰጥ ህገ መንግስት ተረቅቶ ለህዝቡ መቅረብ እንደሚገባውና ይኸም የሽግግሩ ወቅት ተወካዮች ምክር ቤት ግዴታና ሀላፊነት እንደሆነ የሽግግር ወቅት ቻርተር አንቀጽ 9 (ሰ) በግልጽ ደንግጓል፡፡

የሽግግር ወቅት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይህንን በቻርተሩ የተጣለበትን ህዝባዊ አደራና ሀላፊነት ለመወጣት በነሀሴ ወር 1984 ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 24/1984 ዓ.ም የህገ መንግስት አርቃቂ ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ በማወጅ የህገ መንግስት አርቃቂ ኮሚሽን አቋቁሟል፡፡ አርቃቂ ኮሚሽኑ ዋና ጽ/ቤቱ የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ጥናት ኢንስቲትዩት ሆኖ በህግ በተሰጠው ስልጣንና ሀላፊነት መሠረት ግዴታውን ለመወጣት በትጋትና በብርታት እንደሰራ የአርቃቂ ኮሚሽኑ ሪኮርዶች የሥራ እንቅስቃሴዎች በማየት ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

**የአርቃቂ ኮሚሽኑ ዋና ተልዕኮ ፡-**

- በቻርተሩ መንፈስ አዲሲቷ ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ የምትመሠረትበትንና የምትተዳደርበትን ሕገ መንግስት በማርቀቅ ፡
- ረቂቅን በሽግግር ወቅት ለነበረው ለተወካዮች ምክር ቤት ማቅረብ የምክር ቤቱን ስምምነት ሲያገኝ ለህዝብ ውይይት ማቅረብ ፡፡
- ከህዝብ በውይይት በተገኘው አስተያየት መሠረት ረቂቁን በማሻሻል የመጨረሻ ረቂቁን አዘገጅቶ በተወካዮች ምክር ቤት ማፀደቅ፡
- በተወካዮች ምክር ቤት የፀደቀውን ረቂቅ ለህገ መንግስት ጉባኤ ማቅረብ እንደሆነ በአዋጁ አንቀጽ 4 በግልጽ ተደንግጓል፡፡

የኢፌዲሪ ህገ መንግስት ረቂቅ የተዘጋጀው በተወካዮች ምክር ቤት በተሰየሙና ተልዕኳቸው ስልጣንና ሀላፊነታቸው በህግ ተዘርዝሮ በተሰጣቸው ሀያ ዘጠኝ የህገ መንግስት አርቃቂ ኮሚሽን አባላት ሲሆን በኮሚሽኑ ውስጥ የተወካዮች ምክር ቤት አባላት የፖለቲካ ድርጅቶች ተወካዮች ፣ የሰራተኛ ማህበር ተወካዮች ፣ የንግድ ምክር ቤት አባላት ተወካዮች ፣ የህግ ባለሙያዎች ማህበር ተወካዮች ፣ የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር ተወካዮች ፣ የጤና ባለሙያዎች ማህበር ተወካዮችና የሴቶች ተወካዮች የተውጣጣ እንደሆነ ከማቋቋሚያ አዋጁና ከአርቃቂ  ኮሚሽኑ አባላት ስብጥር ለመረዳት ይቻላል፡፡

ኮሚሽኑ የመጀመሪያውን ረቂቅ አዘጋጅቶ የሽግግሩን የተወካዮች ምክር ቤት ስምምነት ካገኘ በኂላ በረቂቁ ላይ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን እና የህዝቡን አስተያየት ለማሰባሰብ፡-

- በህገ መንግስታዊ ፅንሰ ሀሳቦችና በረቂቅ ህገ መንግስቱ ላይ የተለያዩ የትምርት ተቋሞች እና መንግስት መገናኛ ዘዴዎች ውይይቶችን ሴሚናሮችንና ሲምፖዚየሞችን በማዘጋጀት ረቂቁን ሊያዳብሩ የሚችሉ ሀሳቦችን እና አስተያየቶችን የማሰባሰብ ሥራ እንደሰራ፣
- ረቂቁ ለክልል መስተዳድር ምክር ቤቶች እና ለወረዳ ምክር ቤት አባላት ቀርቦ እንዲወያዩበት እና አስተያየታቸውን እንዲሰጡበት ማድረጉንና ከምክር ቤቶቹ የተሰጠውን አስተያየት በግብዓትነት መጠቀሙን፡

- እንደዚሁም በረቂቅ ህገ መንግስቱ ላይ ህዝቡ በየቀበሌው ውይይት በማድረግ አስተያየት ሊሰጥ የሚችልበትን መድረክ በማመቻቸት ህዝቡ በረቂቁ ላይ የሰጠውን ትችትና አስተያየት ማሰባሰቡን በግብዓትነት መጠቀሙን ፡
- ኮሚሽኑ በተለያየ ጊዜ ረቂቅ ህገ መንግስቱን አስመልክቶ ከህዝብ ለሚቀርቡለት ጥያቄዎች ማብራሪያና ገለጻ በመስጠት ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የቀረቡትን አስተያየቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች በማካተት የመጨረሻውን ረቂቅ ህገ መንግስት ለተወካዩች ምክር ቤት አቅርቧል፡፡ የመጨረሻው ረቂቅ የቀረበለት የተወካዮች ምክር ቤት በረቂቁ ላይ ከተወያየና ተገቢ ናቸው የሚላቸውን ተጨማሪና የማሻሻያ ሀሳቦች በማከል ረቂቁን በማፅደቅ ለህገ መንግስት ጉባኤ እንዲቀርብ ወስኗል፡፡
- የተወካዮች ምክር ቤት ፣የህገ መንግስቱ አርቃቂ ኮሚሽን ሥር ከሚያደረገው ክትትል ጎን ለጎን ፣ የህገ መንግስት ጉባኤ አባላትንና ሌሎች ምርጫዎችን ነፃ ገለልተኛና ሚዛናዊ በሆነ መንገድ፣ ለማከናወን የሚያስችል የኢትዮጵያ ምርጫ ህግ ቁጥር 64/1985 ዓ.ም በማውጣት የህገ መንግስት ጉባኤ አባላት ምርጫ እንዲከናወን አድርጓል፡፡ ከዚህ በኋላ የህገ መንግስቱ የመጨረሻ ረቂቅ በህዝብ ድምጽ ለዚሁ ተግባር ለተመረጡት የህገ መንግስት ጉባኤ በማቅረብ በሰፊው ከተመከረበት በኋላ ህገ መንግስቱን በማፅደቅ በህግ የተጣለበትን ከፍተኛ ሀላፊነት በብቃት ተወጥቷል፡፡

ከዚህ ነባራዊ ሀቅ ተነስተን የኢፌዲሪ ህገ መንግስት የረቂቅ ዝግጅት ሒደት ስንመለከተው የህገ መንግስት ረቂቅ አሰራር ሒደት ሊከበሩ የሚገባቸውን መሠረታዊ መርሆዎች ተግባራዊ በማድረግ የተከናወነ ነው፡፡ የአርቃቂ ኮሚሽኑ አባላት ተዋጽኦ ለህዝብ ግልጽ በሆነና በህግ ስልጣንና ሀላፊነታቸው የተዘረዘረ መሆኑን፣ በተወካዮች ምክር ቤት በመጀመሪያ ደረጃ ተቀባይነት ያገኘው ረቂቅ ለክልሎችና የወረዳ ምክር ቤት አባላትና መላው ህዝብ ተወያይቶ አስተያየት የሰጠበት መሆኑን፣ የመጨረሻው ረቂቅ በተወካዮች ምክር ቤት ታይቶና ፀድቆ ለህገ መንግስት ጉባኤ የቀረበ መሆኑን ሒደቱ ግልጽ አሳታፊና ዲሞክራሲያዊ እንደነበር ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

የህገ መንግስቱ ረቂቅ በህገ መንግስት ጉባኤ በሰፊው ተመክሮበት ስለመጽደቁ ከላይ እንደተገለጸው በረቂቁ ዝግጅት ሒደት የተለያየ የህብረተሰብ ክፍሎችና መላው ህብረተሰብ እንደዚሁም በክልልና በወረዳ ደረጃ በዴሞክራሲያዊ መንገድ የተመረጡ የህዝብ እንደራሴዎች በሰፊው የመከሩበት እና አስተያየት የሰጡበት እንደሆነ አሌ የሚባል አይደለም፡፡

በክልሎችና በወረዳ ምክር ቤቶች እና በምልዓተ ህዝቡ ተመክሮበት በተወካዮች ምክር ቤት ተመርምሮ ለህገ መንግስት ጉባኤ የቀረበ ረቂቅ ህዝቡ እሱን በመወከል ረቂቁን በጥልቀት መርምረው እና መክረው የአገሪቱ ዘላቂ ሰላም ዲሞክራሲና ኢኮኖሚያዊ እድገት ለማስመዝገብ መሠረት የሚሆን አገሪቱና መንግስት የሚተደደሩበት ህገ መንግስት እንዲያጸድቁለት ወክሎ በላካቸው የህገ መንግስት ጉባኤ አባላት፣ በህገ መንግስቱ አወቃቀር በይዘቱ ማለትም በእያንዳንዷ አንቀጽና ቃል ወይም ሀረግ ዙሪያ በነፃነት በሰፊው ተከራክረውና መክረው ያፀደቁት ህገ መንግስት ነው፡፡

በህገ መንግስቱ ረቂቅ ላይ የህገ መንግስት ጉበኤ አባላት የመሰላቸውና ሀሳብና አስተያየት በነፃነት አራምደዋል፡፡ አባላቱ አሣማኝ ናቸው የሚሏቸውን የመከራከሪያና የማሻሻያ ሀሳብ አንስተው ውይይት እንዲደረግበት አድርገዋል፡፡ በዚህ አይነት ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ የህገ መንግስት ጉባኤ አባላት በማናቸውም መንገድ የማይታረቁ ፍጹም ተቃራኒ የሆኑ ሀሳቦችን አንስተው የተከራከሩ መሆኑን የህገ መንግስት ጉባኤ ውይይት ባደረገበት ወቅት የተያዘውን ቃለ ጉባኤ ሁሉንም ሣይሆን አንድ ወይም ሁለት ገጽ ብቻ በማንበብ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ የጉባኤው አባላት ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ አለን የሚሉትን የማሻሻያ ሀሳብ አስተያየት ወይም ክርክር ካቀረቡ በኋላ ጉዳዩ የጉባኤው አባላት ድምጽ እየሰጡበት የጉባኤ አባላት አብላጫ ድምጽ ያገኘው ድጋፍ ሀሳብ በህገ መንግስቱ ውስጥ እየተካተተ የአብዛኛውን ድምጽ ድጋፍ ያላገኘ ሀሳብ ደግሞ ውድቅ እየሆነ ነፃ ግልጽና ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ተመክሮበትና ተዘክሮበት የፀደቀ ህገ መንግስት መሆኑን የጉባኤውን ሪኮርዶች በመመርመር ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ ስንመለከተው የኢፌዲሪ ህገ መንግስት ከቀደምት ህገ መንግስቶች በተለየ ሁኔታ የህገ መንግስቱ ረቂቅ ላይ መላው ህዝብ ነፃና ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ መክሮ ትችትና አስተያየት ሰጥቶበት ፡-

- የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች የሽግግር ወቅት ቻርተር ያረጋገጠላቸውን የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት ተጠቅመው ያቋቋማቸው የክልል መስተዳድር እና የወረዳ መስተዳድር ምክር ቤት አባላት በሰፊው መክረውበትና አስተያየት ሰጥተውበት ፣
- የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ተወካይ የሆኑትና በህዝብ የተመረጡት የህገ መንግስት ጉባኤ አባላት ያለምንም ፍርሀት ሀሳባቸውን ሣይገድቡ ተከራክረውበት እና መክረውበት ፣
- ለዘመናት ምላሽ ሳይሰጠው ለኖረው የሰብአዊ መብቶች መከበር ለህዝቡ ሉዓላዊነትና የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች የማንነትና የራስን እድል በራስ የመወሰን ጥያቄ እና ለአገራችን አንገብጋቢ ለህልውናውና ጉዳይ ለሆነው የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ህጋዊ መሠረት ሆኖ እንዲያገለግል በህዝብ ሰፊ ተሣትፎና በዲሞክራሲያዊ መንገድ የፀደቀ ህገ መንግስት መሆኑን ለመረዳት ይቻላል፡፡
- የኢትዮጵያ የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ለዚህ ይህንን ልዩ ተግባር እነሱን ወክለው እንዲያከናውኑላቸው በምርጫ ወክለው የላኳቸው የህገ መንግስት ጉባኤ አባላት ህገ መንግስቱ ረቂቅ ላይ ሲመክሩና ሲወያዩ በአገር የግዛት አንድነት በማስጠበቅ ስም ለዘመናት አገሪቱን የመሩት ዘውዳዊ አንባገነናዊ ሥርዓትና የእነርሱ ተቀጥያ የሆነው የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች የማንነትና የራስን ዕድል በራስ የመወሰን ጥያቄ በሀይልና በጦርነት ለማፈን ቢሞክሩም የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የደርግን ሰራዊት በጦርነት በማሸነፍ ማንነታቸውን በማስከበር የራሳቸውን እድል በራሳቸው የመወሰን መብታቸውን በማረጋገጥ የክልል መስተዳድሮችን በማቋቋም የትግላቸውን ፍሬ እያጣጣሙ መሆናቸውን ከግምት ውስጥ በማስገባት፤

ለዘመናት በዘላቀው የአብሮነት ጉዞ የገገሯው መደብ አባላት ሊካድና ሊስተባበል የማይችል የብሔርና የመደብ ጭቆና ያደረሱባቸው መሆኑንና ብሔራዊ ማንነታቸውንና

መብታቸውን ጠብቀው ለወደፊቱ በአንድነት ለመዝለቅ በፊት የነበረውን የተዛባ ግንኙነት መስተካከልና መታረም እንዳለበትና ግንኙነታቸውን በእኩልነትና በመከባበር መርሆዎች ላይ መመስረት እንዳለበት በመተማመን፤

የራሳቸውን በራሳቸውን የማስተዳደር ፣ የራሳቸውን ጉዳይ በራሳቸው የመወሰን፣ በራሳቸው ቋንቋ የመጠቀምና የመዳኘት መብታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በፌዴሬሽን አብረው ለመቀጠል የሚጠቅሙ የጋራ እሴቶች ያላቸውና ልዩነትን የሚያከብር አንድ የፖለቲካ ማህበረሰብና አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ቢገነቡ ሊያገኙ የሚችሉት የጋራ ጥቅም ያለ መሆኑን በጥልቀት በመመርመር ፤

በክልሎችም ሆነ በፌዴራል ደረጃ ሰብአዊ መብቶች በተሟላ ሁኔታ ህገ መንግስታዊ ዋስትና ካልተሰጣቸውና ካልተከበሩ በአገሪቱ ዘላቂ ሰላምን ለማስፈንና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መገንባት እንደማይቻል በመገንዘብና ሌሎች አለማዊና አህጉራዊ ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ሁኔታዎችን ታሳቢ በማድረግ የኢፌዲሪን ህገ መንግስት እንዳፀደቁት በህገ መንግስቱ መግቢያ ላይ ካሰፈርዋቸው መሠረታዊ ሀሳቦችና በህገ መንግስቱ ይዘት ላይ በዝርዝር ካደረጉት ውይይትና ክርክር ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

በመሆኑም ህገ መንግስቱ ለዘመናት መልስ ያላገኙ ቁልፍ የፖለቲካ የኢኮኖሚ እና የማህበራዊ ጥያቄዎችን በዘላቂነት ምላሽ በመስጠት የግለሰብ ሰብዓዊ መብቶችና የብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መብት በእኩል ደረጃ በተሟላ ሁኔታ የተከበረባት ፌዴራላዊና ዲሞክራሲያዊ የለማች ኢትዮጵያ ለመገንባት በሚያስችል በመንገድ በስከነ አእምሮና በጥንቃቄ ተመክሮበት የፀደቀ መሆኑን በመገንዘብ ህገ መንግስቱን ለማስከበርና ተግባራዊ ለማድረግ በትጋት መስራት ይገባናል፡፡

## *የመወያያ ጥያቄ*

1. የክልልም ህገ መንግስት ፣ረቂቅ ዝግጅትና አፀዳደቅ ያብራሩ፡፡
2. የክልሉም ህገ መንግስት በማን በኩል እንደፀደቀና የአፀዳደቅ ሂደቱ ትክክለኛነት ይመዝኑ፡፡

## 1.4. የሕገ-መንግሥቱ መርሆዎች

<u>ዝርዝር አላማዎች</u>

**ከዚህ ክፍል ትምህርት በኃላ፡**

- ☐ ስለሉአላዊነትና የህዝብ ሉአላዊነት ምንነት ይተነትናሉ፡፡
- ☐ በኢፌዲሪ ህገ መንግስታዊ ስርአት የኢትዮጵያ ህዝቦች የሉአላዊ ስልጣን ባለቤት መሆናቸውን የሚያረጋግጡ ስርአቶችን ይተነትናሉ፣ ለተፈጻሚነታቸውም የራሳቸውን ሚና ለመጫወት ዝግጁ ይሆናሉ፡፡
- ☐ በኢትዮጵያ ያለው የምርጫ ስርአትና አፈጻጸም ዴሞክራሲያዊ መርሆዎችን የተከተለ መሆኑን ይተነትናሉ፡፡
- ☐ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር ከዴሞክራሲ ስርአት የማይነጠል መሆኑና የኢፌዲሪ ህገ መንግስት መሰረታዊ መርሆ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡
- ☐ በኢፌዲሪ ህገ መንግስት ሀይማኖትና መንግስት የተለያዩ መሆናቸውን ያስረዳሉ ሀይማኖትና የመንግስት ስራ እንዳይደባለቅ የራሳቸውን ሚና ለመጫወት ዝግጁ ይሆናሉ፡፡
- ☐ የህግ የበላይነት መገለጫና ማስፈጸሚያ መንገዶችን ይተነትናሉ፣ በኢፌዲሪ ህገ መንግስታዊ ስርአት የህግ የበላይነት ማረጋገጫ ስርአቶችን በዝርዝር ይተነትናሉ፣ ለህግ የበላይነት መከበርም የራሳቸውን ሚና ለመጫወት ዝግጁ ይሆናሉ፡፡
- ☐ ተጠያቂነትንና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የተዘረጋውን ህገመንግስታዊ ስርአት ይተነትናሉ ለተፈጻሚነታቸውም ዝግጁ ይሆናሉ፡፡

**ውድ ሰልጣኞች፣**

- ☐ በኢፌዲሪ ህገ መንግስታዊ ስርዓት የኢትዮጵያ ህዝቦች የሉአላዊ ስልጣን ባለቤት መሆናቸውን የሚያረጋግጡ ስርአቶች ምንድናቸው?
- ☐ ሀይማኖትና መንግስት የተለያዩ ናቸው ሲባል ምን ማለት ነው?

☐ በኢትዮጵያ ተጠያቂነትንና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የተዘረጋው ህገመንግስታዊ ስርአት ምንድነው?

በዚህ ፅሑፍ የመጀመሪያው ክፍል ዲሞክራሲያዊ ስርአት ህዝብ ወኪሎቹን በመምረጥ እራሱን በራሱ የሚያስተዳደርበት ስርአተ መንግስት መሆኑን ተመልክተናል፡፡ በተለያዩ አገራት ያሉ የዲሞክራሲያዊ ስርአተ መንግስታት ከአገራቸው ልዩ ሁኔታ አንጻር አንዱን ከሌላው የሚለያቸው የራሳቸው ልዩ ባህርይ ቢኖራቸውም ሁሉም የዲሞክራሲያዊ ስርአተ መንግስታት የሚጋሩዋቸው መሰረታዊ ባህርያት ወይም መርሆዎች አሉ፡፡ እነዚህን መርሆዎች በሚመለከት የተለያዩ ምሁራን እንዲሁም የተለያዩ አገራት ህገመንግስቶች የየራሳቸው መስፈርቶችን በመጠቀም በተለያየ መልኩ እየከፋፈሉ ያስቀምጣሉ፡፡ ሁሉም ምሁራን ወይም ህገመንግስቶች የሚስማሙባቸው እኩል ስያሜና ቁጥር ያላቸው መርሆዎች የሉም፡፡ ይሁንና በአከፋፈል(classification) ይለያዩ እንጂ በሁሉም ሰነዶች ከሞላ ጎደል ሁሉም መሰረታዊ ባህርያት ወይም መርሆዎች የተካተቱ ናቸው፡፡ የኢፌዲሪ ህገመንግስትም ህገመንግስቱ የሚመራባቸውን መሰረታዊ መርሆዎች በምእራፍ ሁለት ደንግጎአል፡፡ በዚህ ክፍል እነዚህን መርሆዎች እንመለከታለን፡፡

### 1.4.1. <u>ሉአላዊነት</u>

A sovereign is the supreme lawmaking authority, subject to no other. ሉአላዊ ስልጣን ማለት የመጨረሻውና ከበላዩ የሚያዘው ሌላ ስልጣን የሌለው ስልጣን ሆኖ ለሌሎች ስልጣኖች ሁሉ መሰረት የሚሆን ማለት ነው፡፡ የህዝቦች ሉአላዊነት ማለትም በአንድ አገር ያሉ ህዝቦች የመጨረሻው የወሳኝነት ስልጣን ባለቤት ናቸው ማለት ነው፡፡ ሉአላዊነት በሁለት መልኩ ይገለፃል፡፡

### ውስጣዊ ሉአላዊነት (Internal Sovereignty)

ውስጣዊ ሉአላዊነት የአንድ አገር መንግስት በስልጣኑ ክልል በዜጎችና በሌሎች ላይ የሰፈነ የበላይነት ነው፡፡ ስለሆነም በአገሪቱ ዜጎች የሚተዳደሩበትን ህግ በማውጣት" በማሻሻል ይለገፃል፡፡

## ከሌሎች መንግስታት ጋር ባለው ግንኙነት ያለው ሉአላዊነት (External Sovereignty)

ይህ ከሌሎች መንግስታት ጋር ባለው ግንኙነት የሚገልፅ ነው፡፡ ይህም ማለት ከሌሎች መንግስታት ጋር ያለው ግንኙነት በእኩልነት ላይ የተመሰረተ እና ፍፁም ነፃነትን የሚመለከት ነው፡፡ አንድ መንግስት ሉአላዊ መንግስት ሲባል ከራሱ በላይ ሌላ ስልጣን ያለው መንግስት የለም ወይም ሊኖር አይችልም ማለት ነው፡፡ ሉአላዊነት በሌላ መልኩም ሊገለፅ ይችላል፡፡

1. <u>ህጋዊ ሉአላዊነት</u>፡-

ህጋዊ ሉአላዊነት በአንድ መንግስት መዋቅር ውስጥ የህግ አውጪው የሚኖረው የበላይነት ስልጣን ወይም የስልጣን የበላይነት ማለት ነው፡፡ ይህም በአንድ ዲሞክራሲያዊ ስርአተ መንግስት ህግ የማውጣት ስልጣን የተሰጠው አካል ነው፡፡ ስለሆነም የህግ አውጪ ምክር ቤት በአንድ መንግስት መዋቅር ውስጥ ህጋዊ ሉአላዊ አካል ነው ይባላል፡፡

2. <u>ፖለቲካዊ ሉአላዊነት</u>፡-

ፖለቲካዊ ሉአላዊነት የአንድ መንግስት ከፍተኛው የስልጣን ባለቤትነት ወይም የበላይነት ማለት ነው፡፡ ይህ ከፍተኛ የመንግስት ስልጣን ሌላ ሳይሆን መራጩ ህዝብ ማለት ነው፡፡ በሌላ አነጋገር ፖለቲካዊ ሉአላዊነት ማለት የህዝብ ሉአላዊነት ማለት ነው፡፡ የህዝብ ስልጣን በህግ ተደንግጎ የሚሰጥ ሳይሆን ከራሱ ከህዝብ ሉአላዊነት የሚመነጭ ነው፡፡

## <u>3. ሉአላዊነት በዲሞክራሲያዊ ስርአተ መንግስት</u>

የሁሉም ዲሞክራሲያዊ ስርአተ መንግስቶች አንዱ መሰረታዊ መለያ ባህርይ የሕዝብ/ሕዝቦች ሉአላዊነት የሚገለፅበት መሆኑ ነው፡፡

ሕዝቦች የራሳቸውን እድል በራሳቸው የሚወስኑበት" የሚያስተዳድሩዋቸውን ተወካዮቻቸውን የሚመርጡበት" ሲፈልጉ ደግሞ ከስልጣን የሚያወርዱበት ስርአት ከሌለ ህዝቡ የሉአላዊ ስልጣን ባለቤት ሳይሆን የሌሎች ሀይሎች ፍላጎት ማስፈፀሚያና

አገልጋይ ይሆናል ማለት ነው። የህዝብ/ህዝቦች ሉአላዊነት ባልተረጋገጠበት የትኛውም አገር ቢሆን ህዝቡን የሚያስተዳድረው መንግስት ማስተዳደር የሚችለው በሀይልና በጉልበት ነው። ህዝቡ ደግሞ በሀይልና በጉልበት የተጫነበትን አገዛዝ እንዲወገድለት መታገሉ አይቀርም።

ሕዝቦች ሰብአዊ መብታቸው እንዲከበርላቸው" ማህበራዊ "ፖለቲካዊና ባህላዊ መብቶቻቸውን እንዲከበሩላቸውና እንዲስፋፉላቸው ለዘመናት ሲታገሉ የቆዩ ለመሆኑ የታሪክ መዛግብት በስፋት አስፍረዋል። በዛሬው አለም በበርካታ አገሮች ተገንብተው የምናያቸው ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብት የተከበረባቸው ዲሞክራሲያዊ ሥርዓቶች እንዲሁ በገዢዎች ፍላጎትና ፈቃድ የመጡ ሳይሆን ህዝቦች ለመብታቸው መከበር ያደረጉት ትግል ውጤቶች ናቸው።

የኢትዮጵያ ህዝቦች የሉአላዊ ስልጣን ባለቤት ባልነበሩበት ወቅት ኢትዮጵያ ሰላም አጥታ"ልማቷ ተገትቶ የረሀብና የችግር አገር ሆና ቆይታለች። የኢትዮጵያ ህዝቦችም ለዲሞክራሲና ለዴሞክራሲያዊ ስርአት በተለያየ ደረጃና በተለያየ አኳኋን ታግለዋል"ከፍተኛ መስዋእትነትም ከፍለው በላያቸው ላይ የተጫነው ኢዲሞክራሲያዊ አገዛዝ አስወግደዋል።

የኢፌዲሪ ህገ መንግስት የኢትዮጵያ ሉአላዊ ስልጣን ባለቤት የኢትዮጵያ ብሄሮች"ብሄረሰቦችና ህዝቦች እንደሆኑ በግልፅ ደንግጎአል።

<u>ሕገ መንግስት አንቀፅ 8</u>

1. የኢትዮጵያ ብሄሮች "ብሄረሰቦች ህዝቦች የኢትዮጵያ ሉአላዊ ስልጣን ባለቤቶች ናቸው።
2. ይህ ህገ መንግስት የሉአላዊነታቸው መግለጫ ነው።
3. ሉአላዊነታቸውም የሚገለፀው በዚህ ሕገ መንግስት መሠረት በሚመርጧቸው ተወካዮቻቸውና በቀጥታ በሚያደርጉት ዲሞክራሲያዊ ተሳትፎ አማካይነት ይሆናል።

በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ1. በግልፅ እንደተደነገገው በኢትዮጵያ የሉአላዊ ስልጣን ባለቤቶች የኢትዮጵያ ብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች ናቸው፡፡ ይህ ማለት በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ ለመወሰን የመጨረሻ ስልጣን ያላቸው የኢትዮጵያ ህዝቦች ናቸው ማለት ነው፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝቦች የሉአላዊ ሥልጣን ባለቤትነት በምን ይገለጻል? በምን ይረጋገጣል?

## የህጎች ሁሉ የበላይ የሆነውን ህግ ማጽደቅ

ህገ መንግሥቱ በአንቀፅ ስምንት በንኡስ አንቀፅ 2 "ይህ ህገ መንግስት የሉአላዊነታቸው መግለጫ ነው" በማለት ደንግጎአል፡፡ የአንድ አገር ህዝብ የሉአላዊ ስልጣን ባለቤት መሆኑ ማረጋገጫ የሁሉም ሥልጣኖች ምንጭ በሆነው መሠረታዊ ጉዳይ ላይ ባለው የወሳኝነት ስልጣን ነው፡፡ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግሥት የህጎች ሁሉ የበላይ ህግ ነው፡፡ ስለሆነም ይህንን ህገ-መንግሥት የማጽደቅ ስልጣን ያለው የመጨረሻው የሥልጣን አካል ነው፡፡

> "ህገ-መንግሥት የሉአላዊነታቸው መግለጫ ነው፡፡" ሲል ምን ማለቱ ነው? ይህንን ህገ-መንግሥት የኢትዮጵያ ሕዝቦች ያጸደቁት ነው ማለቱ ነው፡፡ እርግጥ ነው ህገ-መንግሥቱ የፀደቀው በህገ-መንግሥት ጉባዔ ነው፡፡ የህገ-መንግሥት ጉባዔ አባላት በኢትዮጵያ ህዝብ ህገ-መንግሥቱን ተወያይተው እንዲያጸደቁ የተመረጡ ናቸው፡፡ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግሥት የፀደቀበት ሁኔታ ምን ያህል ህዝቡ የራሱን እድል በራሱ እንዲወስን ያደረገ ስለመሆኑ ቀደም ብለን በተማርነው የትምህርት ክፍል በዝርዝር ተመልክተነዋል፡፡ ስለሆነም የኢትዮጵያ ህዝቦች ህገ-መንግሥቱን ለዚህ ብለው በመረጡዋቸው ተወካዮቻቸው አማካይነት ያጸደቁት ስለሆነ ይህ ሕገ-መንግሥት የሉአላዊነታቸው መገለጫ ነው ማለት ነው፡፡

## በየጊዜው ተወካዮችን መምረጥ

ሕገ መንግስትን ማፅደቅ አንዱ የህዝብ ሉአላዊነት መገለጫ መሰረታዊ ጉዳይ ቢሆንም" ነገር ግን የሕዝብ ሉአላዊነት መገለጫ በዚህ ብቻ የሚያቆም አይደለም፡፡ ህዝቡ በወኪሎቹ አማካይነት ባፀደቀው ህገ መንግስት መሰረት የተቋቋመውን መንግስት የሚመሩ ወኪሎቹን በተወሰነ ጊዜ ነፃና ፍትሀዊ በሆነ መንገድ መምረጥ ሌላው የህዝብ

ሉአላዊነት መገለጫና ማረጋገጫ መንገድ ነው፡፡ ህዝቡ መንግስትን የሚመሩ ኃላፊዎችን ወይም መሪዎችን በነፃና ፍትሀዊ በሆነ መልኩ መምረጥን ባላረጋገጠ ስርአት የህዝብ ሉአላዊነት ተረጋግጧል ማለት አይቻልም፡፡ የህዝብ ሉአላዊነት ሊረጋገጥ የሚችለው መሪዎቹን/ወኪሎቹን በመምረጥ ብቻ ሳይሆን የመረጣቸውን መሪዎችን ማውረድና በሌላ መተካት ወይም መለወጥ ሲችልም ነው፡፡ ምርጫውም ለአንድ ጊዜ ብቻ ተደርጎ የሚያበቃ ሳይሆን በየተወሰነ ጊዜ ውስጥ ህዝቡ ፍላጎቱን እንዲገልፅ የሚያደርግ ስርአት ሲኖርም ነው፡፡ ይህም ስልጣን ላይ ያለው አካል ሁልጊዜ በስልጣን ላይ እንደማይቆይ ተገንዝቦ ስልጣኑን በአግባቡ እንዲጠቀም የሚያደርግ" በሌላ በኩል ደግሞ ህዝቡ የመረጠው መንግስት እንደጠበቀው ሆኖ ባያገኘው ሌላ ወገን እንዲመርጥ እድል የሚሰጥ ነው፡፡ ለዚህም ነው በህገ መንግስቱ ንኡስ አንቀፅ ሶስት "ሉአላዊነታቸውም የሚገልፀው በዚህ ህገ መንግስት መሰረት በሚመርጧቸው ተወካዮቻቸው አማካይነት ነው በሚል የተደነገገው፡፡ እንደሚታወቀው የኢፌዲሪ ህገ መንግስት ከፀደቀ በኋላ ለሶስት ጊዜ የህዝብ ተወካዮች ምርጫ ተደርጎአል፡ ምርጫ በእርግጥም የህዝቡን ሉአላዊነት እንዲያረጋግጥ መሟላት ያለባቸው መሰረታዊ ሁኔታዎች ማለትም ፍትሀዊ የሆነ የምርጫ ስርአት፣ ሁሉን የሚያሳትፍ የምርጫ መርሆ፣ ገለልተኛ የምርጫ አስፈጻሚ፣ ፍትሀዊ ምርጫ ለማድረግ እኩል የመወዳደሪያ መድረክ (ዴሞክራሲያዊ መብቶች)፣ በምርጫ ወቅት የሚነሱ ቅሬታዎች የሚፈቱበት ፍትሀዊ ስርአት ያስፈልጋሉ፡፡ ከዚህ በታች እነዚህን መሰረታዊ ጉዳዮች ከኢፌዲሪ ህገመንግስትና አግባብ ካላቸው ህጎች ጋር በማያያዝ እንመለከታለን፡፡

## 1. የምርጫ ሥርዓት

የህዝብ ሉአላዊነት መረጋገጡን ከሚወስኑት ጉዳዮች አንዱ የምርጫ ስርአት ነው፡፡ በዲሞክራሲያዊ ሥርዓቶች ሦስት ዓይነት የምርጫ ሥርዓቶች አሉ፡፡ እነርሱም፡- 1, የአብላጫ ድምጽ ሥርዓት፣ 2, የብዙሀን ድጋፍ ሥርዓት፣ 3, የተመጣጠነ የውክልና ሥርዓት ናቸው፡፡ ከዚህ በታች የእነዚህ የተለያዩ የምርጫ ስርአቶች ምንነትና ልዩነት በአጭሩ ቀርቧል፡፡

### ሀ. የአብላጭ ድምጽ ሥርዓት

በዚህ ሥርዓት ሂደት ለምሳሌ በአንድ ምርጫ ክልል ውስጥ ለአንድ የውክልና ቦታ አራት ሰዎች ቢወዳደሩ፣ እያንዳንዳቸው የተለያየ የድምጽ ድጋፍ ሊያገኙ ይችላሉ፡፡

ከመሀከላቸው አንደኛው ከፍ ባለ ድምጽ፣ ለምሳሌ ያህል ከሀምሳ በመቶ /50%/ በላይ የድምጽ ድጋፍ አግኝቶ ቢመረጥ ችግር የለም፡፡ ነገር ግን አራቱም ተወዳዳሪዎች ተመጣጣኝ የሆነ ድጋፍ፣ ለምሣሌ ያህል አንዱ 20% ሁለተኛው 23% ሶስተኛው 25% እና አራተኛው 21% የድጋፍ ድምጽ ቢያገኙ፣ የሚመረጠው 25% ያገኘው ይሆናል፡፡ በዚህም ምክንያት አንድ ወኪል አናሳ በሆነ የሕዝብ ድምጽ እንዲመረጥ ያደርገዋል፡፡

ይህ ሁኔታ በአብዛኛው የምርጫ ክልል የተንጸባረቀ እንደሆነ መንግሥት በአብዛኛው ሕዝብ የተደገፈ ያልሆነበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል፡፡ ከዲሞክራሲያዊነት አንጻር ሲታይ እንዲህ ዓይነት ውጤት የሥርዓቱ ደካማ ጐን ነው ማለት ይቻላል፡፡

የዚህ የምርጫ ሥርዓት ጠንካራ ጐን ነው ሊባል የሚችለው በየጊዜው የማይለዋወጥና የተረጋጋ መንግሥት እንዲቋቋም የሚረዳ መሆኑ ነው፡፡ እንዲሁም ደግሞ ለምርጫ አፈጻጸም ቀላልና አመቺ መሆኑና ብዙ ወጭ የማይጠይቅ ሥርዓት መሆኑ ነው፡፡ አብዛኛው ረዘም ያለ የዲሞክራሲ ልምድ ያላቸው እንደእንግሊዝ፣ አሜሪካ እና ካናዳ ያሉ አገሮች ምርጫ የሚያካሄዱት በዚህ ሥርዓት መሠረት ነው፡፡ ኢትዮጵያም የምትከተለው ይህንን ስርአት ነው፡፡ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 54(4) የምክር ቤቱ አባላት በአንድ የምርጫ ክልል ውስጥ ከሌሎች ተወዳዳሪዎች መካከል አብላጫ ድምጽ ያገኘ ተወዳዳሪ አሸናፊ በሚሆንበት የምርጫ ስርአት ይመረጣሉ ይላል፡፡

ለ. <u>የብዙሃኑ ድጋፍ ሥርዓት</u>

በዚህ ሥርዓት ለምሳሌ በአንድ የምርጫ ክልል ውስጥ አራት ተወዳዳሪዎች ቢኖሩ አሸናፊ ሆኖ የሚመረጠው ከሃምሣ በመቶ በላይ የሆነውን የሕዝብ ድምጽ ድጋፍ ያገኘው ነው፡፡ ይህ እንዲሆን በመጀመሪያው ምርጫ ከአራቱ ተወዳዳሪዎች መካከል አንዱ ሃምሣ በመቶ ድምጽ ካላገኘ፣ አንዱ ተወዳዳሪ ሃምሣ በመቶ የድምጽ ብልጫ እንዲያገኝ ሁለተኛ ዙር ምርጫ ይካሄዳል፡፡ ይህን የምርጫ ሥርዓት የሚከተሉ አገሮች አብዛኛዎቹ በሁለተኛው ዙር በተወዳዳሪነት እንዲቀርቡ የሚያደርጓቸው በመጀመሪያው ዙር በድምጽ ብልጫ አንደኛና ሁለተኛ የወጡትን ተወዳዳሪዎች ነው፡፡

ይህ የምርጫ ሥርዓት አብዛኛውን የሕዝብ ድጋፍ ያገኘው ተወዳዳሪ እንዲመረጥ ማድረጉ ጠንካራ ጐኑ ሲሆን፣ ደካማ ጐኑ ደግሞ ከሁለተኛው ዙር ውድድር የወጡት

ተወዳዳሪዎች፣ድጋፋቸውን ለአንዱ ወይም ለሌላው የቀሩት ተወዳዳሪዎች ለመስጠት ሰፋ ያለ የፓርቲ ድርድር በር ስለሚከፍት፣በመጨረሻ የሚመረጠው ሰው የራሱን ወይም የፓርቲውን ኘሮግራም ለማስፈጸም በቂ የመራጮች ድጋፍ የሌለው መሆኑ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት በዚህ የምርጫ ሥርዓት የራሱን ኘሮግራም ለማስፈጸም ከበቂ ውክልና የመነጨ ሥልጣን ያለው መንግሥት እንዳይፈጠር ሊያደርግ ይችላል፡፡

ሐ.<u>የተመጣጠነ የውክልና ሥርዓት</u>

ይህ የምርጫ ሥርዓት በግላቸው ወይም ፓርቲዎችን በመወከል ግለሰቦች ቀርበው የሚወዳደሩበት ሥርዓት አይደለም፡፡ ተወዳዳሪዎቹ ፓርቲዎች ናቸው፡፡ እያንዳንዱ ፓርቲ በምርጫ ውድድር ባገኘው የሕዝብ ድምጽ መጠን ውክልና ያገኛል፣ ከምርጫ በኋላ ወኪሎቹን ፓርቲው ይሰይማል፡፡

በዲሞክራሲ መርሆ መሠረት በአንድ በኩል ሁሉም ምርጫ ውስጥ የተሳተፈ ሕዝብ እንዲወከል በማድረጉ የሕዝቡን ውክልና በአጠቃላይ እንዲሟላ ሲያደርግ፣ በሌላ በኩል ደግሞ መራጩ ተወዳዳሪዎቹን አውቆ እንዲመርጣቸው የሚያደርግ አይደለም፡፡ እንዲሁም ተወካዮቹን ከሕዝብ ጋር የሚያቀራርቧቸው ሁኔታዎች አይፈጥርም፡፡

ይህ የምርጫ ሥርዓት የአብዛኛው ሕዝብ ድጋፍ ያለው መንግሥት እንዲመረጥ የሚረዳ አይደለም፡፡ አብዛኛውን ጊዜ የሚያመራው፣ አነስተኛ ድጋፍ ያላቸው ፓርቲዎች በጥምር መንግሥት እንዲያቋቁሙ ወደማድረግ ነው፡፡ ከዚህ የተነሣ በዚህ መንገድ የተቋቋመ መንግሥት የአንድን የአነስተኛ ክፍል ድጋፍ ካላገኘ ከሥልጣን ሊወርድ ይችላል፡፡ ስለዚህ አነስተኛ ፓርቲዎች፣ ሕዝብ በምርጫ ከሰጣቸው ድጋፍ በላይ መንግሥት እንዲቋቋም ወይም ከሥልጣን እንዲወርድ የማድረግ ከፍተኛ ኃይል ይሰጣቸዋል፡፡

## <u>2. የምርጫ መርሆዎች</u>

ሕዝቦች በየጊዜው በሚያደርጉት ምርጫ በእርግጥም የህዝቦች ፈቃድ ተገልጾ ሉአላዊነታቸው ለማረጋገጥ የምርጫው ስርአት ሊያሟላቸው የሚገቡ መሰረታዊ

መርሆዎች አሉ። ምርጫ በትክክልም የህዝቡን ሉአላዊነት ማረጋገጫ እንዲሆን 1/ ሁሉአቀፍ 2/ እኩልነት 3/ ርቱእ 4/ ሚስጢራዊ ድምፅ መስጠትን ያረጋገጠ መሆን አለበት።

1. <u>ሁሉ አቀፍ (Universal)</u>

ሁሉ አቀፍ ማለት ዜጎች <u>በብሄር ብሄረሰብ</u> ቋንቋ ሃይማኖት ወይም ሌላ ማህበራዊ ምክንያት ሳይኖር ሁሉም ዜጎች መምረጥና መመረጥ መቻላቸውን የሚያረጋገጥ ነው። ስለሆነም ሁሉ አቀፍ የምርጫ መብት በህገ መንግስት ወይም በምርጫ ህግ የሚመለከቱ መመዘኛዎችን የሚያሟሉ ሁሉ በምርጫ የሚካፈሉበት የምርጫ ስርአት ማለት ነው። የወል ሆነው የሚታወቁት የመምረጥና የመመረጥ መመዘኛዎች የሚከተሉት ናቸው።

1. የመምረጥ የመመረጥ መብት ባለቤት ለመሆን ዝቅተኛ ዕድሜን ማሟላት
2. የአእምሮ ጤንነትና
3. በህግ መብትን አለመገፈፍ ናቸው።

በእነዚህ መመዘኛዎች ያለፈ ሁሉ መምረጥም መመረጥም ይችላል። በኢትዮጵያ ከ1967 በፊት በነበረው የምርጫ ሥርዓት አንድ ሰው በእጩነት ለመቅረብ በሚመረጥበት አውራጃ ግምቱ ከብር 1000 የማያንስ የማይንቀሳቀስ ንብረት ወይም ከብር 2000 የማያንስ የሚንቀሳቀስ ንብረት ሊኖር ይገባ ነበር። የኢፌዲሪ የምርጫ ህግ አዋጅ ቁጥር አንቀፅ 20(2) ማንኛውም ሰው በህግ ያልተገደበ የመምረጥም ሆነ የመመረጥ መብት እንደአለው ደንግጎአል። ለመምረጥ የሚያስፈልገው መስፈርትም

1. አስራ ስምንት አመት የሞላው፣
2. የአእምሮ በሽታ የሌለበት፣
3. በፍርድ የእስራት ቅጣት ያልተወሰነበት"ወይም ቅጣቱን ጨርሶ የወጣ መሆን ብቻ ናቸው።

ለዕጩነት የሚያበቁ መስፈርቶችም በምርጫ ህጉ አንቀፅ 38 እንደተመለከተው

1. ኢትዮጵያዊ የሆነ
2. የሚወዳደርበትን ብሄራዊ ክልል ቋንቋ የሚያውቅ
3. በምዝገባው እለት እድሜው ሃያ አንድና ከዚያ በላይ የሆነ
4. በምርጫ ክልል በመደበኛነት ቢያንስ ሁለት ዓመት የኖረ

5. የፓርቲ አባል መሆን ወይም የፓርቲ አባል ካልሆነ ከ 1000 ያላነሰ ድጋፍ ያለው መሆን ይበቃል፡፡

አንድ ተመራጭ ምን ያህል ሰው ይወክላል የሚለውን ለመመለስም በምርጫ ህጉ አንቀፅ 15(2) የምክር ቤቱን ወንበሮች 550 ለኢትዮጵያ ህዝብ በማካፈል የሚገኘውን ማእከላዊ ግምት መሰረት ባደረገ መልኩ እንደሚሆን ደንግጎአል፡፡ ይሁንና አናሳ ብሄረሰቦች ውክልና እንዲኖራቸው ወኪላቸውን የሚመርጡበትን ሁኔታ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንደሚወስን በምርጫ ህጉ አንቀጽ 15(3) ደንግጎአል፡፡

2. <u>እኩል የምርጫ መብት መርህ(Equal)</u>

አንድን የህዝብ ተወካይ ለመምረጥ አንድ ሰው አንድ ድምፅ ብቻ ሊኖረው ሲችል እኩል የምርጫ መብት አለ ማለት ነው፡፡ ይህ ማለት የአንድ ሀብታም ወይም የአንድ ሚኒስትር ድምፅ ከአንድ የጥበቃ ሰራተኛ ድምፅ እኩል ነው ማለት ነው፡፡ ይህ አሁን የቀረ ቢሆንም ለምሳሌ በቤልጅየም ከ 1921 በፊት 25 አመት እድሜ የሞላው ዜጋ አንድ ድምፅ ሲኖረው 35 ዓመት የሞላው የቤተሰብ ኃላፊ እንደዚሁም የማይንቀሳቀስ ንብረት ያላቸው ወይም ከፍተኛ ግብር የሚከፍሉ ሰዎች ከአንድ ድምፅ በላይ ይኖራቸው ነበር፡፡ አንዳንድ ጊዜ የተወሰኑ ሰዎች ከአንድ የምርጫ ጣቢያ በላይ ድምፅ የመስጠት መብት ይኖራቸዋል፡፡ በእንግሊዝ እስከ 1948 ድረስ ይህ አይነት ስርአት ይሰራበት ነበር፡፡ የኢፌድሪ የምርጫ ህግ አንቀፅ 14(4) ምርጫን በሚመለከት የመራጮች ድምፅ እኩል መሆኑን ደንግጎአል፡፡ በኢፌዲሪ የምርጫ ህግ አንቀፅ 56(2) እያንዳንዱ መራጭ ድምፅ መስጠት የሚችለው አንድ ጊዜ ብቻ እንደሆነ ደንግጎአል፡፡

3. <u>ርቱእ(direct suffrage)</u>

አንድ መራጭ ማንኛውም አይነት ጣልቃ ገብነት ሳይኖር ምርጫው በሚከናወንበት ቦታ በመገኘት የሚፈልገውን ተወካይ ለመምረጥ የሚችልበት ስርአት ርቱእ የምርጫ ስርአት ይባላል፡፡

4. <u>ሚስጢራዊ(secret vote)</u>

ሚስጢራዊ የመምረጥ ስርአት መራጩ ማንም ሳያውቅበት እንዲመርጥ የሚያረጋግጥ ስርአት ነው፡፡ በዚህ መሰረት ማን ማንን እንደመረጠ ከራሱ በስተቀር ለሶስተኛ ሰው ሚስጥር ነው፡፡ ይህ አብዛኛውን ጊዜ በዝግ ቦታ ድምፅ የሚሰጥበት ስርአት ነው፡፡ ከዚህ ውጭ ያለው እጅን በማንሳት የሚደረግ ምርጫ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ማን ማንን

እንደመረጠ ስለሚታወቅ ተፅእኖ አለው፡፡ በሚስጥር የመምረጥ ዘዴ መራጩ ከፍርሃት ነፃ በሆነ መልኩ የመምረጥ መብቱን እንዲጠቀምበት ያደርጋል፡፡ በኢፌዲሪ የምርጫ ህግ አንቀፅ 14(1) የምርጫ አሰጣጥ በሚስጥር እንደሚሰጥ ይደነግጋል፡፡

## 3. ነጻ ምርጫ አስፈፃሚ

ነፃና ፍትሀዊ ምርጫ ለማድረግ ምርጫው ከተወዳዳሪዎች ተፅእኖ ነፃ በሆነ መልኩ እንዲከናወን ነጻ የምርጫ አስፈፃሚ መኖሩ አስፈላጊ ነው፡፡ ዲሞክራሲያዊ ምርጫ ለማድረግ ኃላፊነት የሚሰጠው አካል ከየትኛውም ተወዳዳሪ ተፅእኖ ነፃ ሆኖ በገለልተኝነት የሚያስመርጥ መሆን አለበት፡፡ በኢትዮጵያ ምርጫ የማድረግ ኃላፊነት የተሰጠው ለብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ነው፡፡

በኢፌዲሪ ህገ መንግስት በአንቀፅ 102 ስለምርጫ ቦርድ የሚከተለው ተደንግጎ ይገኛል፡፡

1. በፌዴራልና በክልል የምርጫ ክልሎች ነፃና ትክክለኛ ምርጫ በገለልተኝነት እንዲያካሄድ ከማንኛውም ተፅእኖ ነፃ የሆነ ብሄራዊ የምርጫ ቦርድ ይቋቋማል፡፡
2. የቦርዱ አባላት በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሾማሉ፡፡ ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል ይላል፡፡

ይህንን መሰረት አድርጎም የምርጫ ህግ አዋጅ ቁጥር 111/87 የወጣ ሲሆን ይህም በአዋጅ ቁጥር 438/97 ተሻሽሎ ነበር፡፡ እነዚህ ሁለቱም የምርጫ አዋጆች በተሻሻለው የኢትዩጵያ ምርጫ ህግ አዋጅ ቁጥር 532/1999ዓ.ም ተሻሽለዋል፡፡ በህጉ መሰረትም ተጠሪነቱ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሆነ ከማንኛውም ተፅዕኖ ነፃ የሆነና ራሱን የቻለ የምርጫ አስፈፃሚ አካል ተቋቁሟል፡፡ የምርጫ ቦርድ አባላት የሥራ ጊዜያቸው አምስት ዓመት ሆኖ ከሁለት ጊዜ በላይ እንደማይመረጡም ተደንግጎአል፡፡ የምርጫ ቦርዱ በብሔራዊ ደረጃ፣ በክልል ደረጃና ከክልል በታች ጽ/ቤቶች እንደሚኖሩት በአዋጁ ተመልክቷል፡፡

## የምርጫ ቦርድ ሥልጣንና ተግባር

### 7.የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፣

1/ በሕገመንግስቱ እና በዚህ አዋጅ መሠረት የሚካሄድ ማናቸውንም ምርጫ እና ህዝበ ውሳኔ በገለልተኝነት የማስፈጸም፣

2/ በየደረጃውእ እና በየጊዜው የሚካሄዱ ምርጫዎች ነፃና ፍትሃዊ በሆነ መንገድ የሚካሄዱበትን ሁኔታ እና ማረጋገጥ፣

3/ ምርጫን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ሰነዶችና ቁሳቁሶች የማዘጋጀትና የማሰራጨት፣

4/ ምርጫን አስመልክቶ ለሕዝቡ የሲቪክ ትምህርት በስፋት የመስጠት እና ትምህርት ለሚሰጡ አካላት ፈቃድ የመስጠት፣የመከታተልና የመቆጣጠር፣

5/.ለምርጫ ታዛቢዎች ፈቃድ የመስጠት፣የመከታተልና የመቆጣጠር፣

6/. የፖለቲካ ድርጅቶችን የመመዝገብ፣ ፈቃድ የመስጠት፣በህጉ መሠረት የመከታተልና የመቆጣጠር፣

7/. በየእርከኑ ለሚካሄዱ ምርጫዎች አፈፃፀም የሚያስፈልጉ የምርጫ አስፈፃሚ ጽህፈት ቤቶችን የሙያ ብቃት ባለው ገለልተኛ የሰው ሃይል በቋሚነት፣በጊዜያዊነት ወይም በኮንትራት የማደራጀት ከሌሎች ተቋማት በትውስት በመውሰድ የማሰማራት እንዲሁም የምርጫ አስፈጻሚዎችን የማሰልጠን፣

1. በየጊዜው የሚደረጉትን ምርጫዎች አፈጻጸምና የምርጫ ህጎች የመገምገም፣ጥናት የማካሄድ፣ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን የመሰብሰብ እና የማጠናቀር ማሻሻያ የሚያስፈላጋቸውን ጉዳዮች ለይቶ ለሚመለከተው አካል የማቅረብ፣እንዲሁም ማናቸውንም የምርጫ ሰነዶች በአግባቡ እንዲያዙ የማድረግ፣
2. የፖለቲካ ድርጅቶችን የጋራ መድረክ የማደራጀትና የማስተባበር፣

   ለምርጫ አፈጻጸም የሚያስፈልገውን ገለልተኛ የሰው ኃይል የማደራጀትና የማሠልጠን፣
3. በምርጫ ሂደት የተፈጸመ የህግ መጣስ፣የማጭበርበር፣ወይም የሰላምና ፀጥታ ማደፍረስ ድርጊት በስፋት በዓይነቱ የምርጫውን ውጤት እንደሚያዛንፍ ከተወዳዳሪ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ከግል እጩዎች፣ከታዛቢዎች፣ከምርጫ አስፈፃሚዎች ወይም ከሌላ ከማንኛውም ምንጭ መረጃ ደርሶት ተጨባጭነቱን በራሱ ማጣራት ሲያረጋግጥ ወይም ተፈፅሟል ብሎ ሲያምን ሁኔታውን የመመርመር፣ውጤቱን የመሰረዝና አዲስ ምርጫ እንዲካሄድ ወይም ድርጊቱ እንዲቆም የማዘዝ፣ጥፋተኞች በህግ እንዲጠየቁ የማድረግ፣
4. በምርጫ ሂደት ለተከሰቱ አለመግባባቶች አስተዳደራዊ መፍትሄ የመስጠት፣የምርጫ ጉድለቶችን የማረምና ለሚቀርቡ ቅሬታዎች ውሳኔ የመስጠት፣

5. የምርጫ ውጤቶችን የማረጋገጥና በይፋ የማሳወቅ፣
6. በጀት አዘጋጅቶ የማቅረብና ሲፈቀድም በስራ ላይ የማዋል፣
7. እንደአስፈላጊነቱ ከመንግስትና መንግስታዊ ካላሆኑ አካላት የምርጫ አስፈፃሚዎችን በመመልመልና በመመደብ የማንቀሳቀስ፣
8. የምርጫ አስፈፃሚዎችን በርጫ ስራቸው ምክንያት ሊደርስባቸው ከሚችል ተፅዕኖ መከላከል፣በምርጫ ስራ በመሳተፋቸው መብትና ጥቅማቸው እንዳይጓደል መጠበቅና መከላከል፣
9. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር በየደረጃው የሚካሄዱ ምርጫዎች የጊዜ ሰሌዳ የማውጣት፣የማሻሻል፣የመለወጥ በወቅቱ ለሕዝብ ይፋ የማድረግ፣
10. ስለሥራው እንቅስቃሴ በየጊዜው ለተወካዮች ምክር ቤት በየጊዜው ሪፖርት የማቅረብ፣
11. በየደረጃው የሞገኙ የቦርድ ጽህፈት ቤት ኃላፊዎች ሠራተኞችን የስራ አፈፃፀም የመቆጣጠር፣የመከታተል አስፈላጊ እርምጃም የመውሰድ፣
12. ምርጫውን ግልፅ፣ ነፃና ፍትሃዊ ለማድረግ የሚረዳ ደንብ ወይም መመሪያ የማውጣት፣
13. የጽህፈት ቤቱ ኃላፊ ሥራውን መከናወን ሳይችል ሲቀርና ውክልና መስጠት በማይቻልበት ጊዜ ሌላ ኃላፊ እስከሚሾም ቦርዱ ከምክትል ዋና ኃላፊዎች አንዱን በውክልና እንዲሠራ የማድግ፣
14. በውጭ አገር ያሉ ኢትዮጵያውያን በምርጫ የሚሳተፉበትን ሁኔታ አጥንቶ ለሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት የማቅረብ፣
15. በሕገመንግስቱ አንቀጽ 61 ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት የክልል ምክርቤት የፌዴሬሽን ምክርቤት አባላትን በቀጥታ ከሕዝብ እንዲመረጡ ሲወሰን ምርጫ የማካሄድ፣
16. ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያግዙ ተመሳሳይ ተግባራትን የማከናወን።

## 19. የቦርዱ <u>የክልል ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ተግባርና ኃላፊነት</u>

እያንዳንዱ **የቦርዱ የክልል ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት** ከዚህ በታች የተዘረዘረው ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል።

1. ቦርዱ በሚያወጣው ደንብና መመሪያ መሠረት በክልል ደረጃ የሚካሄደውን ምርጫ ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፣

2. በሥሩ የሚቋቋሙትን የምርጫ ጽሕፈት ቤቶች ስለሚደራጁበት ሁኔታ ለቦርዱ ጽህፈት ቤት ሀሳብ ያቀርባል፣
3. ለምርጫ የሚያስፈልጉ ሰነዶችና ቁሳቁሶች ለሚመለከታቸው የምርጫ ጽሕፈት ቤቶች በወቅቱ መድረሳቸውን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣
4. ቦርዱ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር የስነዜጋና የመራጮች የትምህርት ይሰጣላ፣ያስተባብራል፣
5. የመራጮች አመዘጋገብ፣ የእጩዎች አቀራረብና የደምጽ አሰጣጥ ሥርዓት ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት የተካሄደ መሆኑን የከታተላል፣ይቆጣጠራል፣
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /5/ በተጠቀሱ ጉዳዮች ላይ የሚነሱተን ቅሬታዎችና ተቃውሞዎች በክልል ደረጃ እየመረመረ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይወስናል።
7. የክልሉን የምርጫ ሂደትና ውጤት በሚመለከት ለቦርዱ ጽሕፈት ቤት ሪፖርት ያቀርባል፣
8. ለምርጫ አፈጻጸም በሚያመች መልኩ አግባብ ያላቸውን መረጃዎች እየሰበሰበና እያጠና በየጊዜው ለቦርዱ ጽሕፈት ቤት ሪፖርት ያቀርባል፣
9. ለምርጫ አፈጻጸም በሚያመች መልኩ አግባብ ያላቸውን መረጃዎች እየሰበሰበና እያጠና በየጊዜው ለቦርዱ ጽህፈት ቤት ሪፖርት ያቀርባል፣
10. ስለሥራ እንቅስቃሰው በየወቅቱ ለቦርዱ ጽ/ቤት ሪፖርት ያቀርባል፣
11. ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት በክልል፣በምርጫ ክልል እና በምርጫ ጣቢያ ደረጃ የፖለቲካ ድርጅቶች የጋራ መድረክ እንዲዋቀር ያደርጋል፣በክልል የሚቋቋመው የፖለቲካ ድርጅት የጋራ መድረክ ሰብሳቢ በመሆን ያገለግላል፣
12. የክልሉ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይቋቋማል፣
13. ቦርዱ የሚመደብለትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

21. የምርጫ ክልል ሥልጣንና ተግባር፣

እያንዳንዱ የምርጫ ክልል የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

1. ቦርዱ በሚያወጣው ጊዜ ሠሌዳ መሠረት፡-

ሀ/የምርጫ ቁሳቁሶችን ለምርጫ ጣቢያዎች ያሰራጫል፣

ለ/ዕጩዎችን ይመዘግባል፣መስፈርቱን ላሟሉ ዕጩዎች የመታወቂያ ካርድ ይሰጣል፣

2. ከምርጫ ጣቢያዎች የሚመጡ ሠነዶችና የምርጫ ቁሳቁሶች በአግባቡ ተሟልተው መምጣታቸውን ያረጋግጣል፣ይረከባል፣በጥንቃቄ እንዲያዙ ያደርጋል፡፡
3. .ምርጫ ጣቢያዎች ተግባራቸውን በአግባቡ ማከናወናቸውን ይቆጣጠራል፣
4. በሕግ መሠረት ለሚቀርቡ ቅሬታዎችና አቤቱታዎች ውሳኔ ይሰጣል፣
5. ከምርጫ ጣቢያ የመጡ የምርጫ ውጤቶችን በማዳመር አሸናፊዎችን ከለየ በኃላ ውጤቱን ለህዝብ ይፋ በማድረግ አስፈላጊ ቅጾችን በመሙላት ለቦርዱ ይልካል፡፡
6. ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የተመራጭነት መታወቂያ ካርድ ለአሸናፊዎች ይሰጣል፣
7. የዕጩወኪሎችን ዝርዝር ለምርጫ ጣቢያዎች ያስተላልፋል፣
8. ምርጫ ክልሉን የሕዝብ ታዛቢዎች ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ያስመርጣል፣
9. የፖለቲ ድርጅቶች የጋራ መድረክ ለያደራጅ ይችላል፣
10. ከቦርዱ ወይም ከክልሉ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

## 4. <u>መሠረታዊ መብቶችን ማረጋገጥ</u>

በዲሞክራሲያዊ ስርአት ምርጫ ነጻና የህዝብ ሉአላዊነትን እንዲያረጋግጥ መሰረታዊ የህዝቦች መብቶች መከበር አለባቸው፡፡ ከእነዚህም መካከል ሀሳብን በነጻ የመያዝና የመግለጽ መብትና የመደራጀት መብት፣ ምርጫን የመታዘብ መብት የሚካተቱ ናቸው፡፡

### 1. <u>ሀሳብን በነጻ የመያዝና የመግለጽ መብት</u>

ሕዝቡ ተወካዮቹን ሊመርጥ የሚችለው ለዚህ ኃላፊነት ይሆናሉ የሚላቸውን በማወዳደር ነው፡፡ ከእነዚህ ተወዳዳሪዎች መካከል ለመምረጥ ደግሞ አንዱ ከሌላው በምን እንደሚሻል፣ የሕዝቡን ፍላጎት የሚወክለው ማን እንደሆነ ማወቅ አለበት፡፡ አንዱ ከሌላው በምን እንደሚሻል ለማወቅ ደግሞ ሀሳብን የመግለጽ ነጻነት ሊኖር የግድ ነው፡፡ ሃሳብን የመግለጽ መብት ከተከበረ የተለያዩ ለመመረጥ የሚፈልጉ ሰዎች ሃሳባቸውን መግለጽ ይችላሉ፡፡ በዚህ አማካይነትም ሕዝቡ ከቀረቡት ሃሳቦች ውስጥ የሚሻለው ይሄ ነው ብሎ ለመምረጥ ይችላል ማለት ነው፡፡ በዚህም አማካይነት አብዛኛው ሰው የመረጠው ሰው ሥልጣን ይይዛል ማለት ነው፡፡ ከዚህ

በተጨማሪ ሃሳብን የመግለጽ መብት መኖሩ መንግሥት በሥራው የሚታየውን ድክመት እና ስህተት በመጠቆም አካሄዱን እንዲያስተካክል ዜጐች እንዲችሉ የሚያደርግ ሥርዓት ነው፡፡ ሃሳብን የመግለጽ መብት የሚገለጽባቸው መንገዶች በንግግር በስብሰባዎች ላይ በጋዜጦች ላይ በሬድዮና ቴሌቭዥን በመሳሰሉት መንገዶች ነው፡፡ የኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት የአመለካከትና ሃሳብን በነጻ የመግለጽ መብት በአንቀጽ 29 አረጋግጧል፡፡

የምርጫ ሕግ ሃሳብን ከመግለጽ መብት ጋር በተያያዘ የምርጫ ህጉ የመንግሥት የመገናኛ ብዙሀንን እና የመንግሥት አካላትን ኃላፊነት በግልጽ አስቀምጦአል፡፡

59.<u>ስለመገናኛ ብዙሃን አጠቃቀም</u>

1. በመንግሥት ቁጥጥር ስር ያሉትን መገናኛ ብዙሃን ማለትም ሬዲዮን፣ ቴሌቭዥንና ጋዜጦችን የእጩዎች ደጋፊ የሆኑት የፖለቲካ ድርጅቶችና የሕብረተሰብ ክፍሎች ያለ አድልዎ ለመጠቀም መብት ይኖራቸዋል፡፡
2. እጩዎች በመገናኛ ብዙሃን ነፃ የአየር ጊዜ አግኝተው የመጠቀም መብት ይኖራቸዋል፡፡
3. የአጠቃቀሙ ሥርዓት የማስታወቂያ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይሆናል፡፡ድልድሉም ተወዳዳሪ የፖለቲካ ድርጅቶች እንዲያውቁት እና አስተያየት እንዲሰቁበት ይደረጋል፡፡
4. የመገናኛ ብዙሃንና ጋዜጦች የምርጫ አዘጋገብ ስነምግባር ቦርዱ በሚያወጣው ደንብ መሰረት ይወሰናል፡፡

60.<u>የመንግሥት አካላት ግዴታ</u>

በማናቸውም ደረጃ የሚገኙት የመንግሥት አካላትና ኃላፊዎች የምርጫ ውድድር እንቅስቃሴ በቂጡ እንዲሳካ ለማድረግ በየኃላፊነታቸው ስር የሚገኙትን ሬዲዮ ጣቢያዎች፣ የስብሰባ አዳራሾች፣ ጋዜጦችና የመሳሰሉትን እጩዎችና ደጋፊዎቻቸው ያለ አድልዎ ለመጠቀም የሚያስችላቸው ሁኔታ የማመቻቸት ግዴታ አለባቸው፡፡

የምርጫ ቅስቀሳ ሀሳብን የመግለጽ መብት አንዱ ቢሆንም፣ ሀሣቡን በመግለጽ መብት ስም የወንጀል ድርጊት፣ ማለትም የሌላውን ሰው ህጋዊ መብት የሚጎዳ፣ ወይም ህግና ሥርዓትን የሚቃረን የወንጀል ድርጊት ሊፈጸምም ይችላል፡፡ በተለይም ዲሞክራሲ

በመገንባት ላይ ባሉ አገሮች ሃሳብን የመግለጽ መብት ለወንጀል ሥራ ከማነሳሳት ተግባር ለይቶ ማስቀመጥ አስቸጋሪ ነው፡፡ በሌላ በኩል የምርጫ ቅስቀሳው እንዳይደናቀፍና፣ የሕዝብ ዲሞክራሲያዊ መብቶች በተሟላ መልኩ እንዲገለጽ ማድረግም ያስፈልጋል፡፡ ይህንን በሚመለከት በምርጫ ሕጉ የሚከተለው ተደንግጎ ይገኛል፡፡

<u>የእጩዎች ልዩ መብት</u>

አንቀጽ 57(1) እጩዎች ከባድ የወንጀል ድርጊት ፈጽመው ካልሆነ ወይም ከባድ ወንጀል ሲፈጽሙ እጅ ከፍንጅ ካልተያዙ በስተቀር ምርጫው እስከሚጠናቀቅ ድረስ አይያዙም፡፡

አንቀጽ 57(2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ከተጠቀሰው በተለየ ሁኔታ እጩዎች ሕገ ወጥ ድርጊት የፈጸሙ እንደሆነ ሕጋዊ እርምጃ የሚወሰድባቸው የምርጫው ውጤት በቦርዱ አማካይነት በይፋ ለሕዝብ ከተገለጸ በኂላ ብቻ ይሆናል፡፡

አንቀጽ 57(2 ከላይ በንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው ቢኖርም አሸናፍው ሰው በምርጫ ወቅት በፈፀመው ወንጀል የሚጠየቀው በሚመለከተው ምክር ቤት የህግ ከለላው ሲነሳ ነው፡፡

2. <u>የመደራጀት መብት (የመድበለ ፓርቲ ስርአት)</u>

ሃሳብን የመግለጽ መብት በተሟላ መልኩ ውጤታማ ሊሆን የሚችለው የመሰብሰብና የመደራጀት መብት ከተፈቀደ ብቻ ነው፡፡ ሃሳብን የመግለጽ መብት አንዱ ግቡ ተመሣሣይ ሃሳብ የሚያስቡ ሰዎች በተፈጠረው መብት አማካይነት ተዋውቀው የሚደግፉትን ሃሳብ ሥራ ለይ ለማዋል፣ ተሰባስበው ውጤት እንዲያመጡ ማድረግ ነው፡፡ ሃሳብ ሥራ ላይ እንዲውል ሥራ ላይ የሚያውለው ሰው ያስፈልገዋል፡፡ ለዚህ ደግሞ መሰባሰብ መደራጀት ያስፈልጋል፡፡

በዛሬው ውስብስብ በሆነው ዓለም የመንግሥትን ሥልጣን ለመያዝ በተደራጀ መልኩ የፖሊሲ አማራጮችን ማቅረብና መወዳደር ያስፈልጋል፡፡ በዛሬው ዲሞክራሲያዊ ዓለም ሥልጣን ለመያዝ የሚቻለው በተደራጀ መልኩ በሚደረግ የምርጫ ውድድር ብቻ ነው፡፡ ስለሆነም በየትኛውም ዲሞክራሲያዊ ሥርዓተ መንግሥት ፓርቲዎች ይኖራሉ፡፡ ፖለቲካ ፓርቲዎች በፈቃደኝነት የተመሠረቱ እና ሕዝቡ የመንግሥትን ሥልጣን በመያዝ ሉአላዊነቱን የሚያረጋግጥባቸው መሣሪያዎች ናቸው፡፡ በምርጫ ውድድሩ የአብዛኛውን ድጋፍ ያገኘው/ያገኙት ፓርቲ/ዎች ፖሊሲና ኘሮግራማቸውን ሲያስፈጽሙ ተሸናፊ

ወይም የአናሳውን ድጋፍ ያለው ፓርቲ ደግሞ የመንግሥትን ፖሊሲ አፈጻጸም በመተቸት አማራጭ ፖሊሲዎችን ያቀርባሉ፡፡

ፖለቲካ ፓርቲዎች ሕዝቡ ተመራጮችን ተጠያቂ ለማድረግ የሚጠቅሙ መሣሪያዎችም ናቸው፡፡ ሕዝቡ የሚመርጠው የፓርቲውን ፕሮግራምና ፖሊሲ በመሆኑ ተመራጩ የፓርቲውን ፕሮግራም ተግባራዊ የማያደርግ ከሆነ ፓርቲው ሥልጣኑን እንዲለቅ ወይም ደግሞ በድጋሚ በሚደረግ ምርጫ ስለማይመርጡት ፓርቲው ተመራጮች የገቡትን ቃል እንዲፈጽሙ ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት ነው፡፡ ዲሞክራሲያዊ የሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች በምርጫ ተሸንፈው ሥልጣን ባይዙም የተመረጠውን መንግሥት፣ የሚያወጣቸውን ሕጎች ያከብራሉ፡፡ ልዩነትም በውይይትና በሰላማዊ መንገድ ብቻ መፈታት እንዳለበት ያምናሉ፡፡ ለዲሞክራሲያዊ ስርዓቱ ታማኝ የሆነ ተቃዋሚ ፓርቲ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት በአንቀጽ 31 ማንኛውም ሰው ለማንኛውም ዓላማ በማኀበር የመደራጀት መብት እንዳለው ደንግጓል፡፡ እንዲሁም በአንቀጽ 56 በምክር ቤቱ አብላጫ መቀመጫ ያገኘ የፖለቲካ ድርጅት ወይም ጣምራ ድርጅቶች የፌዴራሉን መንግሥት የሕግ አስፈጻሚ አካል ያደራጃል ይመራል በማለት ደንግጓል፡፡

የፖለቲካ ድርጅቶች የሚመዘገቡበት፣ የሚሰረዙበት ወዘተ ሥርዓቶች በተሻሻለው በፖለቲካ ፖርቲዎች ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 573/2000 ላይ ተመልክቷል፡፡

<u>የፖለቲካ ፓርቲ ምንነት</u>

እንቀጽ 2(2) የፖለቲካ ፓርቲ ወይም “የፖለቲካ ድርጅት” ከሕብረተሰቡ ውስጥ የተወሰኑ ሰዎችን በማሰባሰብ የራሱን የፖለቲካ እምነትና ዓላማ የሚያንጸባርቅበት ኘሮግራም በማውጣት በሀገር አቀፍ ወይም በክልል የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ ተሳትፎ በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት የፖለቲካ ሥልጣን ለመያዝ በዚህ አዋጅ መሠረት የተመዘገበ ማኀበራዊ ተቋም ነው፡፡

የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባን በሚመለከት በሕጉ የሚከተለው ይገኛል፡፡

<u>አንቀጽ 4. የፖለቲካ ፓርቲ ስለመመሥረት</u>

ዳኛ፣መከላከያ እና የፖሊስ ሠራዊት አባል ያልሆኑ ፣ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በላይ የሆኑ ኢትዮጵያዊ በመሥራች አባልነት ተሰብስበው የመተዳደሪያ ደንብና የፖለቲካ

ኘሮግራም በማውጣት የሀገር አቀፍ ወይም የክልል የፖለቲካ ፓርቲ አባል የመሆን መብት አለው፡፡

<u>አንቀጽ 5. አንድ የሀገር አቀፍ የፖለቲካ ፓርቲ ስለመመስረት</u>

1) አንድ የፖለቲ ፓርቲ በሀገር አቀፍ የፖለቲካ ፓርቲነት የሚመሠረተው፣

ሀ. 1500 መሥራች አባላት ሲኖሩት፣

ለ. ከእነዚህ መሥራች አባላት ውስጥ አርባ ከመቶ የማይበልጡት /40/ የአንድ ክልል መደበኛ ነዋሪዎች ሲሆኑና፣

ሐ. የተቀሩት መሥራች አባላት ነዋሪነታቸው በኢትዮጵያ ከሚገኙት ክልሎች ውስጥ ቢያንስ በአራቱ ክልሎች መደበኛ ነዋሪዎች ሲሆኑና

መ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /ሐ/ መሠረት በየክልሉ ለአገር አቀፍ ፓርቲ መሥራችነት ከሚመዘገቡት አባላት በእያንዳንዱ ክልል አሥራ አምስት በመቶ እጅ /15/ ሲሆኑ ነው፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሱት መስራች አባላት ድምፅ ለመስጠት መብት ያላቸው ሆነው፣የፖለቲካ ፓርቲው አባል ለመሆናቸው ስምምነታቸውን በፊርማቸው የገለፁ መሆን አለባቸው፡፡

3) ከላይ በንዑስ 2 መሠረት መስራች አባላት የፈረሙበት ሰነድ ለሕዝብ ይፋ የሚሆን ሰነድ ነው፡፡

የዚህ አንቀጽ አላማው ሕዝብን እወክላለው የሚል አንድ ፓርቲ ከአንድ አከባቢ ተሰባስበው ፍላጎታቸውን በሌላው ላይ የሚጫኑ ሳሆን ቢያንስ የተወሰኑ የአገርቱን አከባቢ ፍላጎቶችን የሚያማክል እንዲሆን ለማስቻል እና ሕዝብ ሳይወክላቸው ሕፃንና የሞቱ ሰዎችን ዝርዝር በማሳየት አባል አለን በሚል ሊፈፀም የሚችለውን የማጭበርበር ተግባር ለመቆጣጠር ነው፡፡

5. <u>የክልል የፖለቲካ ፓርቲ ስለመመስረት</u>

1. አንድ የፖለቲካ ፓርቲ የክልል የፖለቲካ ፓርቲነት የሚመሠረተው፣

ሀ. 750 መሥራች አባላት ሲኖሩት፣

ለ. ከእነዚህ መሥራች አባላት ውስጥ ከስልሳ በመቶ /60/ በላይ የሆኑት የአንድ ክልል መደበኛ ነዋሪዎች ሲሆኑ ነው፡፡

የፖለቲካ ፓርቲው አባል ለመሆናቸው ስምምነታቸውን በፊራማቸው የገለፁ መሆን አለባቸው፡፡ የፊረሙበት ሰነድም ለህዝብ ይፋ መሆን አለበት፡፡በዚህ መልኩ የተቋቋመ የፖለቲካ ፓርቲ መመዝገብ ይኖርበታል፡፡ ካልተመዘገበ መሥራት አይችልም፡፡ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በፖለቲካ ፓርቲነት ለመንቀሳቀስ የሚችለው በዚህ አዋጅ መሠረት በቦርዱ ተመዝግቦ የሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሲያገኝ ነው፡፡ ይህን ቅድመ ሁኔታ ሲሟላ ብቻ ነው መብትም ሆነ ግዴታ የሚኖርበት፡፡

<u>አንቀጽ51. የፖለቲካ ፓርቲው የገንዘብ ምንጭ፡</u>

ከአባላቱ የሚሰበሰብ የአባልነት መዋጮ እና በኢትዮጵያዊያን ግለሰቦች እና ኩባንያዎች ሚደረግ ስጦታ ወይም እርዳታ እና ከመንግስት የሚሰጥ ድጋፍና እርዳታ ሲሆን በተጨማሪ ዝግጅቶችን በማደራጀት ገንዘብ ለማሰባሰብ ይችላል፡፡በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ንግድና ኢንዱስትሪ ስራዎች መስራት አይችልም፡፡ ሂሳብ ወጪና ገቢ መዘገብ የመያዝና በውጪም ሆነ በውስጥ ኦዲተሮች ህሳቡን የማስመርመር ግዴታ አለበት፡፡

ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ከውጭ አገር ዜጎች፣ ከውጪ አገር መንግስት ወይም ከውጪ አገር የፖለቲካ ድርጅቶች፣በጎ አድራጊ ድርጅቶች፣ከሃይማኖት ድርጅቶች፣ ከፍርድ እስረኞች ከህገ-መንግስቱ ውጪ ስልጣን ለመያዝ ከተደራጀ ቡድን ወይም፣ ከሽብርተኛ ድርጅት፣ምንጩ ያልታወቀ ስጦታ ወይም እርዳታ፣ከመንግስታዊ ድርጅት፣ ህገ ወጥ ጥቅም ወደፊት ለማስገኘት ወይም ለማግኘት በማሰብ የሚሰጥ እርዳታ ወይም ስጦታ መቀበልን አዋጁ አጥብቆ ይከለክላል፡፡

ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በዚህ አዋጅ ከተፈቀደለት ውጭ ገንዘብ፣ ወይም ማናቸውንም ንብረት፣በስጦታ፣በዳረጎት፣በውርስ፣በንግድና ኢዱስትሪ ሥራ ወይም በማናቸውም መንገድ ተቀብሎ ቢገኝ አግባብ ባለው ሕግ መጠየቁ እንደተጠበቀ ሆኖ ንብረቱ በፍርድ ቤት ውሳኔ ለመንግስት ገቢ እንደሚሆን ተደንግጓል፡፡

1. <u>ምርጫን የመታዘብ መብት</u>

ምርጫ በሚደረግበት ጊዜ በእርግጥም በፍትሃዊነት መደረጉን ለማረጋገጥ ተወዳዳሪ ፓርቲዎች እንዲሁም ሌሎች ወገኖች የሚታዘቡበት ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር የኢፌዲሪ የምርጫ ሕግ የሚከተሉት ድንጋጌዎች አሉት፡፡

## አንቀጽ78. ስለምርጫ ታዛቢዎች

(1) የምርጫውን ሂደት ለመታዘብ የሚፈልጉ የአገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢዎች ከቦርዱ በሚሰጥ ፈቃድ ምርጫውን ለመታዘብ ይችላሉ፡፡

(2) አገርቱ የተቀበለቻቸው ስምምነቶች እንደተጠበቁ ሆነው መንግስት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የውጭ ምርጫ ታዛቢዎችን ሊጋብዝ ይችላል፡፡

## አንቀጽ79 ስለፈቃድ አሰጣጥ

(1) ቦርዱ የምርጫ የታዛቢነት ፈቃድ ጥያቄ ሲቀርብለት ጥያቄውን ያቀረበው ድርጅት

ሀ/ በሕጋዊ መንገድ ፈቃድ አውጥቶ የሚንቀሳቀስ የአገር በቀል ድርጅት መሆኑን፣

ለ/ ከማንኛውም የፖለቲካ ወገንተኝነት የፀዳ መሆኑን፣

ሐ/ለምርጫ ፍትሃዊነት ነፃነትና ሰላማዊነት ምቹ ሁኔታ የሚፍጥር ዝግጅት ማድረጉን፣

መ/ድርጅቱ የሚያሰማራቸውን ግለሰቦች ምርጫውን በገለልተኝነት ለመታዘብ ችሎታ ያላቸው መሆኑን በማጣራትና በቦርዱ የተዘጋጀውን የምርጫ ታዛቢዎች የስነምግባር ደንብ ወይም መመሪያ መቀበላቸውን ድርጅቱንና ወኪሎቹን በማስፈረም የታዛቢት ፈቃድና መታወቂያ ካርድ ሊሰጥ ይችላል፡፡

2/ቦርዱ ከላይ በንዑስ ቁጥር 1 የተደነገገው ባለመሟላቱ ፈቃድ የከለከለ እንደሆነ ይህንኑ ለአመልካቹ በፅሁፍ ያሳውቃል፡፡

3/ ማንኛውም የምርጫ ታዛቢ ከስነ፣ምግባር ደንቡና ከገባው ግዴታ ውጭ ሲንቀሳቀስ ከተገኘ ቦርዱ እንደሁኔታው ለግለሰቡም ሆነ ለወከለው ድርጅት ማስጠንቀቂያ በመስጠት ስህተቱን እንዲያርም ለማድረግ ወይም ፈቃድን እስከመሰረዝ የሚደርስ እርምጃ ሊወስድ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 80 የታዛቢዎች መብት

1/ የምርጫ የታዛቢነት ፈቃድ የተሰጠው የድርጅት ወኪል በምርጫ ጣቢያ በመዘዋወር የምርጫውን ሂደት የመከታተልና ተገቢ መረጃ ጠይቆ የማግኘት መብት አለው፡፡

2/ የምርጫ ታዛቢዎች የምርጫውን ሂደት በሚመለከት የታዘባቸውን ወይም ያጋጠሟቸውን ጉድለቶች ለቦርዱ ጽህፈት ቤት ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡

## አንቀጽ 81 የታዛቢዎች ግዴታ

(1) ማንኛውም ፈቃድ ያገኘ የምርጫ ታዛቢ፡

ሀ/ የታዛቢነት መታወቂያውን መያዝና ማሳየት፣

ለ/የምርጫ አስፈፃሚዎች የሚሰጡትን መመሪያ ማክበር አለበት፣

ሐ/የምርጫው ሂደት በትክክልና በብቃት እናዳይካሄድ ከሚያደርግ ማናቸውም ተግባር መቆጠብ አለበት፣

መ/ቦርዱ ያወጣውን የስነ-ምግባር ደንብ ማክበር አለበት፣

ሠ/ የምርጫ ታዛቢው የምርጫው ውጤት በይፋ ከመገለጹ በፊት በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጭ ሆኖ ስለምርጫው አስተያየቱን መስጠት የተከለከለ ነው፡፡

ረ/ዝርዝር ሪፖርት አዘጋጅቶ ለቦርዱ የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

3/ከላይ በንኡስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የውጭ የምርጫ ታዛቢ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት በለልተኝነት ልዩ ልዩ ጅጎችን በማክበር የምርጫውን ሂደት መታዘብ ይችላል፡፡

ምርጫ ጣቢያ መራጬ ሕዝብ ነይፋ በሚደረግለት ጥሪ መሰረት በሚያደርገው ስብሰባ የሚመረጡ የምርጫ ጣቢያ ታዛቢዎች ስለሚታዘቡበትም ሁኔታ በአዋጁ አንቀጽ 82 ተደንግጓል፡፡

## 4. ምርጫን በተመለከተ የሚነሱ ቅሬታዎች የሚፈቱበት ስርዓት

በምርጫ ቅስቀሳ ጊዜ፣በድምጽ መስጫ እለት እንዲሁም ድምጽ ቆጠራንና ማሳወቅን በሚመለከት በተወዳዳሪ ፓርቲዎች ቅሬታ ሊኖር ይችላል፡፡ በተወዳዳሪ ፓርቲዎች የሚነሱ ቅሬታዎች የሚፈቱበት ስርአትም ለምርጫው ፍትሀዊነትና ነጻ መሆን አስፈላጊና መሰረታዊ ነው፡፡

በምርጫ ህጉ ውስጥ ቅሬታ ስለሚፈታበት ሁኔታ ድንጋጌዎች አሉ፡፡ በምርጫ ጣቢያዎች አስተዳደራዊ ውሳኔ የሚሰጡ የአቤቱታ ሰሚ ኮሚቴዎች እንደሚኖሩ እንዲሁም በወረዳና ከወረዳ በላይ በሚገኙ ጽ/ቤቶችም አንድ የአቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ እንደሚኖር ተደንግጎአል፡፡

በምርጫ አዋጁ አንቀጽ 93 እንደተመለከተው በመራጭነት ከመመዝገብ የሚያግድ ሁኔታ ያጋጠመው ሰው በሃያ አራት ሰዓት ውስጥ አቤቱታውን ለምርጫ ጣቢያው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ማቅረብና ማስወሰን ይችላል፡፡ በመራጭነት ከመመዝገብ ለማሳገድ የሚቀርብ አቤቱታ መቅረብ የሚችለው የመራጮች የምዝገባ ጊዜ ሰሌዳ እስከሚጠናቀቅበት ጊዜ ይሆናል፡፡ የአቤቱታ ሰሚ ኮሚቴው በሃያ አራት ሰዓት ውስጥ

ውሳኔ ካልሰጠ በአቤቱታ አቅራቢው ጥያቄ እንደተስማማ ይቆጠራል፡፡ የምርጫ ጣቢያው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ በ24 ሰዓት ውስጥ ውሳኔ ካልሰጠ አቤቱታ አቅራቢው ለምርጫ ክልል ፅህፈት ቤት አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ በ48 ሰዓት ውስጥ ይግባኝ የማቅረብ መብት አለው፡፡ የምርጫ ክልል ስአቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ የቀረበለትን ይግባኝ መርምሮ በ24 ሰዓት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡ የምርጫ ክልል ስአቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ የቀረበው ይግባኝ ለመራጭነት ከመመዝገብ የተከለከለ ሲሆንና በ24 ሰዓት ውስጥ ውሳኔ ካልሰጠ በይግባኝ አቅራቢው ጥያቄ እንደተስማማ ተቀጥሮ ምዝገባው ይከናወናል ማለት ነው፡፡ በመራጭነት መመዝገብ የሌለበት ያለአግባብ ተመዝግቦአል ተብሎ የሚቀርብ አቤቱታ ከመራጮች የምዝገባ ቀን ጀምሮ የመራጮች መዝገብ ይፋ የሚሆንበት ጊዜ እስከሚያልቅ ድረስ ይሆናል፡፡ ለምርጫ ክልሉ አቤቱ ሰሚ ኮሚቴ የቀረበው ይግባኝ የተመዘገበን መራጭ ለመቃወም ሲሆን እና  በ24 ሰዓት ውስጥ ውሳኔ ካልሰጠ ይግባኝ ባዩ በ24 ሰአት ውስጥ ለወረዳው ፍርድቤት ይግባኝ የማቅረብ መብት አለው፡፡የወረዳው ፍርድቤት የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

በአዋጁ አንቀጽ 94 እንደተመለከተው በእጩነት ለመመዝገብ የታገደ ማንኛውም ሰው ወይም የፖለቲካ ድርጅት በእጩነት ከመመዝገብ የሚያግድ ሁኔታ ሲያጋጥም ለምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ አቤቱታውን አቅርቦ መልስ የማግኘት መብት አለው፡፡ በ24 ሰዓት ውሳኔ ካልተሰጠ በአበቱታ አቅራቢው ጥያቄ እንደተስማማ ይቆጠራል፡፡ ይሁንና የምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ በ24 ሰዓት ውስጥ ውሳኔ ከሰጠ አቤቱታ አቅራቢው በ72 ሰዓት ውስጥ ለክልሉ ቅርንጫፍ ፅህፈት ቤት አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ይግባኝ ለማቅረብ ይችላል፡፡ ለክልሉ ቅርንጫፍ ፅህፈት ቤት አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴም በ48 ሰዓት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ ውሳኔ ካልተሰጠ በይግባኝ አቅራቢው ጥያቄ እንደተስማማ ይቆጠርና ምዝባው ይካሄዳል፡፡ ነገር ግን ለክልሉ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ የቀረበው  ይግባኝ የአንድን እጩ ምዝገባ በመቃወም ሲሆን እና በ48 ሰዓት ውስጥ ውሳኔ ካልሰጠ ይግባኝ ባዩ 48 ሰዓት ውስጥ ለክልኩ  ጠቅላይ ፍርድ ቤት  ይግባኝ የማቅረብ መብት አለው፡፡ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ በ48 ሰዓት ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡ በተመሳሳይ መንገድ የዞን ወይም የክልል አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ በ48 ሰዓት ውስጥ ውሳኔ ካልሰጠ ውሳኔውን እንዳጻናው ይቆጠራል፡፡

ግለሰቡ ቅሬታ ከአለው ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል። ፍርድቤቱ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል።

በአዋጁ አንቀጽ 95 እንደተመለከተው **በድምጽ አሰጣጥ ሂደት** ድምጽ ከመስጠት የታገደ ሰው በአምስት ሰዓት ውስጥ አቤቱታውን ለምርጫ ጣቢያ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ማቅረብ አለበት። የምርጫ ጣቢያ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴም ጊዜያዊ ድምጽ እንዲሰጥ በማድረግ ጉዳዩን ወደ ምርጫ ክልሉ ጽህፈት ቤት በመላክ ውሳኔ እንዲያገኝ ማድረግ ወይም ጊዜያዊ ድምፅ መስጠት የለበትም ብሎ ሊወስን ይችላል። ጊዜያዊ ድምፅ እንዲሰጥ ባደረገ ጊዜ የምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ከየአቤቱታ ሰሚው በ5 ሰዓት ውስጥ ውሳኔ ካልሰጠ በጥያቄው እንደተስማማ ይቆጠራል። የምርጫ ጣቢያ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ በተወሰነው ጊዜ ውስጥሚቴ ወይም የወረዳ ፍርድቤት የመምረጥ መብት እንዳለው የሚገልፅ ውሳኔ የድምፅ መዳመሩ ከመጠናቀቁ በፊት ካልደረሰ የሰጠው ጊዜያዊ ድምፅ ውድቅ ይደረጋል። በምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ጊዜያዊ ድምፅ ከመስጠት የተከለከለ ሰው ወዲያውኑ ይግባኙን ለወረዳው ፍርድቤት ማቅረብ ይችለል። የወረዳ ፍርድቤት የድምፅ መስጫው ሰዓት ከመጠናቀቁ በፊት የሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል። ሰሚ ኮሚቴ በ24 ሰዓት ውስጥ ውሳኔ ካልሰጠ የምርጫ ጣቢያ ኮሚቴውን ውሳኔ እንዳጸና ይቆጠራል። ግለሰቡ በወረዳው ምርጫ ኮሚቴ ውሳኔ ካልተስማማ ለወረዳ ፍርድ ቤት ይግባኝ ለማቅረብ ይችላል።

በአዋጁ አንቀጽ 96 እንደተመለከተው **በድምጽ ቆጠራ ላይ ቅሬታ** ያለው ሰው ቅረታውን ለምርጫ ጣቢያው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ አስመዝግቦ ይህንኑ ቅረታ በ48 ሰዓት ውስኝ ለምርጫ ክልል አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ሊያቀርብ ይችላል።የምርጫ ክልል አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ የቀረበለትን አቤቱታ መርምሮ በ5 ቀን ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል። በዚህ ውሳኔ ቅር የተሰኘ አቤቱታ አቅራቢ ውሳኔ በተሰጠ በ5 ቀን ውስጥ ይግባኝ ለቦርዱ ያቀርባል። ቦርዱም የቀረበውን ይግባኝ መርምሮ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል። ይግባኝ ባዩ ቦርዱ የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም በ5 ቀን ውስጥ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል። ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድቤትም ለቀረበለት ይግባኝ በተቻለ ፍጥነት ይወስናል።

እንዲሁም በአዋጁ አንቀጽ 97 እስከ 100 ድረስ ባለው በኢፌዲሪ የወንጀል ህግ በሕዝባዊ ምርጫ እና በድምፅ አሰጣጥ ላይ የሚፈፀሙ የወንጀል ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በተጨማሪነት በዚህ ምዕራፍ የተከለከሉ ተግባራትን መፈፀም ወነጀልን የቋቁማሉ፡፡
ማንናውን ሰው ወይም ድርጅት ከቦርዱ ፈቃድ ወጭ ማንኛውንም የምርጫ ሰነድና ቁሳቁስ ያተመ፣ያባዛ፣የፈበረከ ወይም ይህን የመሰለ ህገ ወጥ የምርጫ ሰነድ እና ቁሳቁስ የዞ የተገኘ ወይም ያደለ እንደሆነ ከእጩ ተወዳዳሪዎች ወይም እጩዎችን ካቀረበ ፓርቲ በቀረበለት አቤቱታ መሰረት በምርጫው ሂደት ድርጊቱ ለመፈጸሙ በቂ መረጃ ከተገኘ በእስራት ወይም በገንዘብ መቀጮ ያስቀጣል፡፡
ምርጫ ከተጀመረበት አንስቶ ውጤት እስከሚገለጽበት ቀን ድረስ የማንኛውም እጩ ተወዳዳሪ ፖስተርን ወይም የምርጫ ማስታወቂያን ያበላሸ ያስወገደ ወይም የቀደደ እንደሆነ ከአንድ ዓመት ባልበለጠ እስራት ወይም መቀጮ ይቀጣል፡፡ድርግቱን ወንጀል የሚያሰኘው ምርጫ ሂደት ከተጀመረበት (commencement of election process) ውጤቱ እስከሚታወቅበት ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ድርግቱ ተፈጽሞ ሲገኝ እስከ እንዲቆም፣ የምርምጫውብቻ ነው፡፡ ምርጫው አብቅቱ ውጤቱ ሲገለጽ ቢዘገይና በዚህ ጊዜ ውስጥ ፖስተርን ወይም የምርጫ ማስታወቂያን ያበላሸ ያስወገደ ወይም የቀደደ ጥፋተኛ ሊባልአይገባም፡፡ በመቀጠልም በአንቀጽ 100 በምርጫው ዕለት የምርጫ ውጤት ትንበያ መረጃ በማዘጋጀት ያሰራጨ ወይም እንዲአጋጅ ደረገ ወይም በማናቸውም መንገድ ለህዝብ የገለፀ ማናቸውም ሰው ከአንድ ዓመት ባልበለጠ እስራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል፡፡

### 2.3.3. <u>ቀጥተኛ ዲሞክራሲያዊ ተሳትፎ</u>

ሕገመንግሥቱ ያስቀመጠው ሌላው የሉዓላዊነት መገለጫ ሕዝቡ በቀጥታ የሚያደርገው ዲሞክራሲያዊ ተሳትፎ እንደሆነ ነው፡፡ ይህም ማለት ሥልጣንን ወደታች በማውረድ ሕዝቡ በቅርቡ በሚገኘው የወረዳና የቀበሌ መስተዳድር በቀጥታ የራሱን ጉዳይ እንዲወስን ማድረግ ማለት ነው፡፡ /ስለሕዝቡ ቀጥተኛ ዲሞራክሲያዊ ተሳትፎ በዝርዝር በሚቀጥለው ርእስ የሚቀርብ ይሆናል/

## 2.3.4. የመወያያ ጥያቄዎች

1. ሉዓላዊነትን በሚመለከት በኢትዮጵያ የነበሩት የተለያዩ ሕገመንግሥት ያሰፈሩት እንደሚከተለው ነው፡፡

   የኃይለሥላሴ ሕገመንግሥት አንቀጽ 1 ሉዓላዊነትን ሲገልጽ እንደሚከተለው ነው፡፡" የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገሥት መንግሥት ግዛት በኢትዮጵያ ዘውድ ሙሉ ገዥነት ሥር የሚገኙት አገሮች ሁሉና ባህሮችም ደሴቶቹም ጭምር ነው፡፡ ሙሉ ገዥነቱና አገሮቹ የማይነጣጠሉ ናቸው፡፡ አገሮቹና የገዥነት መብቶቹም ለባእድ የማይተላለፉ ናቸው፡፡" ሉዓላዋነት በዚህ ሰነድ " ሙሉ ገዥነት" በሚል መልኩ የቀረበ ነው፡፡

   የደርግ ሕገመንግሥት አንቀጽ 1/2/

   የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ደሴቶቹንም ጨምሮ የየብስ የአየርና የባህር ግዛቱ የማይነጣጠልና የማይደፈር ሉአላዊ መንግሥት ነው"

   አንቀጽ 3 /1/ በኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ስልጣን የሰርቶ አደሩ ሕዝብ ነው፡፡

   በእነዚህ የተለያዩ ሕገመንግሥቶች ላይ እንደተመለከተው ሉአላዊነት የተገለጸው ከግዛትና ከድንበር አንጻር ነው፡፡ የኢፌዲሪ ሕገመንግሥት ደግሞ ሉአላዊነትን ከግዛትና ድንበር አንጻር ሳይሆን ከሕዘቦች መብት ጋር በማያያዝ የቀረበ ነው፡፡ ትክክለኛው የሉዓላዊነት መገለጫ የትኛው ነው?

2. ደርግ በሕገመንግሥቱ ስልጣን የሰርቶ አደሩ ነው የሚል ድንጋጌ ነበረው፡፡ ይሁንና በደርግ ጊዜ ስልጣን የሰርቶ አደሩ አልነበረም፡፡ የኢፌዲሪ ሕገመንግሥት ስልጣን የሕዝቡ ነው ይላል፡፡ በእርግጥ ስልጣን የሕዝቡ ለመሆኑ ማረጋገጫው ምንድነው?
3. ሕዝብ የሉዓላዊ ስልጣን ባለቤት የሚሆነው ለምንድነው? የሕዝብ ሉአላዊነት የሚመነጨው ከምንድነው? የመንግሥት ስልጣን የያዙ ሰዎች ሕዝብ ሉአላዊ ነው በማለተቸው ነው? ሕዝብ የሉአላዊ ስልጣን ባለቤት ላይሆን ይችላል ወይ?
4. ኢትዮጵያ በምርጫ ስርአት የአብላጫ ድምጽ ስርዓትን መከተሏ ተገቢ ነው ወይ? ሌሎች የምርጫ ስርአቶች በኢትዮጵያ ተግባራዊ ቢሆኑ ምን ጠቀሜታ? ምን ጉዳት አለው?
5. ዜጎች በአንድ አገር ቢኖሩም በስርአቱ ሁሉም እኩል ተጠቃሚ ሁሉም እኩል ተጎጂ አይደሉም፡፡ ሀብትና ንብረት ያለው በስርአቱ በከፍተኛ ደረጃ ተጠቃሚም ሆነ ተጎጂ

ሊሆን ይችላል። ስለሆነም ሁሉም እኩል ተጠቃሚና ተጎጂ ባልሆነበት ሁኔታ ለሁሉም እኩል ድምጽ እንዲኖረው ማድረግ ተገቢ ነው ወይ?

6. በህገመንግስቱ አንቀጽ 9(2) ማንኛውም ዜጋ የመንግስት አካላት የፖለቲካ ድርጅቶች ሌሎች ማህበራት እንዲሁም ባለስልጣኖቻቸው ህገመንግስቱን የማስከበርና ለህገመንግስቱ ተገዢ የመሆን ሀላፊነት አለባቸው ይላል። በምርጫ ቅስቀሳ ወቅት ህገመንግስቱ የህዝብ ሳይሆን በህዝቡ ላይ በጉልበት የተጫነ ነው ብሎ መቀስቀስ ይህንን ድንጋጌ መጣስ አይደለም ወይ? በምርጫ ህጉ በምርጫ ቅስቀሳ ወቅት ከባድ ወንጀል እንደሚያሲዝ ደንግጎአል። ህገመንግስቱ የህዝብ አይደለም ብሎ መቀስቀስ ከባድ ወንጀል ነው ወይ? ከባድ ወንጀል ምንድነው?
7. የምርጫ ውጤትን አለመቀበል መብት ነው ወይስ ሕግን መጣስ?
8. በምርጫ ውድድር የታዛቢዎች ሚና ምንድነው?
9. በምርጫ ህጉ አንቀጽ 52 መሰረት የምርጫ ቦርድ በራሱ አነሳሽነት የምርጫው ህግ መጣሱን የሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ እንደሚሰጥ ተመልክቶአል።

አንቀጽ. 52 ህገወጥ ድርጊትን ስለማስቆም

1. ቦርዱ በራሱ ክትትል ወይም ከእጩ ተወዳዳሪዎች ወይም እጩዎችን ካቀረበ ፓርቲ በቀረበለት አቤቱታ መሰረት በምርጫው ሂደት አዋጁን የሚጥስ ድርጊት ለመፈጸሙ በቂ መረጃ ካገኘ ድርጊቱ እንዲቆም ትእዛዝ ለመስጠት ይችላል።
2. ቦርዱ ማንኛውም አዋጁን የሚጥስ ተግባር በስፋቱና በአይነቱ የምርጫውን ውጤት እንደሚወስን በራሱ ክትትል ወይም ከተወዳዳሪዎች ወይም ተወዳዳሪዎችን ካቀረበ ፓርቲ በቂ መረጃ ካገኘ የምርጫውን ሂደት ለማቆም፣ ወይም የምርጫውን ውጤት ውድቅ ለማድረግና እንደገና ምርጫ እንዲካሄድ ለማዘዝ ይችላል።
3. በዚህ አንቀጽ መሰረት ቦርዱ በሚሰጣቸው ትእዛዞች ላይ ማንኛውም ወገን ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል። ነገር ግን የቦርዱ ትእዛዞች ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት እስከአልታገዱ ወይም እስከአልተሻሩ ድረስ የጸኑ ይሆናሉ።

ተወዳዳሪ ፓርቲ አቤቱታ የሚቀርብበትን የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ ቆጠራው ተጭበርብሮአል ብሎ በሚያቀርበው አቤቱታ መሰረት የምርጫ ቦርድ በዚህ አንቀጽ መሰረት አቤቱታውን ተቀብሎ አቤቱታውን ውድቅ ያደርገዋል። የምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት አቤቱታውን ውድቅ ያደረገው ውሳኔ ይግባኝ ሊቀርብበት የሚችል ነው ወይ?

በአንድ በኩል ምርጫ ቦርድ የሚሰጠው ውሳኔ ይግባኝ እንደሚቀርብበት ስለተደነገገ ይግባኝ ሊቀርብ ይችላል የሚል ክርክር ሊቀርብ ይችላል፡፡ በሌላ በኩል ግን ምርጫ ቦርድ ቅሬታ ማቅረቢያ ጊዜው ካለፈ በኋላ የሚቀርብን አቤቱታ የመቀበል ግዴታ የለበትም፡፡ ስለሆነም ጊዜው አልፎአል አልቀበልም በማለቱ ይግባኝ የሚቀርብ አይመስልም፡፡ ይግባኝ ማቅረብ የሚቻል ከሆነ ግን ቅሬታ የሚቀርብበትን የጊዜ ገደብ ማስቀመጥ አያስፈልግም፡፡ ነገር ግን ቦርዱ አቤቱታውን ተቀብሎ የምርጫውን ውጤት የሚቀይረው ከሆነ በጊዜ ገደቡ ምክንያት መብቱን ያረጋገጠውን ተወዳዳሪ መብት የሚነካ ስለሆነ ይግባኝ መቅረቡ ተገቢ ነው፡፡ ነገር ግን ምርጫ ቦርድ በራሱ ዲስክሬሽን አቤቱታውን መርምሮ ምርጫው ችግር የለውም ብሎ አቤቱታውን ባይቀበለው ይግባኝ ለፍርድ ቤት ሊቀርብ አይገባም የሚል ክርክር ይቀርባል፡፡ በአንቀጹ ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 መሰረት ምርጫ ቦርድ የሚሰጠው ውሳኔ ምን እንደሆነ ተመልክቶአል፡፡ ምንም ህገወጥ ነገር አልተፈጸመም በማለት የሚሰጠው ውሳኔ በእነዚህ ድንጋጌዎች ውስጥ የሚወድቅ አይደለም፡፡ ስለሆነም ይግባኝ ሊቀርብ አይችልም የሚል ክርክር ይቀርባል፡፡ የትኛው ክርክር ጠንካራ ነው?

### 1.4.2. ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች

1. የዜጎች መብቶችና ዴሞክራሲያዊ ስርአት የማይነጣጠሉ ናቸው፡፡

የሰብዓዊ መብቶች መነሻና ግብ ዜጎችን ከመንግሥት ሥልጣን abuse መጠበቅ ነው፡፡ ከታሪክ እንደምንገነዘበው ለዲሞክራሲያዊ ስርአቶች ምስረታ የተደረገው ትግል የሰዎች መብቶች እንዲታወቁና እንዲከበሩ ከተደረገው ትግል ጋር የተያያዘ ነው፡፡

በዓለም ላይ የሕዝቦች ሉዓላዊነት የተረጋገጠባቸው ዲሞክራሲያዊ ስርዓተ መንግሥታት የተመሠረቱት በገዥዎች ፈቃድ ሳይሆን ሕዝቦች የራሳቸውን እድል በራሳቸው ለመወሰን ስለሆነም ለመብቶቻቸው መከበር ባደረጉት ትግል ነው፡፡

በሕግ ካልሆነ በስተቀር ያለመታሰር፣ የእምነት መብት ወዘተ በእንግሊዝ አገር ዲሞክራሲያዊ ስርዓተ መንግሥት ከመመስረቱ በፊት በከባድ ትግል ዕውቅና ያገኙ መብቶች ናቸው፡፡ ይሁንና እነዚህና ሌሎች የሰው ልጆች መብቶች ዋስትና ሊያገኙ የሚችሉት የመብቱ ተጠቃሚ የሆኑት እራሳቸው ሰዎች የሥልጣን ባለቤት ሲሆኑ

ነው። ሕዝቦች የሉዓላዊ ሥልጣን ባለቤት ባልሆኑበት የሰዎች ሰብዓዊ መብቶች ዋስትና ሊያገኙ አይችሉም።

የዛሬዋን አሜሪካ የመሰረቱት መስራች አባቶች የአሜሪካን ነጻነት ሲያውጁ በተፈራረሙት ሰነድ የሚከተለው ይገኛል።

> We hold these truths to be self-evident, that all men are created equal, that they are endowed by their creator with certain unalienable rights that among these are the pursuit of happiness- that to secure these rights, Governments are instituted among men, deriving their just power from the consent of the governed. '
>
> Taken from 'Declaration of Independence'

የዲሞክራሲያዊ ሥርዓተ መንግሥት ምስረታ ዋና መሰረቱ የሰዎችና የሕዝቦች መብት መከበር ስለሆነ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓተ መንግሥትና የሰዎች መብቶች መከበር የሚነጣጠሉ አይደሉም። ስለሆነም የዲሞክራሲያዊ ሥርዓተ መንግሥት መንስኤውም ሆነ ዋና መገለጫው የሰዎች መብቶች መከበር ነው ማለት ይቻላል።

2. <u>የመብቶች አከፋፈል (classification of rights)</u>

ምሁራን የሰዎች መብቶችን የተለያዩ መስፈርቶችን በመጠቀም ከፋፍለው ያስቀምጣሉ። በአንዳንዶቹ positive and negative ተብለው ሲከፋፈሉ negative ማለት መንግሥት እጁን እንዲሰበስብ የሚያስገድዱ ለምሳሌ በህይወት የመኖር መብትን ማወቅ ማለት ሲሆን Positive ማለት ደግሞ መንግሥት ለሁሉም እኩል ጥበቃ ሊያደርግ የሚገባው ለምሳሌ የትምህርትና የጤና መብት ለሁሉም ማዳረስ ማለት ነው። በሌላ በኩል ደግሞ አንደኛ ትውልድ መብት (first generation) ማለትም ሰብአዊና ፖለቲካዊ መብቶች፣ ሁለተኛ ትውልድ መብት (second generation) ማለትም ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ መብቶች እና ሶስተኛ ትውልድ መብት (third generation) ማለትም በንጹህ አካባቢ የመኖር መብት ወዘተ... በማለት ይከፋፈላሉ። በኢፌዲሪ ህገ መንግስት መብቶችን ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በማለት ይከፍላቸዋል። በዚህ ጽሁፍ የኢፌዲሪ ህገ መንግስትን መስፈርት መሰረት አድርገን ለመመልከት እንሞክራለን።

## አንቀጽ 10

## ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች

1. ሰብዓዊ መብቶችና ነፃነቶች ከሰው ልጅ ተፈጥሮ የሚመነጩ የማይጣሱና የማይገፈፉ ናቸው ብሏል፡፡
2. የዜጎች እና ሕዝቦች ሰብዓዊና ዲምክራሲያዊ መብቶች ይከበራሉ፡፡

በንዑስ አንቀጽ 2 እንደተደነገገው እነዚህ ሰብዓዊ መብቶች እንዲሁም ዲሞክራሲያዊ መብቶች እንደሚከበሩ ደንግጓል፡፡ የዜጎች ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች መከበር ሰላምን ለማስፈን ልማትን ለማምጣት እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ዜጎች መብታቸው ከተከበረ ወደ አመጽና ሁከት መፍጠር የሚሄዱበት ምክንያት አይኖርም፡፡ ኑሮአቸውን ለማሻሻል ብቻ ተግተው እንዲሠሩ የሚያደርግ ነው፡፡ በተለይ በኢትዮጵያ ሁኔታ ለሰላምም ለእድገትም የሰብዓዊና ዲሞክራሲ መብቶች መከበር መሠረታዊ ቅድመ ሁኔታ ነው፡፡

### ሰብዓዊ መብቶች

ሰብዓዊ መብቶች ማለት ማንም የሚሰጣቸው ወይም የሚነፍጋቸው ሳይሆን ሰዎች በመሆናቸው ብቻ በተፈጥሮ ያገኟቸው መብቶች ማለት ነው፡፡ መንግሥት እነዚህን መብቶች እውቅና ይሰጣቸዋል እንጂ የሚያበረክታቸው ስጦታዎች አይደሉም፡፡ እነዚህ መብቶች ከዜግነት ጋር የተያያዙ ሳይሆን ሰው በመሆኑ ብቻ የሚከበሩ መብቶች ናቸው፡፡

ሰብዓዊ መብቶች ተብለው ከሚጠቀሱት መካከል አንዳንዶቹ፣

1/ በሕይወት የመኖር መብት፣

2/ የአካል ደህንነት መብት እና

3/ የነፃነት መብት ናቸው፡፡

### ዲሞክራሲያዊ መብቶች

ዲሞክራሲያዊ መብቶች የሚባሉት ዜጎች በአንድ አገር አብረው በመኖራቸው ምክንያት በጋራ የመሰረቱት ማህበረሰብ ውስጥ የሚኖራቸውን እኩል ተሳትፎና

ተጠቃሚነት በሚመለከት እኩል መብት እንዳላቸው የሚያረጋግጥ በሥርዓቱ እውቅና የሚሰጠው መብት ነው።

ዲሞክራሲያዊ መብቶች ተብለው ከሚታወቁት መካከል አንዳንዶቹ፣

1/ ሃሳብን በነፃ የመግለጽ መብት፣

2/ የመሰብሰብ፣ የመደራጀትና ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ መብት፣

3/ የመምረጥና የመመረጥ መብት ናቸው።

## 3. በመብቶች ላይ ስለሚኖር ገደብ

በዴሞክራሲያዊ ስርአት ዜጎች ሁሉ እኩል በመሆናቸው በመብት አጠቃቀም እኩል ተጠቃሚ ናቸው። በዚህም መሰረት ለምሳሌ ሃሳብን የመግለጽ መብት የሁሉም መብት ስለሆነ አንዱ ሃሳቡን ሲገልጽ ሌላውም የተለየ ሃሳብ ካለው ያንን ሀሣቡን የመግለጽ መብት አለው ማለት ነው። እኔ ያቀረብኩትን ሃሳብ ሌላው ሊቀበል ይገባል አለበለዚያ መብቴ አልተከበረም የሚል አመለካከት የራስን ብቻ እንጂ የሌላውን መብት አለማወቅ ይሆናል። ስለሆነም ማንኛውም ሰው በመብቱ ሲጠቀም የሌሎችን ሰዎች ተመሣሣይ መብቶች ማክበር ይገባዋል። ስለሆነም የማንኛውም ሰው መብት እውቅና የሚሰጠውና ጥበቃ የሚደረግለት የሌላውን ሰው መብት እስካከበረ ድረስ ብቻ ነው። የሌላውን ሰው መብት የሚነካ ሲሆን መብት መሆኑ ያቆምና የሌላውን ሰው መብት መጣስ ይሆናል። ይሁንና የአንደኛው መብት አቁሞ የሌላው የሚጀምርበትን መለያውን ማስመር ከባድና አስቸጋሪ ነው። ይህ በተለይ ሃሳብን ከመግለጽ መብት ጋር በተያያዘ ጎልቶ ይታያል። ስለሆነም የአንዱን መብት ከሌላው መብት ጋር አጣጥሞ መሄድ አንዱ በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት የሚያጋጥም ፈተና ነው።

መብቶች ሊከበሩ የሚችሉት መብቶች ሲጣሱ የሚያስከብር ሥርዓት ሲኖር ነው። ስለሆነም መብቶች እንዳይጣሱ፣ ከተጣሱም አጥፊው የሚቀጣበት ወይም ላደረሰው ጉዳት ተመጣጣኙን የሚከፍልበት ህግና ስርአት መኖር አለበት። በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ሥርዓቱ የሚገዛበትና የሚተዳደርበትና የሚገዛበት ሕግና ሥርዓት አለ። ዲሞክራሲያዊ ሥርዓቱን ማስጠበቅ ማለት እነዚህን ሕጎችና ሥርዓቶች ማስጠበቅ

ማለት ነው። መብቶች እንዲከበሩ እነዚህ ህግና ስርአቶች መከበር አለባቸው። እነዚህ ህግና ስርአቶች ችግሮችና ጉድለት ያለባቸው ቢሆንም በህግና በስርአት መሰረት ብቻ ነው ሊታረሙና ሊስተካከሉ የሚገባው። ህግና ስርአት እስከሆኑ ድረስ ግን ማንም ሰው ሊያከብራቸው ይገባል። ስለሆነም ዜጎች የዲሞክራሲያዊ ሥርዓቱን ለመጠበቅ ተብለው የወጡ ህጎችና ሥርዓቶችን የማክበር ኃላፊነት አለባቸው። ይሁንና የሕግ ማስከበር ሥራው የት አቁሞ ሰብዓዊ መብት መጣስ የሚጀምረው የቱ ጋ እንደሆነ መለየትም ከባድና አስቸጋሪ ነው። እነዚህን ሕጎች ለማስፈጸም የቆመው የሕግ አስፈጻሚ አካል ሕግን ለማስከበር በሚወስደው እርምጃ የሰብዓዊ መብቶች ሊነኩና ሊጣሱ ይችላሉ። በዚህ ምክንያት በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት የሕግ አስፈጻሚው አካል ከፍተኛ ፈተና እንደሚገጥመው መገመት አያስቸግርም። ብዙውን ጊዜ የሰብዓዊ መብት ተከራካሪ ቡድኖች ትኩረት ሰጥተው የሚተቹት ወንጀል በመፈጸሙ የሚፈጸመውን የሰብዓዊ መብት መጣስ ሳይሆን የሕግ አስከባሪው ሕግ ሊያስከበር በሚወስደው እርምጃ የወንጀል ተጠርጣሪ መብት እንዳይነካ መከላከል ላይ ነው።

መብቶች በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ምክንያት ሊገደቡ ይችላሉ። በህገ-መንግሥቱ አንቀጽ 93 የውጭ ወራሪ ሲያጋጥም፣ ህገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን አደጋ ላይ የሚጥል ሁኔታ ሲከሰትና በተለመደው የሕግ ማስከበር ለመቋቋም የማይቻል ሲሆን መብቶች ሊገደቡ እንደሚችሉ ተደንግጓል። ነገር ግን በአንቀጽ 18 የኢሰብአዊ አያያዝ ስለመከልከሉ፣ በአንቀጽ 25 የእኩልነት መብትና በአንቀጽ 39 የብሔር ብሔረሰቦች መብት እንደማይገደብ ደንግጓል።

## 4 የአብዛኛው ሥልጣን በአናሳው ቡድን መብት የሚገደብ መሆኑ (the majority rule restrained and limited by the rights of the minorities)

የመብት አከባበር ሲወሳ የማኅበረሰቡ አናሳ ክፍሎች መብት የተለየ ትኩረት የሚሰጠው መሆኑ ግንዛቤ መውሰድ ያስፈልጋል። ዲሞክራሲ የአናሳውን ክፍል ጥቅምና አስተያየት ከግንዛቤ ማስገባትና በተቻለ መጠን በአወካከል ሆነ የአስተያየቱን መከበር በተግባር መገለጽ ይኖርበታል። ይህ ካልሆነ ግን ማንኛውም ማኅበረሰቡን የሚነካ ውሳኔ በድምጽ ብልጫ ብቻ ከተወሰነ አናሳው ክፍል ጥቅሙ አንዳንድ ጊዜ ሳይጠበቅለት

ይቀራል። ከዚያም አልፎ ሊረሳና ሊጨቆንም ይችላል። ይህ ሲሆን አናሳዎች ማኅበረሰቡ ውስጥ በእኩልነት ተሳታፊ ሆነው አብረው የመኖር ፍላጎታቸው ሊመነምን ይችላል።

አናሳ ሲባል የብሔረሰብ፣ የባህል፣ የሃይማኖት፣ የቋንቋ እንዲሁም ደግሞ የፖለቲካ አስተያየት የሚወክሉ ክፍሎችን ሁሉ ያካትታል።

የእነዚህ አናሳዎች ቁጥር በዛ ካለ፣ ቁጥራቸው በሚፈቅደው መጠን የፖለቲካ ውክልና ሊያገኙ ስለሚችሉ የመብታቸው መከበር ሁኔታ አጠያያቂ ላይሆን ይችላል። ነገር ግን በሚኖሩበት ማኅበረሰብ ወይም ብሔረሰብ ክልል ውስጥ ቁጥራቸው በጣም አነስተኛ ሆኖ በፖለቲካ ተቋማት ውስጥ ውክልና ለማግኘት የማይችሉ ከሆነ ሕልውናቸው፣ ጥቅማቸውና አስተያየታቸው እንዲታወቅና እንዲከበር የተለየ መብት እንዲሰጣቸው ማድረግ የዲምክራሲ መርሆ የሚጠይቀው ነው። ለምሣሌ በአንድ ክልል ውስጥ የሚኖሩ በቁጥራቸው ማነስ ምክንያት ውክልና ማግኘት ካልቻሉ ከብዙሃን አወካከል ለየት ያለ የአወካከል መብት በተለያዩ የዲሞክርሲ ሥርዓት ይሰጣቸዋል። ስለዚህ የአንድን ማኅበረሰብ አናሳ ክፍሎች መብት ማስጠበቅ የዳሞክራሲን መርሆ የሚቃረን ሳይሆን ዲሞክራሲን እንደማጠናከር የሚቆጠር ነው።

ከዚህ በላይ እንደቀረበው በአንድ በኩል የብዙሀኑ የበላይነት ማስከበር በሌላ በኩል የአናሳውን መብት መጠበቅ የሚቃረኑ ይመስላሉ። ይሁንና እነዚህ የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት የመሠረተ ምሰሶዎች ናቸው። የአብዛኛው የበላይነት የሚያስፈልገው በጋራ ጉዳይ ላይ ለመወሰን እንጂ ሌላውን አናሳ ወገን ለመጨቆን የተዘጋጀ አይደለም።

ስለሆነም በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት የአናሳዎች መሠረታዊ መብቶች መከበር የዲሞክራሲያዊ ሥርዓቱ መሠረታዊ መለያ ባሕርይ ነው። አናሳዎች መብታቸው እንደተከበረ ካረጋገጡ በዳሞክራሲያዊ ሥርዓቱ ውስጥ አዎንታዊ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ማረጋገጫ ነው።

በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት የአናሳውን መብት ለመጠበቅ የሚያስችል ድንጋጌዎች ይገኛሉ። እነርሱም፣

1. <u>የብሔር ብሄረሰብ የራስን እድል በራስ የመወሰን እስከመገንጠል መብት</u>። ይህ መብት የብሔረሰቡን ቁጥር ከግምት ሳያስገባ ለማንኛውም ብሄር ብሄረሰብ በሕገመንግሥቱ የተረጋገጠ መብት ነው። ስለሆነም በቁጥሩ አነስተኛ የሆነ

ብሄር ወይም ብሄረሰብ በተመሰረተው ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት መሠረት አሁን የሚገኝበት ሁኔታ ካልተመቸውና ካልተስማማው ማንም ሌላ ወገን ሳያገባው የራሱን መስተዳድር ለመመስረት ወይም እስከመገንጠልና የራሱን መንግሥት ለመመስረት የሚያስችለው መብት ነው፡፡

2. <u>በፌዴሬሽን ምክር ቤት ብሄረሰብን መሠረት ያደረገ ውክልና፡፡</u> በኢፌዲሪ የተወካዮች ምክር ቤት አባልነት የተመሠረተው በሕዝብ ብዛት አንድ ሰው አንድ ድምጽ የሚለውን መሰረት ባደረገ ውክልና ነው፡፡ በዚህም ምክንያት አብዛኛው ሕዝብ የያዘው ብሄረሰብ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ውክልና ይኖረዋል፡፡ በተወካዮች ምክር ቤት እያንዳንዱ ብሄር ብሄረሰብ ውክልና ሊያገኝ በሚችል መልኩ የምርጫ ክልል እንደሚወሰንም ተመልክቶአል፡፡ በዋነኛት ግን በፌዴሬሽን ምክር ቤት እያንዳንዱ ብሄር ብሄረሰብ የሚወከልበት ስለሆነም አናሳ ብሄረሰቦች ከፍተኛ ቁጥር ያለው ውክልና እንዲኖራቸው የሚያደርግ ነው፡፡

3. <u>በሕገመንግሥቱ የተደነገጉ መሠረታዊ መብቶች፡፡</u> እነዚህ በመሠረቱ የአናሳ ቡድኖች መብት ለመጠበቅ ተብለው የተደረገጉ መብቶች ናቸው፡፡ እነዚህን መሠረታዊ መብቶች ለመለወጥ የሚቻለው ሁሉም የክልል ምክር ቤቶች ሲስማሙ ብቻ ነው፡፡ አንዱ አነስተኛ ቁጥር ያለው ክልል ምክር ቤት ካልተስማማ እነዚህ መብቶች ላይ አንድም ዓይነት መሻሻል አይደረግም፡፡

*<u>መወያያ ጥያቄዎች</u>*

1. ዲሞክረሲ የብዙሀን አገዛዝ ነው፡፡ ስለሆነም የግለሰብ መብት መከበር ከዴሞክራሲ ጋር ምን ያገናኘዋል?
2. በህገመንግስቱ የሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በተደነገጉበት ክፍል አንዳንድ አንቀጾች ለምሳሌ አንቀጽ 15፣ 17፣19(6) እና ሌሎችም ‹በሕግ የተደነገገ ካልሆነ› የሚሉ ሀረጎች አሉባቸው፡፡ ይህ ማለት ህግ አውጪው አካል በህግ በሚደነግገው መሰረት መብቶቹ እንደሚከበሩ የሚያመለክት ነው፡፡ ይህ በህግ የተደነገገ የሚለው አባባል ህግ አውጪው እንደፈለገው የመብቶችን አፈጻጸም እንዲያጠብ ወይም በተዘዋዋሪ መብቶችን እንዲነፍግ የሚያደርገው አይሆንም ወይ? ለዚህ ምን መከላከያ አለው?
3. ዜጎች አስተዳደራዊ በደል ደረሰብን፣ ተጉላላን፣ መንግስት አሰራሩን ያሻሽል በማለት በተደጋጋሚ ሰላማዊ ሰልፍ በማድረግ ጥያቄ ለመንግስት ቢያቀርቡም፣ መንግስት

ጆሮ ዳባ ልበስ በማለት ጨርሶውኑ አልሰማቸውም። እነዚህ ሰዎች የዴሞክራሲ መብታችን አልተከበረም በማለት ወደአመጽ ስራ ገቡ። የዴሞክራሲ መብት ተከበረ የሚባለው አቤቱታ የማቅረብ መብታቸው ሲከበር ነው ወይስ አቤቱታቸው ተቀባይነት አግኝቶ መንግስት እነሱ እንደሚፈልጉት ሲያደርግ ነው? ዜጎች መንግስት አልሰማቸው ሲል ወደአመጽ ስራ ከመግባት ሌላ ምን ምርጫ አላቸው?

4. ህገወጥ የሆነ ስብሰባ ያደረጉ ሰዎችን ፖሊስ እንዲበተኑ ማሳሰቢያ ቢሰጥም ለመበተን ፈቃደኛ አልሆኑም። እንዲያውም በፖሊሶች ላይ ድንጋይ መወርወር ይጀምራሉ። ፖሊሶች መሳሪያ ቢይዙም በተመሳሳይ መልኩ በረባሾቹ ላይ ድንጋይ ይወረውራሉ። ከፖሊሶች በተወረወረ ድንጋይ አጉል ቦታ የተመታ የረባሾች አባል ይሞታል። ድንጋይ ወርዋሪ ፖሊሶች ሰው በመግደል ወንጀል ሊከሰሱ ይገባል ወይ? የሚከሰሱ ከሆነ የህግ ማስከበር ተግባር እንዴት ሊከናወን ይችላል?
5. በነጻነት ላይ ከሚጣሉ ገደቦች አንዱ ለህዝብ ሞራል ተቃራኒ ያልሆነ የሚል ነው። የሕዝብ ሞራል ነው? ለምሳሌ በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 27(5) ሃይማኖትንና እምነትን የመግለጽ መብት ሊገደብ የሚችለው ‹... የህዝብን የሞራል ሁኔታ...› ለማረጋገጥ ነው ይላል። በኢትዮጵያ የህዝብ የሞራል ሁኔታ ሲባል የትኛው ህዝብ ሞራል ነው?
6. የኢፌዲሪ ሕገመንግሥት ሰብአዊና ዲሞክራሱያዊ መብቶችን የያዘው ክፍልን ለማሻሻል ሁሉም ክልሎች ምክር ቤት በአብላጫ ድምጽ መስማማት አለባቸው ይላል። ይሁንና አነስተኛ ውክልና ያለው የሀረሪ ክልል ምክር ቤት ካልተስማማ ሊቀየር አይችልም። በዚህ ሁኔታ በአናሳው ወገን ፍላጎት ብቻ የአብዛኛው ወገን ፍላጎት እንዲወሰን እያደረገ እንዴት ዲሞክሪሲያዊ ነው ሊባል ይችላል?

### 1.4.3. <u>የሃይማኖትና መንግሥት መለያየት</u>

የዜጎችን መሰረታዊ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን እውቅና የሰጠ ስርአተ መንግስት በመሰረቱ የአንድ ሀይማኖት አራማጅ ሊሆን አይችልም። ስለሆነም ዲሞክራሲያዊ በሆነ ስርአተ መንግስት መንግስትና ሀይማኖት የተለያዩ ናቸው። በታሪክ እንደሚታወቀው ለሰብአዊ መብት መከበር የተደረገው ትግል አንዱና መሠረታዊ መብት የእምነት ነጻነት መከበር ነው።

የሀይማኖትና የእምነት ነጻነት ሀሳብን በነጻ ከመግለጽ መብት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ የእምነትና የራስን ሀሳብ የመግለጽ መብት በተከበረበት ሁኔታ የሀይማኖት ነጻነት መከበርም የግድ ነው፡፡

ሀይማኖት በመንግስት ሥራ ውስጥ የሚገባ ከሆነ መንግስት የአንድ ሀይማኖት መንግስት ይሆናል፡፡ መንግሥት የአንድ ሀይማኖት ተከታይ በሆነበት፣ የእምነት ነጻነት ሊከበር አይችልም፡፡ ወይም በሌላ አነጋገር የአንደኛው እምነት ማስፋፊያ መሣሪያ ሲሆን፣ የዜጎች እኩልነት ሊከበር አይችልም፡፡ መንግሥት ከያዘው እምነት የተለየ እምነት ያለው በመንግሥት ሥራና ኃላፊነት ሊሳተፍ አይችልም፡፡ በዚህ ምክንያት የሌላ ሀይማኖት ተከታይ የሆኑ ዜጎች እኩል የሚወከሉበት አይሆንም፡፡ የተወሰነውን የህብረተሰብ ክፍል ሀይማኖት የሚወክል መንግስት የሁሉም ህዝብ መንግስት ስለማይሆን መንግስትና ሀይማኖት ባልተለያዩበት ሁኔታ የህዝብ ሉአላዊነት ሊከበር አይችልም፣ ዲሞክራሲያዊ ስርአትም ሊኖር አይችልም፡፡ ስለሆነም መንግሥት ከሀይማኖት ነጻ መሆን ይኖርበታል፡፡ ይህ ማለት የመንግሥት ኃላፊዎች የራሳቸው ሀይማኖት አይኖራቸውም ማለት አይደለም፡፡ ይሁንና ሀይማኖታቸው የመንግሥት ሥራ መምራት የለበትም ማለት ነው፡፡

ኢትዮጵያ የተለያዩ ሀይማኖት ያላቸው ህዝቦች የሚኖሩባት አገር እንደመሆኗ መጠን መንግስትና ሃይማኖት መለያየቱ የህዝቡን ሉአላዊነት ከማረጋገጥ አንጻር መሰረታዊ ጉዳይ ነው፡፡

በህገመንግስቱ በአንቀጽ 11 የሚከተለው ተደንግጎአል፡፡

1. መንግስትና ሀይማኖት የተለያዩ ናቸው
2. መንግስታዊ ሀይማኖት አይኖርም
3. መንግስት በሀይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም፡፡ ሃይማኖትም በመንግስት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም፡፡

በአንቀጹ ከተመለከተው በመነሳት መረዳት የሚቻለው የመንግስት ሚና የዜጎችን የሀይማኖት ነጻነት እንዲከበርና እንዲረጋገጥ ከማድረግ ያለፈ በሀይማኖት ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ እንደማይገባ ነው፡፡

ይህ ማለት ግን ሀይማኖትን ከለላ አድርገው የሚነሱ የአመጽ እንቅስቃሴዎችን በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም በማለት እጁን አጣጥፎ የሚቀመጥበት ጉዳይ

አይደለም። አመጽና የጉልበት ስራ የአንዱን ፍላጎት በሌላው ላይ መጫን ስለሆነ ይህ ማለትም የአንዱን የሀይማኖት እምነት በሌላው ላይ ለመጫን የሚደረግ እንቅስቃሴ በመጀመሪያ ደረጃ የሀይማኖትና የእምነት ነጻነትን የሚጻረር ስለሚሆን፣ መንግስት የሀይማኖት ነጻነትን የማስከበር ግዴታ ስለአለበት እንዲህ አይነት በሃይማኖት ከለላ የሚነሱ የአመጽ ድርጊቶችን መቆጣጠርና ማስቆም መንግስታዊ ግዴታው ነው።

ለረጅም ጊዜ የሀይማኖት እኩልነት ባልነበረበት አገር ውስጥ በሀይማኖቶች መካከል እኩልነትን የሚያውቅ መንግስት በሚመሰረትበት ጊዜ ጭቆናና መድልዎ ሲደርስባቸው የነበሩ ሀይማኖቶች በተገኘው ነጻነት ለመጠቀም በሚያደርጉት እንቅስቃሴ አንዳንድ ችግሮች መፈጠራቸው አይቀርም። መንግስት እንዲህ አይነት ችግሮች ሲፈጠሩ በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ ሳይገባ በጥንቃቄና በሰላማዊ መንገድ የሚፈቱበትን መንገድ መሻት ይኖርበታል።

<u>መወያያ ጥያቄዎች</u>

1. የሀይማኖት ትምህርት ፈሪሀ እግዚአብሄርን በማሳደር ዜጎች ከልጅነታቸው ጀምረው መልካም ስነምግባር እንዲይዙ የሚያደርግ ነው። መንግስትም በሀይማኖት ሲመራ ፈሪሀ እግዚአብሄር ያላቸው ብቻ ስለሚመረጡ ለመልካም አስተዳደር መሰረት ነው። ነገር ግን መንግስት ከሀይማኖት እንዲለይ በመደረጉ ለስነምግባር መላሸቅ፣ ለሙስናና ለአልጠግብ ባይነት መስፋፋት ምክንያት ነው ብለው የሚከራከሩ አሉ። በዚህ አስተያየት ምን ያህል ይስማማሉ? መልካም ስነምግባርን ለማስፈን መንግስት ምን ማድረግ ይችላል?
2. የሃይማኖት ድርጅቶች አንዳንድ ጊዜ ሰላምን ለማምጣት በፖለቲካ ኃይሎች መካከል የሽምግልና ሥራ ሲሰሩ የታያል። ይህ በመንገሥት ጉዳይ ጣልቃ እንደመግባት ሊቆጠር ይችላል ወይ? ሃይማኖት በመንግሥት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም ማለት ምን ማለት ነው?
3. ሃይማኖት በመንግስት ስራ ጣልቃ አይገባም ይባል እንጂ ሃይማኖተኛው የመንግስት ባለስልጣን የሃይማኖቱን ህግጋት ተግባራዊ እንዳያደርግ ምን ይከለክለዋል?
4. መንግስት በሀይማኖት ጉዳይ አይገባም ሲባል ምን ማለት ነው? የራሳችሁ ጉዳይ እንደፈለጋችሁ ሁኑ ብሎ እጁን መሰብሰብ ብቻ ነው? በአንድ ወቅት የተገፉና የተጎዱ ሀይማኖቶችና የሀይማኖቱ ተከታዮች እምነታቸውን ለመተግበር

የሚፈልጉትን ሁኔታ (ለምሳሌ የአምልኮ መፈጸሚያ ቦታዎችን) እንዲያገኙ ማድረግ በሀይማኖት ጉዳይ ጣልቃ መግባት ነው?

## 1.4.4. <u>የሕግ የበላይነት</u>

### 1.4.4.1. <u>የህግ የበላይነት ጽንሰሀሳብ</u>

የሕግ የበላይነት ማለት ማንም ሰው ቢሆን ከሕግ በላይ አይደለም፣ ለሚሠራው ሥራ ሁሉ ተጠያቂ ነው ማለት ነው፡፡ የሕግ የበላይነት በሌለበት ሁኔታ ሊኖር የሚችለው የሰዎች የበላይነት፣ ይህም ማለት ጉልበትና ኃይል ያላቸው ሰዎች የበላይነት ነው፡፡ ሁሉም ሰው በሕግ በማይጠየቅበት ሥርዓት ተጠያቂ ያልሆነው ወገን እንደፈለገውና እንዳሻው ማድረግ ይችላል ማለት ነው፡፡ በታሪክ ገዥዎችና ሕግ አንድና አንድ የነበሩበት ጊዜ ነበር፡፡ ስለሆነም ሕግ ማለት የገዥው ፍላጎትና ፈቃድ ማለት ነበር፡፡

What pleases the ruler is the law. የሕግ የበላይነትን ማክበር ማለት፣

- ሀገሪቱ የበላይ ሕግ የሆነውን ሕገ መንግሥቱን ማክበርና ማስከበር፣
- በሕገ መንግሥቱ መሠረት ሥልጣን የተሰጣቸው አካላት የሚሰጡትን ውሳኔ ማክበርና ለውሳኔ ተገዥ መሆን፣
- በሚሰጡት ውሳኔዎች ላይ ቅሬታ ከአለ፣ በህገ መንግስቱ የተረጋገጡት መብቶች ከተጣሱ፣ ወይም ማንኛውንም አይነት አለመግባባት የተቀመጡ የህግ ስርአቶች ተከትሎ እንዲስተካከሉ፣ እንዲታረሙ ማድረግ፣ ማለት ነው፡፡

የሕግ የበላይነት በተለያዩ መልኮች ይገለጻል፡፡

1. <u>ሥልጣንን መወሰን ( Limitation of power )</u>

የሕግ የበላይነት አንዱ መሠረታዊ መገለጫ ባለሥልጣኖች እንደፈለጉት ያለገደብ የሚወስኑበት ሁኔታ እንዳይኖር በማድረግ የመወሰን ሥልጣናቸውን መገደብ ነው፡ ፡ Rule of law puts limits on the discretionary power of the government, including the power to change laws.

ይህም ማለት ማንኛውም የስልጣን አካል ወይም ባለሥልጣን የሚሰራው ሥራ በህግ በተሰጠው ስልጣን ላይ ብቻ መሆን አለበት ማለት ነው፡፡ በህግ ከተሰጠው ስልጣን በላይ መስራት ያለስልጣን መሥራት ስለሆነም የህግ መጣስ ይሆናል ማለት ነው፡፡

## 2. በህግ ፊት እኩልነት፣

የህግ የበላይነት ሌላው መገለጫ ማንኛውም ሰው የፈለገው የስልጣን ደረጃ ይኑረው ሁሉም ሰው በህግ ፊት እኩልና ተጠያቂ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ስለሆነም በየትኛውም ደረጃ የሚገኝ ሰው ለሚፈጽመው የህግ መጣስ በተመሳሳይ ህግና ስርዓት መሠረት ይጠየቃል ማለት ነው፡፡

## 3. ስልጣንን በመጠቀም ጊዜ የሚኖር የሥነሥርዓትና አፈጻጸም ሥርዓት፣

ማንኛውም የሥልጣን አካል ወይም ባለስልጣን ለመወሰን ስልጣን ባለው ጉዳይ ላይ ሲወስን በውሣኔ አሰጣጡ ሂደት ሊከተላቸው የሚገቡ ስርዓቶች፣ ሊጥሳቸው የማይችሉ መሠረታዊ መብቶች አሉ፡፡ ስለሆነም የመወሰን ስልጣን ቢኖረውም በሚወስንበት ጊዜ ሊከበሩ የሚገባቸው የሥነሥርዓት ህጎችና ደንቦች ቀደም ብለው የተዘጋጁና ሁሉም ሰው የሚያውቀቸው ሊሆኑ ይገባል፡፡ እነዚህ ህጎች በግልጽነት ተግባራዊ መደረግ አለባቸው፡፡

If the government is to be restricted in its exercise of discretion, the government has to follow legal procedures that are pre-fixed and pre-announced.

ስለሆነም ለምሣሌ ወንጀል ሰርቶአል ተብሎ የሚጠረጠር ሰው ላይ ምርመራ ሲደረግ ወይም ክስ ቀርቦ ሲወሰንበት በማስረጃ ማሰባሰብ፣ በክርክር ሂደት ላይ የህግ አስፈጻሚውና ፍርድ ቤቱ ሊያከብረው የሚገባው ስርዓት ማለት ነው፡፡ ህግ አውጪው ህግ በሚያወጣበት ጊዜ ሊጥሳቸው የማይችላቸው መሰረታዊ መብቶች እንደአሉ ሁሉ ሕግ በማውጣት ጊዜ የሚከተላቸው ስርዓቶችም በዚህ ውስጥ የሚካተቱ ናቸው፡፡

የሉአላዊ ስልጣን ባለቤት የሆነው ህዝብ በተወካዮቹ አማካይነት ያወጣቸውን ህጎች ሲጣሱ የሚጥሰው ወገን ተጠያቂ ካልሆነ የህዝብ ሉአላዊነት ተጣሰ ማለት ነው፡፡ የሕዝብ ሉአላዊነት የሚረጋገጥ ከሆነ የሕግ የበላይነት መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ የህዝብ ሉአላዊነትና የህግ የበላይነት ሊነጣጠሉ የማይችሉ ናቸው፡፡ በዲሞክራሲያዊ ስርዓት ህጎች የህዝብ ሉአላዊነት መገለጫ ስለሆኑ ዜጎች እንዲያከብሩ የሚጠየቁት ሌላ ሰው በእነሱ ላይ የጫነውን ሕግ ሳይሆን እራሳቸው በቀጥታ ወይም በተወካዮቻቸው አማካይነት ያወጡትን ሕግ ነው፡፡ ስለሆነም በዲሞክራሲያዊ ስርዓት ውስጥ ይህ ዜጎች ህጉን አክብረው እንዲኖሩ አንድ መሠረታዊ ምክንያት ነው፡፡ ስለሆነም በዲሞክራሲያዊ ስርዓት ህጉን ለማክበር ምቹ ነባራዊ ሁኔታ አለ ማለት ይቻላል፡፡ የኤፌዲሪ ህገ መንግሥቱ የህገመንግሥቱ መሰረታዊ መርሆ አድርጎ ካስቀመጣቸው አንዱ የህግ የበላይነት መርህ ነው፡፡

## ህገመንግሥት አንቀጽ 9

1. ህገመንግሥቱ የሀገሪቱ የበላይ ሕግ ነው፡፡ ማንኛውም ሕግ ልማዳዊ አሰራር እንዲሁም የመንግሥት አካል ወይም ባለስልጣን ውሣኔ ከዚህ ሕገ መንግሥት ጋር የሚቃረን ከሆነ ተፈጻሚነት የለውም፡፡
2. ማንኛውም ዜጋ የመንግሥት አካላት የፖለቲካ ድርጅቶች ሌሎች ማህበራት እንዲሁም ባለስልጣኖቻቸው ሕገመንግሥቱን የማስከበርና ለህገመንግሥቱ ተገዥ የመሆን ኃላፊነት አለባቸው፡፡
3. በዚህ ሕገ መንግሥት ከተደነገገው ውጭ በማናቸውም አካኋን የመንግሥት ስልጣን መያዝ የተከለከለ ነው፡፡
4. ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች የሀገሪቱ ሕግ አካል ናቸው፡፡

በዚህ አንቀጽ በንኡስ አንቀጽ አንድ እንደተመለከተው ሕገመንግሥቱ የህጎች ሁሉ የበላይ ሕግ እንደሆነ፣ ከዚህ ሕገ መንግሥት በተቃራኒ መሄድ በፍጹም የተከለከለ

መሆኑን በመደንገግ የማንኛውም የመንግሥት ስልጣን አካል ስልጣን በሕገመንግሥቱ የተገደበ መሆኑን በመግለጽ የህግ የበላይነትን ያረጋግጣል፡፡

በንዑስ አንቀጽ ሁለትም ህገመንግሥቱን የበላይ መሆኑን መቀበልና ህገመንግሥቱን የማስከበርና ለህገመንግሥቱ ተገዥ መሆን የማንኛውም ዜጋ ሀላፊነት መሆኑን በመደንገግ ዜጎች ሁሉ በህግ ፊት እኩል ተጠያቂ መሆናቸውን በመደንገግ የህግ የበላይነትን አረጋግጦአል፡፡

በንዑስ አንቀጽ ሶስት ላይ ደግሞ በዚህ ሕገመንግሥት ከተደነገገው ውጭ ስልጣን መያዝ የተከለከለ መሆኑንም ደንግጎአል፡፡ ህገመንግሥቱ የመንግሥት ስልጣን የሚያዘው በምርጫ የአብዛኛውን ድጋፍ ያገኘ ብቻ እንደሆነ የደነገገ ሲሆን፣ ከዚህ ውጭ ስልጣን ለመያዝ መሞከር የህዝቡን የሉአላዊ ስልጣን ባለቤትነት አለመቀበል ስለሚሆንም ይህ የተከለከለ መሆኑን ደንግጎአል፡፡

### 1.4.4.2. <u>የህግ የበላይነትን ለማስፈን የተቀመጡ የህግ ስርአቶች</u>

1. <u>ስልጣንን በህግ መገደብ</u>

በማንኛውም ስርዓት የህግ የበላይነት እንዲረጋገጥ ከተፈለገ ገደብ የሌለው ስልጣን ያለው የመንግሥት አካል መኖር የለበትም፡፡ ማንኛውም የመንግሥት አካል ስልጣኑ በህግ የተገደበ መሆን አለበት፡፡ በዲሞክራሲያዊ ስርዓት ህገመንግሥቶች የከፍተኛው የስልጣን አካል / የህግ አውጪው ስልጣን / ስልጣን በህገመንግሥቱ የተገደበ ነው፡፡ ህግ አውጪው አካል ህግ የማውጣት ስልጣን ቢኖረውም ያለገደብ እንደፈለገው የሚያወጣው ሳይሆን በህገመንግሥቱ የተቀመጡ መሰረታዊ መብቶችንና ነጻነቶችን እንዲሁም የህግ ስርዓቶችን ባከበረ መልኩ ብቻ ነው ማውጣት የሚችለው፡፡ የሚወጡት ህጎች መሰረታዊ የሆኑ መብቶችን የሚያከብሩና የማይጥሱ መሆን አለባቸው፡፡

2. <u>የስልጣን/ ሥራ ክፍፍል መኖር፣</u>

ስልጣን በአንድ ቦታ ከማከማቸት ስልጣንን መከፋፈል የህግ የበላይነትን ለማረጋገጥ እንደአንድ መሣሪያ ይጠቀሳል፡፡ በንድፈ ሀሳብ ደረጃ ስልጣን አይከፋፈልም የሚከፋፈለው ተግባራቱ ናቸው የሚል ክርክር የሚያቀርቡ ምሁራን እንዳሉ ሁሉ፣ ስልጣን ይከፋፈላል ብለው የሚከራከሩ ምሁራን አሉ፡፡ ይህ የንድፈሀሳብ ክርክር እንደተጠበቀ ሆኖ በሁሉም ደሞክራሲያዊ ስርዓቶች ማለት ይቻላል የመንግሥት አካላት በህግ አውጪ፣ ህግ አስፈጻሚና ህግ ተርጓሚ የተከፋፈለ ነው፡፡ ስለሆነም ህግ አውጪው ህግ ከማውጣት አልፎ ህግ በማስፈጸም ስራ ውስጥ አይገባም፣ ወይም የዳኝነት ሥራ አይሰራም፡፡ የህግ አስፈጻሚውም ህግ ከማስፈጸም ውጪ ህግ የማውጣትም ሆነ የዳኝነት ስራ አይሰራም፡፡ የዳኝነት አካሉም ዳኝነት ከመስጠት ውጪ ህግ አያወጣም አያስፈጽምም፡፡

ይሁንና የእነዚህ አካላት አንዱን ሌላው የመቆጣጠሩ ሁኔታ እንደየስርአተ መንግሥቱ ይለያያል፡፡ ለምሳሌ በኘሬዚዳንታዊ ስርዓት ውስጥ ኘሬዚዳንቱና የፓርላማ አባላቶች በቀጥታ በህዝብ የሚመረጡ ስለሚሆኑ አንዱ ሌላውን መቆጣጠር የሚችልበት ስርአት ነው፡፡ በዳኝነት ስራ ላይ የሚቀመጠው የመንግሥት ሀላፊም በሁለቱ የሥልጣን አካላት ስምምነት የሚመረጥ በመሆኑ የዳኝነት አካሉ በአንደኛው ወገን ተጽእኖ ስር እንዳይወድቅ ያደርገዋል፡፡ የዳኝነት ስርዓቱ ደግሞ በሚቀርብለት ክስ መሠረት በእነዚህ አካላት የተሰሩ ህግን ያልተከተሉ፣ ስራዎች ወይም ከህግ ውጭ የተሰሩ ስራዎች እንዲስተካከሉ፣ አጥፊው እንዲቀጣ፣ ተጎጂው እንዲካስ ያደርጋል፡፡ ለምሳሌ በአሜሪካ ህግ አውጭው አካል የሚያወጣው ሕግ በህገ መንግሥቱ የተደነገጉትን መሰረታዊ መብቶች የሚቃረን ከሆነ በፍርድ ቤት ክስ ቀርቦበት ሊሻር ይችላል፡፡

በሌላ በኩል በፖርላሜንታዊ ስርዓት ህዝቡ በቀጥታ የሚመርጠው የህዝብ ተወካዮች የሚገኙበትን ህግ አውጪውን ብቻ ስለሚሆንና የሉአላዊነት መገለጫ ተደርጎ የሚወሰደው ይህ አካል ስለሚሆን ስልጣን እንደተከፋፈለ ተደርጎ አይቆጠርም፡፡ ህግ አውጪው ከመሀከሉ የአስፈጻሚውን አካል የሚመርጥበት ስርአት በመሆኑ ፖርላማው ከሁሉም የበለጠ ስልጣን ያለው ሲሆን በኘሬዚዳንታዊ ስርዓት እንዳለው

ሌሎች አካላት የሚቆጣጠሩት አይደለም፡፡ ይሁንና የስራ ክፍፍሉ ግን ተመሳሳይነት ያለው ነው፡፡ በዚህ ስርዓት ውስጥ የህግ አውጪው አካል በህጉ መሠረት መሰራቱን ለማረጋገጥ የተቀመጠ ስርዓትም እንደየአገሩ ይለያያል፡፡ በኢፌዲሪ ህገ መንግሥት የህግ አውጪው የሚያወጣው ሕግ ህገመንግሥቱን የሚቃረን ሆኖ ከተገኘ እና ይህንን በሚመለከት ጥቅም ያለው ወገን ከጠየቀ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ህጉ በእርግጥም ህገ መንግሥቱን የሚቃረን ሆኖ ከአገኘው ሊሽረው ይችላል፡፡ ስለሆነም በኢትዮጵያ ሁኔታ ህግ አውጪውን የሚቆጣጠር አካል በመኖሩ የህግ  የበላይነትን ለማረጋገጥ ጠንካራ ስርዓት እንደአለ ያመለክታል፡፡

ስልጣን ወደጎን ብቻ ሳይሆን ወደታች የሚከፋፈልበት ስርዓትም በተመሳሳይ መልኩ የስልጣን ክፍፍል አካል ነው፡፡ ፌዴራላዊ አወቃቀር ባላቸው አገራት ስልጣን በፌዴራል መንግሥቱና  በክልል መንግሥታት መካከል ይከፋፈላል፡፡ በኤፌዲሪ ቅረጻ መንግሥቱ ፌዴራላዊ በመሆኑ ምክንያት ለፌዴራል መንግሥትና ለክልል መንግስት የተከፋፈለ ነው፡፡ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግሥቱን ለመለወጥ የበርካታ ክልላዊ መንግስታት ስምምነት ያስፈልጋል ይህም ሥልጣንን ለተለያዩ አካላት በመከፋፈል የህግ የበላይነትን ለማስጠበቅ ጠንካራ ዋስትና መኖሩን የሚያሳይ ነው፡፡

## 3. <u>የዜጎች ዲሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶች መከበር</u>

የዜጎች ዲሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶች በመከበራቸው ዜጎች በመብታቸው ተጠቅመው በመንግሥት ላይ የሚታዩ ድክመቶችንና ስህተቶችን ጥፋቶችን የሚያጋልጡበት በዚህም መሰረት ሌሎች የመንግሥት የስልጣን አካላት በህግ መሠረት ሥራቸውን እንዲወጡ በማድረግ የህግ የበላይነት እንዲከበር ከፍተኛ ሚና አላቸው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞም ዜጎች ተወካዮቻቸውን በማንኛውም ጊዜ የመጥራትና የመተካት መብታቸውን በመጠቀም ተወካዮቻቸውን ሊሽሩ ስለሚችሉ መንግሥት በሕግና በህግ መሠረት ብቻ እንዲሰራ የሚያስገድድ አሰራር ነው፡፡

ይሁንና የህግ የበላይነት ሲባልና ህግ መከበር አለበት ሲባል ስርዓቱን ባልጠበቀና ከስልጣን ውጭ የወጣ ህግን ማክበርንም ይጠይቃል ወይ? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ በዲሞክራሲያዊ ስርዓተ መንግሥት ውስጥ ስርዓቱን ባልጠበቀ መሰረት የሚወጣ ህግ

ህግ አይደለም፡፡ ስለሆነም ይህንን አለማክበር እንደህግ መጣስ አይታይም የሚል ክርክር ሊቀርብ ይችላል፡፡

በብዙዎች ዲሞክራሲያዊ ስርዓት በተመሰረተባቸው አገራት ማንኛውም የስልጣን አካል የሚያወጣው ሕግ ወይም ደንብ የሚታረምበትና የሚስተካከልበት ስርዓት አለ፡፡ ስለሆነም ህጉ በአግባቡ ሥርዓቱን ጠብቆ የወጣ ነው ወይም አይደለም ብሎ ለመወሰን የሚችለው በስርዓቱ ውስጥ ይህንን ለመወሰን ስልጣን ያለው አካል ነው እንጂ ማንም ሰው አይደለም፡፡ ስለሆነም ማንኛውም ወገን ይህንን ስርዓት ተከትሎ ህጉ እንዲሻር ወይም እንዲለወጥ ጥያቄ በማቅረብ ውሣኔ እንዲሰጥ ማድረግ እንጂ ስልጣን ባለው አካል የወጣን ሕግ ወይም የተሰጠን ውሣኔ ሥርዓቱን የጠበቀ አይደለም ወይም ለምሣሌ ከሕገ-መንግሥቱ ጋር ይቃረናል በማለት አለማክበር አይችልም፡፡ የሕግ የበላይነት የሚረጋገጠው ማንኛውም ሰው ይህ ህግ ከስልጣን ውጪ የወጣ ስለሆነ ህግ አይደለም ስለሆነም አላከብርም በማለት ሳይሆን ህጉ እንዲሻር ወይም እንዲለወጥ በተቀመጠው ሥርዓት መሠረት ሥልጣን ላለው አካል በማቅረብና እንዲታረም በማድረግ ብቻ ነው፡፡

የህግ የበላይነት ባለበት የሰውን ውሣኔ ሰጪነት (Discretion ) ሙሉ በሙሉ ይጠፋል ማለት አይደለም፡፡ እያንዳንዷ ጉዳይ በሕግ ተወስና ትቀመጥ ቢባል ለአፈጻጸም አስቸጋሪ እንዲሁም ውሣኔ ከተጨባጭ ሁኔታ ጋር እየተገናዘበ መሰጠት የሚገባው ከመሆኑ አንፃር ፍትህንም ማዛባት ይሆናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የሚቻልም አይደለም፡፡ እራሱ ህጉ ቢሆንም ዝምብሎ የመጣ ሳይሆን በሰዎች የሚወጣ ነው፣ በራሳቸው ተግባራዊ የሚሆኑ ሳይሆኑ በሰው አማካይነት ተግባራዊ የሚሆኑ ናቸው፡፡ ስለሆነም ዋናው ጥያቄ የሰዎችን አገዛዝ ( Discretion) ሙሉ በሙሉ ማስወገድ ሳይሆን በህግ የበላይነትና በሰዎች የመወሰን ነጻነት መሀል ሚዛኑን ለመጠበቅ ነጻነትን እኩልነትን እና ፍትህን ማረጋገጥ ወይም ማግኘት የሚቻልበት ሥርዓት መዘርጋት ነው፡፡

**<u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>**

1. የመጨረሻ መጨረሻ ሕጉን የሚያወጡት ሰዎች ሆነው ሳለ እንዴት የሕግ የበላይነት ይባላል? ፈላጭ ቆራጭ ንጉሥ በሚያወጣው ህግና የህዝብ ተመራጮች በሚያወጡት ህግ መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው?
2. በኢትዮጵያ የስልጣን ክፍፍል (separation of power) አለ ወይ?
3. በሕገመንግሥቱ ውሣኔ እንዲሰጥ ስልጣን የተሰጠው አካል በአድልዎ ወይም በስህተት የሰጠውን ውሣኔ አለማክበር የህግ የበላይነትን እንደመጣስ ይቆጠራል ወይ?
4. በዲሞክራሲያዊ ስርዓተ መንግሥት የሕግ የበላይነት አለ ይባላል። በኢትዮጵያ አንዳንድ ጊዜ ሰብዓዊ መብቶች ሲጣሱ ይታያል። ይህ ባለበት ሁኔታ እንዴት የሕግ የበላይነት አለ ማለት ይቻላል?

## 1.4.5. <u>የመንግሥት አሰራርና ተጠያቂነት</u>

### 1.4.5.1. <u>ስለተጠያቂነት በጠቅላላው</u>

በዲሞክራሲያዊ መንግሥት ስልጣን የህዝቡ በመሆኑና የመንግሥት ሥራ የሚሰሩት የህዝብ ወኪሎች በመሆናቸው ተወካዮች ለመረጣቸው ህዝብ ተጠያቂ ናቸው። ማለትም ስለሥራቸው ሪፖርት ማቅረብ፣ መረጃ መስጠት እንዲሁም ህግን በመጣስ ለሚፈጽሙት ተግባር ተመጣጣኙን ቅጣት እንዲያገኙ ወይም ላደረሱት ጉዳት ካሣ የመክፈል ተጠያቂነት አለባቸው።

ህዝብ የመረጠው ተወካይ ተጠያቂነት የሌለው እንደሆነ የህዝብ ሉአላዊነት መናዱ አይቀርም። የሕዝብ ሉአላዊነት እውን ሊሆን ከሆነ ደግሞ ተወካዮች ተጠያቂ መሆን አለባቸው።

በኢትዮጵያ በተለይ ዲሞክራሲን የመገንባት ጉዳይ የህልውና ጥያቄ በሆነበት ሁኔታ ውጤታማ የሆነ የተጠያቂነት ስርዓት ከሌለ ዲሞክራሲ ስርዓትን መገንባት አይቻልም። ዲሞክራሲ የህልውና ጉዳይ በሆነበት አገር ውጤታማ ተጠያቂነት እንዲኖር ማድረግ በተመሳሳይ የሕልውና ጥያቄ ይሆናል።

ተጠያቂነትን በሚመለከት የኢፌዲሪ ህገ መንግሥት በአንቀጽ 12 እንደሚከተለው ያስቀምጣል።

1. የመንግሥት አሰራር ለሕዝብ ግልጽ በሆነ መንገድ መከናወን አለበት፡፡
2. ማንኛውም ሀላፊና የህዝብ ተመራጭ ሀላፊነቱን ሲያጓድል ተጠያቂ ይሆናል፡፡
3. ሕዝብ በመረጠው ተወካይ ላይ እምነት ባጣ ጊዜ ከቦታው ለማንሳት ይችላል፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡

1. መረጃ የማግኘት መብት

የተጠያቂነት የመጀመሪያ መርህ ግልጽነት ነው፡፡ መንግሥት ለወከለው ሕዝብ አሠራሩን ግልጽ በሆነ ሁኔታ የማከናወን ግዴታ አለበት፡፡ ሕዝቡ የመረጠው መንግሥት ምን እየሠራ እንደሆነ የማወቅ መብት አለው፡፡ ከግልጽነት አንጻር፣ ምን መደረግ አለበት?

1. ሕዝቡ በመንግሥት ውሣኔዎች ላይ በብቃት መሳተፍ የሚችለዉ ትክክለኛና ወቅታዊ መረጃ ማግኘት ሲችል ነው፡፡ ህዝቡ የመረጠው መንግሥት በትክክል መስራቱን ለመቆጣጠር የሚችለው … ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ ሲያገኝ ነው፡፡ ህብረተሰቡ ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ ማግኘት ከቻለ ነገሩ ሁሉ ግልጽ በመሆኑ ብቻ የአስተዳደር በደልና ብልሹነትን ለማስቀረት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማድረግ ይችላል፡፡ ግልጽነቱ ራሱ በቀጥታ ከሚያስከትለው መሻሻል በላይ ህብረተሰቡ ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ በማግኘት ጉድለቶችን ለማስተካከል ርምጃ እንዲወስድ ማድረግ ይቻላል፡፡ የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም፣ በሥነ-ምግባር ንዑስ ፕሮግራም ውስጥ ከተያዙት ፕሮጀክቶች አንዱ መረጃን የማግኘት መብት ህግ የማዘጋጀት ሲሆን ይህ ህግ ተዘጋጅቶ ሲጸድቅ ግልጽነትን ለማስፈን ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡
2. እያንዳንዱ መሥሪያ ቤት የሚሰጠውን መንግሥታዊ አገልግሎት በተመለከተ ምን ዓይነት አገልግሎት በምን መስፈርት ለማን እንደሚሰጥ በዝርዝር የሚያብራራ መመሪያ ማውጣትና ተጠቃሚው ህብረተሰብ ይህንኑ በሚገባ እንዲያውቅ መደረግ ይኖርበታል፡፡ በሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም የስነምግባር ንዑስ ፕሮግራም ውስጥ ተይዘው ከነበሩት ፕሮጀክቶች አንዱ የዜጎች

ቻርተር ሲሆን፣ ይህም ረቂቅ የተዘጋጀ ሲሆን ይህም ህግ ሆኖ ሲወጣ የተጠያቂነት ሥርዓት የተሟላ ይሆናል፡፡

3. ህግ አስፈጻሚው አካል የሚያወጣቸው ፖሊሲዎች የሚያቀርባቸው የሕግ ረቂቆች ወዘተ.. ጉዳዮች ላይ ህብረተሰቡ አስቀድሞ የተወያየባቸውና አስተያየት የሰጠባቸው ሊሆኑ ይገባል፡፡ ለተወካዮች ምክር ቤት በሚቀርቡ የህግ ረቂቆች ከመጽደቃቸው በፊት ህዝቡ አስተያየት እንዲሰጥበት የሚያደርግ ስርአት ተዘርግቶ እየተተገበረ እንደሆነ የሚታወቅ ነው፡፡

## 2. ተጠያቂነት

መረጃን የማግኘት መብት መረጋገጡ ሕዝቡ ወይም የሚመለከተው ወገን መረጃ አግኝቶ በራሱ በኩል ማድረግ የሚችለውን እንዲያደርግ የሚረዳ ቢሆንም ከዚሁ ጋር ውጤታማ የሆነ የተጠያቂነት ስርዓት መኖሩ የግድ አስፈላጊ ነው፡፡ ውጤታማ ተጠያቂነት ከሚገለጽባቸው መንገዶች መካከል ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

### 2.1. የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት

1. የህዝቡ ሉአላዊነት መገለጫ የሆነው ምክር ቤት በምክር ቤቱ የወጡ ሕጐች ፣ ፖሊሲዎች እቅዶች ምክር ቤቱ በሾማቸው የፖለቲካ ተሿሚዎች በትክክል ተፈጻሚ መሆናቸውን የማረጋገጥ ሥራ መሰራት አለበት፡፡ ምክር ቤቶች በቴክኒክ ጉዳይ የሚረዱዋቸው እንደዋና ኦዲተር ጽ/ቤት ያሉ አካላት የመንግሥት በጀትና ዕቅድ አፈጻጸምን በተመለከተ በመመርመር አስፈላጊውን መረጃ ስለሚያቀርቡ ምክር ቤቱ ሀላፊነቱን በሚገባ እንዲወጣ የሚረዱ ናቸው፡፡ የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋምም በአስፈጻሚው አካል የሚፈጸሙ የአስተዳደራዊ በደሎችን እየመረመረ አሰራሩ እንዲስተካከል በማድረግ ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ በመሳሪያነት የሚያገለግል ነው፡፡
2. የፖለቲካ ተሿሚዎች ቋሚ የመንግሥት ሰራተኞችና ሲቪል ሰርቪሱ በአጠቃላይ በምክር ቤቱ የተቀመጡ መሰረታዊ አቅጣጫዎችና እነዚህን ለማስፈጸም የሚወጡ እቅዶች ደንቦችና መመሪያዎች በትክክል መፈጸማቸውን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡

## 2.2. የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች

በመንግሥት ባለሥልጣኖችና ሠራተኞ የሚፈጸሙ የሙስና ወንጀሎችን ለመመርመርና ለመክሰስ እንዲሁም የሙስና ወንጀል እንዳይፈጸም ለመከላከል ነጻ የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች በፌዴራል በብዙ ክልሎች ተቋቁመዋል፡፡ በቀሪዎቹ ክልሎችም ይቋቋማሉ፡፡ ተብሎ ይገመታል፡፡

የፌዴራል ሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ሥልጣንና ተግባር በከፊል

2. አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ስለሙስና ጎጂነት የህዝቡ ንቃተ ህሊና እንዲጎለብት በማስተማር እና መልካም ስነምግባር በህዝብ አገልግሎት እና በህብረተሰቡ ውስጥ እንዲስፋፋ በማድረግ ሙስናንና ብልሹ አሰራርን መዋጋት፣
3. አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በመንግስት መስሪያ ቤቶች እና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ውስጥ ለሙስናና ለብልሹ አሰራር የተጋለጡና ሊጋለጡ የሚችሉ የአሰራር ስርአቶችን በማጥናት ወይም እንዲጠኑ በማድረግ እንዲሻሻሉ ማማከርና ማሳሰብ፣ የአሰራር ስርአቶቹ የተሸሻሉ መሆናቸውን መከታተል፣ እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ተገቢ የሆነው እርምጃ እንዲወሰድ ወይም ውሳኔ እንዲሰጥ አግባብ ላለው አካል በማሳወቅ ዌም በማሳሰብ ሙስናን መከላከል፣
4. በመንግስት መስሪያ ቤቶች ወይም በመንግስት የልማት ድርጅቶች ወይም ፌዴራል መንግስቱ ለክልሎች ከሚሰጠው ድጎማ ጋር በተያያዘ በክልል መ/ቤቶች በወንጀል ህግና በሌሎች ህጎች ውስጥ የተመለከቱት የሙስና ወንጀሎች በመንግስት ሰራተኞች ወይም ባለስልጣኖች ወይም በሌሎች ሰዎች ስለመፈጸማቸው ጥቆማ ሲደርሰው ወይም በቂ ጥርጣሬ ሲኖረው የመመርመርና የመክሰስ ወይም እንዲመረመርና እንዲከሰስ የማድረግ፣
5. ከሙስና ወንጀል ጋር በተያያዘ በቂ ጥርጣሬ ሲኖረው በማናቸውም ባንክ የሚገኝ የተጠርጣሪዎች የባንክ ሂሳብ በኮሚሽነሩ ትእዛዝ እንዲመረመር የማድረግ መረጃ የማግኘትና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በፍርድ ቤት ትእዛዝ እንዲከበር ማድረግ

በክልል ያሉ የስነምግባርና ጸረ ሙስና ኮሚሽኖች በክልላቸው ተመሳሳይ አይነት ስልጣንና ተግባር አላቸው፡፡

የፌዴራል ስነምግባርና ጸረ ሙስና ኮሚሽን በቀጥታ የስራ አስፈጻሚውን ለመከታተልና ለመቆጣጠር የተቋቋመ ስለሆነ የአስፈጻሚው አካል ተጽእኖ እንዳይደርስበት ለማድረግ የተቀመጡ ድንጋጌዎች በአዋጁ ውስጥ ይገኛሉ።

አንቀጽ 3(2) የኮሚሽኑ ተጠሪነት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ነው።

አንቀጽ 4. ስለኮሚሽኑ የአሰራር ነጻነት

በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 3(2) የተደነገገው ቢኖርም ኮሚሽኑ በሚመረምራቸው ወይም ክስ በሚመሰርትባቸው ወይም ክስ በመሰረተባቸው ጉዳዮች ከማንኛውም ሰው ወይም አካል ጣልቃ ገብነትና አመራር ነጻ ነው።

አንቀጽ 10

ኮሚሽኑ

1. በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት በተወካዮች ምክር ቤት የሚሾም አንድ ኮሚሽነር
2. በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሾም አንድ ምክትል ኮሚሽነር ይኖሩታል።

አንቀጽ 14

የኮሚሽነሩና የምክትል ኮሚሽነሩ የስራ ዘመን

1. የኮሚሽነሩና የምክትል ኮሚሽነሩ የሹመት ዘመን ስድስት አመት ይሆናል። ሆኖም አስፈላጊ ሲሆን እንደገና ሊሾም ይችላል።
2. ኮሚሽነሩ ወይም ምክትል ኮሚሽነሩ ከዚህ በታች ካልሆነ በስተቀር የተሾሙበት የስራ ዘመን ከማለቁ በፊት ከፈቃዱ ውጭ ከስራው አይነሳም

   ሀ. አግባብነት ባለው የስነምግባር ደንብ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ተላልፎ ሲገኝ፣

   ለ. ጉልህ የሆነ የስራ ችሎታና ቅልጥፍና የሌለው ሲሆን፣

   ሐ. በህመም ምክንያት ተግባሩን በተገቢው ሁኔታ ማከናወን የማይችል ሆኖ ሲገኝ፣

## <u>2.3. ነጻ ፍርድ ቤት</u>

የተጠያቂነት ሥርዓትን ከመመሥረት አንጻር ነጻነት ያለው ፍርድ ቤት መኖር አስፈላጊና መሠረታዊ ነው። አንድ የመንግሥት ኃላፊ ባጠፋው ጥፋት የሚጠየቅበትና የሚቀጣበት ነጻ የሆነ ፍርድ ቤት ያስፈልጋል። " የሕግ አስፈጻሚው አካል በተጠያቂነት

መርህ እንዲሰራ ከማድረግ አኳያ የዳኝነት አካሉና የዳኝነት አካላት ተብለው የሚታወቁት ተቋሞች ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሊያደርጉ ይችላሉ። መስተዳድሩ ከሕግ ውጭ የዜጎችን መብትና ጥቅም በሚጥስበት ወቅት ዜጎች መንግሥትን በፍርድ ቤት ከሰው መብትና ጥቅማቸውን ማስከበር ይችላሉ። ይህ መብት መረጋገጡ ራሱ መንግሥት ሥራውን በጥንቃቄና ሕጋዊ በሆነ አካኋን ብቻ እንዲሰራ ሊያስገድደው ይችላል።"

ይሁንና ዳኞች ወገናዊና አድሎአዊ እንዳይሆኑ በመጀመሪያ ከሕግ አውጭውና ከሕግ አስፈጻሚው ተጽእኖ ነጻ መሆን አለባቸው። ዳኞች የሥራ ዋስትናና ተመጣጣኝ ክፍያ እንዲያገኙ ያስፈልጋል። በየጊዜውም የዳኞችን አቅም የመገንባት የስልጠና ሥራ ሊሰራ ይገባል። እንዲህ ዓይነት ጥበቃዎች ያሉት የዳኝነት አካል የህዝብ መብቶችና ነጻነቶች ጠባቂ በመሆን ያገለግላል። የተጠያቂነት ስርዓትም ውጤታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ ያደርጋል። በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 78 ንኡስ አንቀጽ 1 ነጻ የዳኝነት አካል በዚህ ህገ መንግስት የተቋቋመ መሆኑን ይደነግጋል።

## 2.4. የመምረጥና ተወካይን የመጥራት መብት

የተጠያቂነት የመጨረሻው መቆጣጠሪያ መሳሪያ ነጻና ፍትሀዊ ምርጫ ነው። ነጻና ፍትሀዊ መርጫ ባለበት ሕዝቡ የሚፈልገውን ለመሾም ያላገለገለውን ደግሞ ለማውረድ የሚጠቀምበት መሰረታዊ የስልጣን ባለቤትነት ማረጋገጫው ስለሆነ ማንም ሰው ተጠያቂ እንደሚሆን አውቆ ተጠንቅቆ እንዲሰራ የሚያደርገው፣ ካልሰራ ደግሞ ከስልጣን ሊያወርድ የሚችልበት ሥርዓት ነው።

በህገ መንግስቱ አንቀጽ 12 ንኡስ አንቀጽ 3 የተደነገገው ድንጋጌ እንደሚያመለክተው ሕዝብ በመረጠው ተወካይ ላይ እምነት ባጣ ጊዜ ከቦታው ለማንሳት እንደሚችል ነው። ይህንን መሰረት አድርጎም ተመራጮች በመራጮቻቸው አመኔታ ሲያጡ ስለሚወሰድ እርምጃ በሚል ርእስ አዋጅ ቁጥር 88/89 ወጥቶአል። በአዋጁ አንቀጽ 5 እንደመለከተው አንድ ተመራጭ የመራጮች አመኔታ የለውም ሊባል የሚችለው ፡-

1. በተወከለበት የምርጫ ክልል ከሚገኙ መራጮች ከ15 ሺህ በላይ የምርጫ ቦርድ በሚያወጣው ደንብ መሠረት የይውረድልን ጥያቄ ለምርጫ ቦርድ ሲያቀርቡ፣
2. በተወከለበት የምርጫ ክልል በሚገኙ 10 ሺህ መራጮች አሳሳቢነት የምርጫ ቦርድ በሚያወጣው ደንብ መሠረት የወረዳ ምክር ቤቶች በአብላጫ ድምጽ ተወካዩ ተመልሶ እንዲጠራ ውሣኔ ያሳለፉ እንደሆነ እንደሆነ፣

3. የልዩ ምርጫ ክልል ተወካይን በተመለከተ የምርጫ ቦርድ በሚያወጣው ደንብ መሠረት የመራጮች አመኔታ ማጣቱ ሲረጋገጥ፣
4. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተመራጮች በሚያሳየው ሥነ ምግባር የወከለውን ሕዝብ በብቃት ሊወክል አልቻለም ብሎ በሁለት ሦስተኛ ድምጽ ሲወስን ይሆናል።

በዚህ አንቀጽ መሰረት ጥያቄው ተሟልቶ ሲቀርብ የምርጫ ቦርድ መመዘኛው መሟላቱን አረጋግጦ መራጩ ህዝብ እምነት አጥቶአል ብሎ ከወሰነ በእሱ ምትክ ሌላ ሰው እንዲመረጥ ይደረጋል ማለት ነው።

2.5. <u>ሌሎች ተጠያቂነትን ለማስፈን የሚረዱ መሣሪያዎች</u>

1. የመንግሥት ሠራተኞና ባለሥልጣናች የሚመሩበት የሥነ-ምግባር ደንብ መኖር፣
2. የጥቅም ግጭትን፣ የገንዘብ ጥቅምን ማሳወቂያና የንብረት ማስመዝገብ ሥርዓትን መዘርጋት፣
3. ለሙስና ወንጀል ምስክሮችና ጠቋሚዎች ጥበቃና ከለላ የሚሰጥ ሕግ ማውጣት፣

## 1.4.5.2. <u>መልካም አስተዳደርና ተጠያቂነት</u>

<u>መልካም አስተዳደር ምንድነው</u>?

መልካም አስተዳደር ማለት ቀልጣፋ የመንግስት አሰራርን ፣ ከሙስና የፀዳና ሙስና በቁጥጥር ስር የገባበት እንዲሁም ለፈጣን እድገት የተመቻቸ ሁኔታ መፍጠር ነው።

<u>የመልካም አስተዳደር መለያ ባህሪያት</u>

መልካም አስተዳደር የሚከተሉት መለያ ባህሪያት አሉት።

1. <u>አሳታፊነት</u>

   ህዝቦች ምንም ልዩነት ሳይደረግባቸው ተሳትፎ እንዲኖራቸው ማድረግ የመልካም አስተዳደር መሰረት ነው። ተሳትፎ በቀጥታ ወይም በውክልና ሊሆን ይችላል። ይሁንና በውክልና ዲሞክራሱ ከህዝቡ አናሳ የሆኑትና ለአደጋ የተጋለጡት ሁሉ ተገቢው ትኩረት አይሰጣቸውም። ስለሆነም አሳታፊነት ማለት ሁሉም ውጤታማ ተሳትፎ የሚያደርጉበት ሁኔታ ማመቻቸት ማለት ነው። ውጤታማ ተሳትፎ ለማድረግ ተሳታፊዎች መረጃ ማግኘትና ሀሳብን በነፃ የመግለፅ እንዲሁም የመደራጀት መብት መንግስት ሊያረጋግጥ ይገባል።

2. <u>የህግ የበላይነት</u>

መልካም አስተዳደር ያልወገነ የህግ አፈፃፀም እንዲኖር ይፈልጋል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ የተሟላ የሰብአዊ መብት ጥበቃን በተለይም አናሳ ቡድኖች ጥበቃ እንዲያገኙ ግድ ይላል፡፡ ያልወገነ የህግ አስፈጻሚ እንዲኖርም ነፃ ፍርድ ቤትና ከሙስና ነፃ የሆነ የህግ አስፈፃሚ ሀይል እንዲኖር የግድ ይላል፡፡

3. <u>ግልፅነት</u>

ግልፅነት ማንኛውም ውሳኔና አፈፃፀም በግልፅ የተቀመጡ የህግ ስርአቶችንና ደንቦችን ተከትሎ መፈፀም ማለት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በውሳኔው በአዎንታዊው ሆነ በአሉታዊ መልኩ የሚነኩ የህብረተሰቡ ክፍሎች መረጃ የማግኘት መብት በማመቻቸት መረጃ በቀላሉ ማግኘት የሚችሉበት አሰራር ማለት ነው፡፡

4. <u>ለህዝብ ጥያቄ ምላሽ መስጠት</u>

መልካም አስተዳደር የመንግስተ አገልግሎቶች የሚሰጡበትን የጊዜ ደገብ ማስቀመጥና በዚሁ ጊዜ ውስጥ ለህዝብ ጥያቄ ምላሽ መስጠት ማለት ነው፡፡

5. <u>የጋራ መግባባትን መፍጠር</u>

በአንድ አገር ውስጥ የተለያየ አመለካከትና አስተሳሰብ ያላቸው ሰዎች እንደሚኖሩ ይታወቃል፡፡ መልካም አስተዳደር በእነዚህ የተለያየ አመለካከትና አስተሳሰብ ባላቸው ወገኖች መካከል ወሳኝና የጋራ በሆኑት ጉዳዮች ላይ የጋራ መግባባት መፍጠር ማለት ነው፡፡

6. <u>ሁሉን አቀፍ</u>

በአንድ አገር ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች መልካምና ምቹ ሁኔታ የሚፈጠረው ሁሉም ወገን የአብሮነት የእኔነት <u>ስሜት</u> ሲሰማውና የመገለል <u>ስሜት</u> ሳይሰማው ሲቀር ነው፡፡ ይህ በተለይ ከሁሉም ለጉዳት የተጋለጡትን/ለምሳሌ ሴቶችን/ማሳተፍንና የእኔነት ስሜት እንዲኖር ማድረግን ይጠይቃል፡፡

7. <u>ውጤታማና ቆጣቢ</u>

መልካም አስተዳደር በአገሪቱ ያሉ የህዝብ ማገልገያ ተቋማቶች በአንድ በኩል የህብረተሰቡን ፍላጎት ለማርካት የሚችሉ እና በሌላ በኩል ቆጣቢ እንዲሆኑ ይጠይቃል፡፡ የቁጠባ ጉዳይ የተፈጥሮ ሀብትን በአግባቡ መጠቀም አካባቢን ከብክለት መጠበቅን ይጨመራል፡፡

8. <u>ተጠያቂነት</u>

ተጠያቂነት የመልካም አስተዳደር መሰረታዊ መገለጫ ነው፡፡ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ብቻ ሳይሆኑ የግል ሴክተሩ ውስጥ ያሉ አደረጃጀቶችም ለህዝቡና ለባለድርሻዎቻቸው ተጠያቂ መሆን አለባቸው፡፡ ይሁንና ተጠያቂነት ያለግልፅነትና ያለ ህግ የበላይነት ተግባራዊ ሊሆን የሚችል አይደለም፡፡

<u>የመልካም አስተዳደርና የዲሞክራሲ ግንኙነት</u>

ለመልካም አስተዳደር መኖር ዲሞክራሲ መሰረታዊ ቅድመ ሁኔታ ነው፡፡ ለምሳሌ አሳታፊነት፣ የህግ የበላይነት የጋራ መግባባት መፍጠር፣ተጠያቂነት ያለዲሞክራሲ ሊኖር አይችልም፡፡ ዲሞክራሲ በሌለበት መልካም አስተዳደር አይኖርም፡፡ ዲሞክራሲ በሌለበት ህዝቡ ደግፎ ሙስናን በህጋዊ መንገድ መታገልና ማጋለጥ አይችልም፡፡

ዲሞክራሲ በሌለበት ግልፅነትና ተጠያቂነት የመንግስት አሰራር መሰረታዊ መርሆዎች ሆነው በጥብቅ ተግባራዊ ሊሆኑ አይችሉም፡፡ በመሆኑም ዲሞክራሲ ለመልካም አስተዳደር ቅድመ ሁኔታ ነው፡፡

ይሁንና ዲሞክራሱ ስለአለ መልካም አስተዳደርም ይረጋገጣል ማለት አይደለም፡፡ ዲሞክራሲ ኖሮም መልካም አስተዳደር ላይኖር ይችላል፡፡ መልካም አስተዳደር በሌለበት ሙስና፣ ስልጣንን ለግል ጥቅም ማዋል ይስፋፋል፡፡ ሙስና ሙሉ በሙሉ የጠፋበት አገር ባይኖርም መልካም አስተዳደር የበላይነትን ከያዘ በቁጥጥር ስር ገብቶ በዝቅተኛ ደረጃ የሚከሰት ሊሆን ይችላል፡፡

ይሁንና መልካም አስተዳደር አለመኖሩ በሙስና መስፋፋት ብቻ የሚወሰን አይደለም፡፡ ሙስና ወይም ስልጣንን ለግል ጥቅም ማዋል በእንጭጩ ካልተገታ ዲሞክራሲያዊ ስርአቱንም አደጋ ላይ ይጥለዋል፡፡ ሙስና ካልተገታ የመንግስት ስልጣን የህዝብ መገልገያ መሆኑ ቀርቶ የጥቂት ሰዎች መጠቀሚያ ይሆናል፡፡ ህዝቡ በመንግስት ስልጣን ተጠቃሚ መሆኑ ቀርቶ ተጎጂ ይሆናል፡፡ በዚህ ሁኔታ ህዝቡ በመንግስት ስልጣን ተጠቃሚ መሆኑ ቀርቶ ተጎጂ ይሆናል፡፡ በዚህ ሁኔታ ህዝቡ ዝም ብሎ ስለማይቀመጥ የመንግስት ስልጣን ለግል ጥቅማቸው የሚገለገሉበት ቡድኖች ጥቅማቸውን ለማስጠበቅና ከተጠያቂነት ለመዳን የህዝቡን ዲሞክራሲያዊ መብቶችና

የህዝቡን ወሳኝነት የተጠያቂነት ስርአቱን ደረጃ በደረጃ መሸራረፋቸውና ማፈራረሳቸው አይቀርም፡፡

“ በኛ አገር ሁኔታ ሙስና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴው ወደ ምርትም ልማት ከማተኮር ይልቅ ወደ ማጭበርበርና የአየር ባየር ንግድ እንዲያዘነብል በማድረግ ልማታችንን ክፉኛ ሊጎዳ ይችላል፡፡ የመንግስት አሰራር በአድልዎና ጉቦ ተጨማልቆ መንግስት በልማት ተግባር ላይ በጎ አስተዋፅኦ ማድረግ ተስኖት የልማት ችግራችን የመፍትሄ አካል መሆኑ ቀርቶ ዋነኛው ችግር ሊሆን ይችላል፡፡ መንግስት ህዝባዊ አገልግሎት የሚበረከትበት ሳይሆን ዝርፊያ የሚከናወንበት መድረክ ይሆንና የመንግስት ስልጣን ለመያዝ የሚደረግ የሞት ሽረት ትግል እንዲሆን ስለሆነም ዲሞክራሲ ከስረ መሰረቱ እንዲናድ በር ሊከፍት ይችላል፡፡ በእነዚህ ምክንያቶች ሁሉ ሙስና ልማታችንን አደናቅፎ የዲሞክራሲ ስርአታችንን ከውስጡ እንዲበሰብስ አድርጎ የልማትና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ተስፋችንን ሊያጨልም ይችላል፡፡ በመሆኑም ሙስናን በመዋጋት መልካም አስተዳደርን ማስፈን የዲሞክራሲ ስርአት ግንባታና የልማት ራእያችን እውን እንዲሆን የማድረግ ጉዳይም ጭምር ነው፡፡

መንግስት አገልግሎቱን ቀልጣፋ በሆነ አኳኋን እንዲሰጥ ማድረጉ ወይም አለማድረጉ ባለንበት አለም በኢኮኖሚ ተወዳድሮ ለማሸነፍ ወይም ለመሸነፍ ምክንያት ከሚሆኑት ዋነኛ ጉዳዮች አንዱ ነው፡፡ መንግስት እንደእኛ ባለው አገር ላይ የላቀ ልማታዊ ሚና መጫወት አለበት፡፡ እንደዚህ አይነቱን ሚና ለመጫወት የሚችለው ከሁሉም ነገር በፊትና ከሁሉም ነገር በላይ ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት ሲችል ነው፡፡ እንደኛ ባሉ አገሮች ህዝቡ ዲሞክራሲን የሚመኝበት አንዱ መሰረታዊ ምክንያት ፍትሃዊና ቀልጣፋ የመንግስት አገልግሎትን ለማግኘት ነው፡፡ እንደዚህ አይነት አገልግሎት ካላስገኘ በዴሞክራሲያዊ ስርአት ላይ ያለው እምነት በከፍተኛ ፍጥነትና ደረጃ ሊሸረሸር እንደሚችል የበርካታ አገሮች ልምድ ያረጋገጠው ነው፡፡ በመሆኑም ፍትሃዊና ቀልጣፋ መንግስታዊ አገልግሎት በማቅረብ መልካም አስተዳደርን ማስፈን የልማትና የዲሞክራሲ ስርአት ግንባታ ራእያችንን እውን ለማድረግ ተፈላጊ ጉዳይ ነው፡፡

ስለሆነም በአገራችን ሁኔታ መልካም አስተዳደርና ዲሞክራሲ ተያያዥና ሊነጣጠሉ የማይችሉ ናቸው፡፡

በህገ መንግስቱ የህዝቦች ቀጥተኛ ተሳተፎ፣ የህግ የበላይነት፣ተጠያቂነት በግልፅ ተደንግገዋል፡፡ ስለሆነም ህገ መንግስቱ የመልካም አስተዳደር መርሆዎችንም ያካተተ

ነው። ስለሆነም እነዚህን የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች መተግበር መልካም አስተዳደርን ማስፈን ማለት ነው። በሌላ በኩል የመልካም አስተዳደር እጦት ወይም አለመኖር በአንድ ወይም በሌላ መልኩ ህገ መንግስቱን ስራ ላይ አለማዋል ማለት ነው።

<u>መወያያ ጥያቄዎች</u>

1. በተወካዮች ምክር ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ የተወካዮች ምክር ቤት የአስፈጻሚውን እንደሚቆጣጠር ተመልክቶአል። ከዚህ በመቀጠልም እርምጃ እንደሚወስድ ተመልክቶአል። ተወካዮች ምክር ቤት ምን አይነት እርምጃ ሊወስድ ይችላል; ሚኒስትር ከስልጣን ይውረድ ብሎ ሊወስን ይችላል ወይ?
2. የፀረ ሙስና ኮሚሽኖች አስፈጻሚውን ለመቆጣጠር ተብለው የተቋቋሙ ሆነው ሳለ ለአስፈጻሚው ተጠሪ መሆናቸው ተገቢ ነው ወይ?
3. የመንግሥት ሠራተኞች መረጃ መስጠት አለባቸው ይህንን ያለማድረግ ያስቀጣል። ይሁንና አንድ የመንግስት ሰራተኛ መረጃ ለመስጠት አለቃዩ መፍቀድ አለበት ይላል። ለአፈጻጸም አያስቸግርም ወይ;
4. ተመራጭን እምነት ማጣት በሚመለከት ከ15 ሺህ ሰው በላይ ከፈረመ ሊነሳ እንደሚችል ተመልክቶአል። በምርጫ ማግስት እንዲህ አይነት ጥያቄ በተሸነፈው ተመራጭ ወገኖች ተፈርሞ ቢቀርብ ምን ይደረጋል;

## 1.5. <u>የሕገ-መንግሥቱ አተረጓጎም</u>

**የትምህርቱ ዝርዝር ዓላማ፡**

ከዚህ ክፍል ትምህርት በኃላ፡

- ☐ የኢፌድሪ ህገ-መንግስት አተረጓጐም ሥርዓት ይለያሉ።
- ☐ ህገ-መንግስትን በመተርጐም ሂደት የፍ/ቤቶች ሚናን ይለያሉ።
- ☐ ስለአገራት ተርጓሚ አካል ሕጋዊነት በቂ ገለጻ ያደርጋሉ።
- ☐ ለህገ-መንግስት ትርጉም ምክንያት የሆኑ ነገሮችን ይዘረዝራሉ።
- ☐ ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያገኙ የሕገ መንግስት መተርጎሚያ መርሆዎችን ምንነት ይገልፃሉ።

- ☐ ህገመንግሥቱን በመተርጎም እና በማስፈጸም መካከል ስላለው ልዩነት ይገልፃሉ፡፡

**ውድ ሰልጣኞች፡**

- ☐ የኢፌዲሪ ህገ-መንግስት የመተርጐም ስልጣን ለፌዴሬሽን ምክር ቤት መስጠቱ ከሌሎች አገሮች ጋር ሲነፃፀር የሚደገፍ ነው? ለምን?
- ☐ ህገ-መንግስት በመተርጐም ወይንም በማስፈፀም ሂደት ውስጥ የፍ/ቤት ሚና ምንድ ነው?
- ☐ ከፍ/ቤት ጉዳዮች እንዴት ለህገ-መንግስት አጣሪ ጉባኤ ይመራል?ወይንም ይለካል?

በዓላማችን ያለው ሕገ መንግሥት የመተርጐም ሥርዓት በሁለት ዋና ዋና ሥርዓቶች ይከፈላሉ፡፡ ይኸውም የተማከለ ሕገ መንግሥትን የመተርጐም ስርዓት (Centralized) እና ያልተማከለ (diffused) ወይንም (Decentralized) ሥርዓት በመባል ይታወቃሉ፡፡

### *ሀ. <u>ያልተማከለ ህገ-መንግስት የመተርጐም ስርዓት/Decentralized system/</u>*

ካልተማከለው ህገ መንግስት የመተርጐም ሥርዓት ብንጀምር ይህ ስርዓት የአሜሪካ ሥርዓት (American Model) ተብሎ ይታወቃል፡፡

ባልተማከለ ሕገ መንግሥትን የመተርጐም ሥርዓት ሕገ መንግሥትን የመተርጐም ሥልጣን የመደበኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ ማለትም መደበኛ ፍርድ ቤቶች ማንኛውንም ሕግ ወይንም የባለስልጣን ውሳኔ ከህገ መንግሥቱ ጋር የማይጣጣም ሆኖ ሲያገኘው ተፈፃሚነት እንዳይኖረው የሚያደርግበት ስልጣን ይሰጠዋል፡፡
ያልተማከለው ሥርዓት የሚከተሉ አገራት ስር <u>አሜሪካ</u>፣ <u>ህንድ</u> እና <u>ካናዳ</u> የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

### *ለ. <u>የተማከለ ህገ-መንግስትን የመተርጐም ስርዓት/Centralized System/</u>*

የተማከለ ሕገ መንግሥትን የመተርጐም ሥርዓት ከሁለተኛው የአለም ጦርነት በኃላ በአውስትራሊያዊው ምሁር ሐንስ ኬልሰን በአውስትራሊያ እየዳበረ የመጣ ሥርዓት

በመቀጠልም ከእንግሊዝ እና ከፈረንሳይ በስተቀር በሌሎች አውሮፖ አገሮች ተቀባይነት ያገኘ ሥርዓት ነው፡፡ ይህ ስርዓት የሕገ መንግሥት ፍርድ ቤትን የሚጠቀም ሥርዓት ነው፡፡ አብዛኛውን ጊዜ የጀርመን የሕገ መንግሥት ፍርድ ቤት እንደአብነት ይጠቀሳል፡፡ በተማከለው ሥርዓት ስር ጀርመን፣ አውስትራሊያ የምስራቅ እና የሴንትራል አውሮፖ አገራት እና ደቡብ አፍሪካ ይገኙበታል፡፡ በነዚህ አገሮች የሕገ መንግሥት ፍርድ ቤት ሕገ መንግሥትን የመተርጐም ሥልጣን አሏቸው፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት ስርዓት ውጪ የሆኑት አገራቸውን የሕገ መንግሥት ታሪካዊ እድገት መሠረት በማድረግ ከሁለቱም የማይመደቡ ህገ-መንግስት የመተርጐም ስርዓት ስር የሚገኙ አገሮች አሉ፡፡ በኢትዮጵያ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ሕገ መንግሥትን የመተርጐም ሥልጣን አለው፡፡

ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከተው በተማከለው ስርዓት የህገ መንግስት ፍርድ ቤቶች የሥልጣናቸው ገደብ ህገ መንግስትን ብቻ መተርጐም ነው፡፡ ማለትም ህገ መንግስትን የመተርጐም ስልጣን የፍርድ ቤቶች ሳይሆን የህገ መንግሥት ፍርድ ቤቶች ብቻ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር ይህን ስላደረጉ በእነዚህ አገራት የፍርድ ቤት ነፃነት አለ ወይም የለም ለማለት አይቻልም፡፡ የፍርድ ቤት ነፃነትና ሕገ መንግሥትን በመተረጐም ረገድ ፍርድ ቤት ምን መስራት እንዳለበትና እንደሌለበት የሚታዩ ፅንሰ ሐሳቦች መሆናቸው መረሳት የለበትም፡፡

## 1.5.1. *ህገ መንግስት ለምን ይተረጐማል?*

ሕገ- መንግስትን ጨምሮ ማንኛውም ህግ ሲተረጐም በዘፈቀደ የሚተረጐም አይደለም፡፡ ሕግን መተርጐም የራሱ የሆነ የመተርጐም ስርዓት፣ ዘዴ ወይንም ስነ ምግባር አለው፡፡ ሕግን በተለይም ሕገ - መንግስትን የመተርጐም ስልጣን የተሰጠው አካል በፈለገበት ወቅትና በፈለገበት መንገድ የሚተረጉመው አይደለም፡፡ መተርጐም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እና በመተርጐሙም ሂደት ተቀባይነት ባለው የመተርጐም መርህ ፣ ዓይነት እና ዘዴ ብቻ ይሆናል፡፡

ማናቸውም የመተርጐም ተግባር መብትን እንዳይጥስ ወይም ከታሰበለት ትርጉም ተቃራኒ የሆነ ትርጐም እንዳይሰጥ ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚጠይቅ ነው፡፡ ይህ ካልሆነ የመተርጐም ስም መያዝ ይቻል ይሆናል እንጂ ትክክለኛ የትርጉም ስራ አለማለት ያስቸግራል፡፡

የህገ-መንግስትን ትርጉም ስንመለከት፣ሕገ-መንግስት ከመጀመሪያው የተለየ የህግ ሰነድ በመሆኑ ለማዘጋጀት፣ ለማጽደቅ ፣ ለማሻሻል ከፍተኛ ጥንቃቄ እንደሚፈልግ ሁሉ በመተርጐምም ወቅት የተለየ ጥንቃቄን ይጠይቃል፡፡ ለዚህ ነው ከላይ እንደጠቀስነው የተለያዩ አገራት ሕገ መንግስትን የመተርጐም ስልጣን ለተለያዩ አካላት የሚሰጡት፡፡

- ህገ መንግስትን መተርጐም ማለት ትርጉምን የመፈለግ ተግባር ማለት ነው፡፡
- ይህን ተግባር አንዳንዶች **አርት** ነው ሲሉ ሌሎች ሳይንስ ነው ሲሉ ሌሎች ሁለቱም ነው ይላሉ
- በመቀጠልም ሕገ መንግስትን መተርጐም ማለት የሕገ መንግስት ትርጉምን የመገንባት ወይም የመወሰን ሳይንስ ነው ይላሉ፡፡

ትርጉም የሚያስፈልገው ህገ-መንግስት ወይም ህግ ግልጽ ሳይሆን ሲቀር ነው፡፡ ለህገ-መንግስት ደግሞ ግልጽ ስላልሆነ ብቻ ሳይሆን ግልጽ ሆኖም መፈጸም የግድ በሚልበት ወቅት ሕገ-መንግስትን መተርጐም ይጠይቃል፡፡ አንድ ህግ ትርጉም የሚፈልገው አሻሚ፣ከሕገ-መንግስት ጋር ግጭት ሲፈጠር ወይም መጣጣም ሳይኖር ሲቀር ነው፡፡ የህገ መንግስት ጉዳዮች አሻሚ ናቸው፣ ግጭት አለ ወይም አይጣጣምም የማለት ስልጣን በኢትዮጵያ የተሰጠው ሕገ መንግስትን የመተርጐም ስልጣን ለተሰጠው የፌዴሬሽን ምክር ቤት ነው፡፡

ማናቸውም ፣ ህግ ወይም ፣ ህገ-መንግስት የመተርጎም ሥራ፣ አንድ መሠረታዊ ዓላማ እንዳለው ከላይ ተገልፆል፡፡ ከዚህ አንፃር ህገ መንግስት ትርጉም የሚሰጠው

## *ሀ. ግልፅ ለማድረግ (Clarity)*

ህገ መንግስት በተፈጥሮ ዝርዝር ሕግ ሳይሆን ጥቅል ህግ እና መሠረታዊ መርህን የሚደነግግ የህጐች ሁሉ የበላይ ሕግ ነው፡፡ ማለትም ህገ መንግስት ጥቅል ህግ

እንደመሆኑ መጠን እንደሌሎች ህጐች በጣም ግልፅ ላይሆን ይችላል፡፡ ግልፅ ያለመሆን የቃላት፣ የአገላለጽ ወይንም የሕጉ መንፈስ ግልጽነትን የሚመለከት ሊሆን ይችላል፡፡

ህገ መንግስት ዝርዝር እና ተራ ከሆኑ መርሆዎች ይልቅ ውስብስብና አጠቃላይ በሆኑ ጽንሰ ኃሳቦች የተሞላ ነው፡፡ የህገ መንግስት ቋንቋ አጠቃላይ ከመሆኑም ባሻገር የቃላቶቹ ተፈጥሮ እና አቀማመጥ ህገ መንግስትን ከሌሎች ህጐች በእጅጉ ይለየዋል፡፡ እንዲሁም የስነ ቋንቋ ጠበብቶች እንደሚናገሩት ቃላትም ሆነ ቋንቋ ከጊዜ ወደ ጊዜ ያድጋል፣ ይሻሻላል፣ ይቀየራል፡፡ ስለሆነም እነዚህን እና እነዚህን የመሳሰሉትን ግልፅ ለማድረግ ሕገ-መንግስትን የመተርጐም ስልጣን የተሰጠው አካል የህግ መንግስትን የመተርጐም ዘዴዎች ወይም መርህን በመጠቀም ግልፅ ለማድረግ ህገ መንግስትን ይተረጉማሉ፡፡

## ለ. ግጭት/ያለመጣጣም/ /Inconsistency/

አንዳንድ ጊዜ የተለያዩ የህገ መንግስት አንቀጾች ወይንም ምዕራፎች አንዳቸው ከአንዳቸው ላይጣጣሙ ወይም በመከካላቸው ግጭት ሊፈጠር ይችላል፡፡ ይህ ያለመጣጣም ወይም ግጭት እንዲጣጣም የሚደረገው ሕገ መንግስቱን በመተርጐም ይሆናል፡፡ ይህ ብቻም ሳይሆን ህገ መንግስት በአብዛኛው የአለማችን አገሮችም ሆነ በኛም አገር የህጐች ሁሉ የበላይ ህገ እንደሆነ አስቀድመን ተመልክተናል፡፡ይህ የበላይነት የሚረጋገጠው ከህገ መንግስት ጋር የሚቃረን ህግ፣ ልማዳዊ አሰራር፣ የመንግስት ውሳኔ ወዘተ ሳይኖር ሲቀር ነው፡፡ ካለም ዋጋ የማይኖረው ሲሆን ነው፡፡ ስለዚህ ይህን የግጭት መኖር ወይም ያለመኖር ለማረጋገጥ ጉዳዩን በመመርመር ሕገ መንግስትን የመተርጐም ስልጣን በኢፌድሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 84(2) መሠረት ለፌዴሬሽን ም/ቤት ተሰጥቷታል፡፡

እስከ አሁን ያሉትን ውሳኔዎች ስንመለከት የሕጐች ሕገመንግስታዊ መሆን እና አለመሆን የሚመረመረው በአንቀጽ 83 (1) ስር እንደተደነገገው የሕገ መንግስት ጉዳይ ክርክር ሲነሳ (Concrete review) ማለትም ጉዳዮች ወይም ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸው ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ሲያቀርቡ ነው፡፡ በአጠቃላይ በሕጐችና በሕገ መንግስቱ መካከል ግጭት ስለመኖሩ የህገ መንግስት ጉዳይ ክርክር ሲቀርብ የፌዴሬሽን ምክር ቤት

በኢፌድሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 83(1) መሠረት ህገ መንግስትን በመተርጐም ውሳኔ ይሰጥበታል፡፡

በመሆኑም ከህገ መንግስቱ መርህ ጋር የሚቃረን ውሳኔ፣ ህግ፣ ወዘተ ሲኖር በህገ መንግስቱ አንቀጽ 83 (1) እንዲሁም አንቀጽ 9(1) እና (2) እና በአዋጅ ቁጥር 251/93 መሠረት ዋጋ የማይኖረው ስለመሆኑ ውሳኔ የመስጠት ስልጣን የፌዴሬሽን ምክር ቤት ነው፡፡

ሐ. <u>ክፍተትን ለመዝጋት</u>

የህገ መንግስት ሰነድ በጣም በጥቅል አቀማመጥ ከመቀመጡ የተነሳ ህገ መንግስት የተወሰኑ ጉዳዮችን ብቻ ሊዘረዝር ይችላል፡፡ በአብዛኛው ጉዳዮች መርህን ብቻ ሊያስቀምጥ ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ ዝርዝር ጉዳዮችን ባይዝም አጠቃላይ ይዘቱ ወይንም መንፈሱን ከሕገ መንግስቱ በመረዳት ህገ መንግስቱን መተርጐም ይቻላል፡፡ ለአብነት ያህል አጠቃላይ የኢኮኖሚ፣ የማህበረዊ፣ ባህላዊ ፖሊሲዎች ህገ መንግስታችን ከአንቀጽ 85 ቀጥሎ በምዕራፍ አስር ስር ተለይተው በአጭሩ ተቀምጠዋል፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ ድንጋጌዎች በጣም ውስንና ጥቅል ሆነው በአጠቃላይ አቀማመጥ የተቀመጡ ናቸው፡፡ ስለሆነም ከነዚህ መርህ በመነሳት በዝርዝር ያልተቀመጡና ያልተሸፈኑትን ጉዳዮች አጠቃላይ የሰነዱን ይዘት በመፈለግ የመተርጐም ስልጣን ያለው አካል ሊተረጉም ይችላል፡፡ በእርግጥ ሕገ መንግስት መሻሻል እንደሚችል ሁሉ በቀላሉና በማናቸውም ጊዜ የሚሻሻል ባለመሆኑ በያንዳንዱ አገራት ነባራዊ የእድገት ሂደት በሕገ መንግስት ያለተሸፈኑ ጉዳዮች ትርጉም እየተሸፈኑ ይሔዳሉ፡፡ <u>ለምሳሌ</u>፡- በአሜሪካን ህገ መንግስት ውስጥ ስለ “Judicial Review” የሚናገር ግልፅ ድንጋጌ ባይኖርም በሂደት ይሀ መርህ በፍርድ ቤት በመዳበርና በማደግ እንደ አንድ ተቀባይነት ያገኘ የህገ መንግስት መርህ በአገሪቱ በማገልገል ላይ ይገኛል፡፡

## 1.5.2 <u>ሕገ-መንግስትን የመተርጐም ዓይነቶች</u>

ህገ-መንግስትን የመተርጐም ዓይነቶች በመደበኛ፣መደበኛ ያልሆነ እና ኢ-መደበኛ በማለት እንደቅደም ተከተላቸው “<u>Formal ”</u>, "<u>Informal"</u> እና <u>Non-formal</u> ተብለው ይታወቃሉ፡፡

መደበኛ ማለት በኛ አገር በፌዴሬሽን ምክር ቤት የሚሰጠው የህገ መንግስት መደበኛው ትርጉም ነው፡፡ መደበኛ ያልሆነ የሚባለው ሕገ መንግስትን ለመፈፀም በእለት ተዕለት ተግባር የመንግስት አካላት ህገ መንግስቱን ለመፈፀም የሚያከናውኑት ተግባር ነው፡፡ ሌላው ፍርድ ቤቶች ለምሳሌ ዋስትናን የሚመለከቱ ውሳኔዎች፣ በመያዝ ትዕዛዝ ፣ የንብረትን መብት በማስጠበቅ ወዘተ የሚወስኑ የፍርድ ቤት ውሳኔዎች ኢ-ቀጥተኛ ውሳኔ ነው፡፡

### 1.5.3 የህገ-መንግስት አተረጓጐም መርሆዎች/ስልቶች/

ሕገ-መንግስትን ሲተረጐም እራሱን የቻለ መርህ/ስልቶች/አሉት፡፡ ስለሆነም ስለ ህገ-መንግስት ትርጉም ሥራ ሲነሳ እነዚህን ስልቶች ጠንቅቆ ማወቅ ያስፈልጋል፡፡

በተለይም ህገ-መንግስት ተራ ሰነድ ባለመሆኑ፣የህግ ሰነድ ብቻ ሳይሆን የፖለቲካ ሰነድ ወይም የህዝቦች የቃል ኪዳን ሰነድ በመሆኑ በሚተረጉምበት ወቅት በርካታ ጉዳዮችን ከግምት ማስገባት ይጠይቃል፡፡ ይህ ብቻም ሳይሆን ህገ-መንግስት በአጠቃላይ አነጋገር ለረጅም ዘመናት እንዲሰራ ተደርጐ የሚደነገግ ስለሆነ ተቀባይነት ያላቸውን የህገ-መንግስት የመተርጐሚያ መርሆዎችን በማወቅ ህገ-መንግስትን መተርጐም አማራጭ የለውም፡፡

እነዚህ ስልቶች እንደየጉዳዩ ዓይነት፣እንደድንጋጌው ምዕራፍ ወይም ክፍል ልዩነት ወዘተ ሊለያይ ወይም አንደኛው ስልት ከሌላኛው ስልት ጋር ተቀላቅሎ ህገ-መንግስትን መተርጐም ይቻላል፡፡ ተቀባይነት የአገኙት ስልቶች ዋና ዋናዎቹ ወደ ሰባት የሚከፈሉ ሲሆን ሌሎች ወደ አራት የሚጠጉ አማራጮች አሉ፡፡

*እነሱም፡-*

“Tectualism,””Orginalism””Doctrinalism”,Developmentalism”,”philosophic approach”, ”Systemic” እና,”Balancing”የሚባሉ ሲሆን እንደ አማራጭ የሚወስዱት ደግሞ ”Strict vs Liberal,” ”Judical activism vs Judical self-restraint”, substance vs procedure እና “Interpretive vs Non Interpretive”ይባላሉ፡፡

የእነዚህን ስልቶች ምንነት በዝርዝር እና የፌዴሬሽን ምክር ቤት ውሳኔ በሰጠባቸው ጉዳዮች ላይ የትኞቹ ስልቶች በየትኞቹ ጉዳዮች ላይ ስራ ላይ እንደዋሉ በገለፃ ወቅት

የሚቀርቡና በመወያያ ጥያቄዎች ጭምር በመታገዝ ከተመለከትናቸው በኂላ ለሙከራ ጥያቄዎቹ መልስ ሊሆኑ የሚችሉት በመጨረሻ ላይ የሚቀርቡ ይሆናሉ።

## 1.5.4.ህገመንግሥቱን በመተርጎም እና በማስፈጸም መካከል ስላለው ልዩነት

ሕገ መንግስት መተርጎም በፓርላማ የወጡት ህጐችና የመንግስት አካላት ውሳኔዎች ሕገመንግስቱን መቃሬን አለመቃሬናቸውን የመጨረሻ ውሳኔ የመስጠትን የሚመለከት ሲሆን ማስፈፀም ግን ማንኛውንም ህግ ሲተረጉሙ የሉአላዊነት መገለጫ የሆነው ህገመንግስትን መሰረት ባደረገና የህገመንግስቱን ዲሞክራሲያዊ መርሆዎች በሚያስፈጽም መልኩ ተግባራዊ ማድረግ የዲሞክራሲያዊ ስርአት ምሰሶዎች የሆኑት ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች በሌሎች አካላት ሲጣሱ እነዚህ መብቶች የጣሱት ወገኖችን ተገቢውን ቅጣት እንዲያገኙ ወይም ካሳ እንዲከፍሉ በማድረግና የሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የመጣስ ተግባራትን እንዳይፈጸሙ በማገድ ሕገመንግስቱን በዕለት ተእለት ተግባር መጠቀምን የሚመለከት ተግባር ነው።

### 1.5.4.1. ህገ መንግስትን የመተርጐም ሂደትና የፍርድ ቤቶች ሚና

ከላይ በግልጽ እንደተጠቀሰው የኢፊድሪ ህገ መንግሥት አንቀጽ 83(1) እና 62(1) መሠረት ህገ መንግስትን የመተርጐም ስልጣን የተሰጠው ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ነው። ለዚህም ዋነኛው ምክንያት ህገ መንግስት ተራ ውል ባለመሆኑ እና የተለዩ ጥንቃቄ የሚፈልግ የብሔር ብሔረሰቦችን ህዝቦች የቃል ኪዳነ ሰነድ መሆኑ ነው።ከዚህ አንጻር በዚህ ጽሑፍ በሌላ ስፍራ እንዳየነው አሳማኝ ከሆኑ ህጋዊ ምክንያቶች መሠረት በማድረግ እንደ አሜሪካ ያሉ አገሮች የህገ መንግስት መተርጐም ስልጣን ለመደበኛው ፍርድ ቤት ሲሰጡ እንደ ጀርመን ያሉ አገሮች ሕገ መንግስትን ለብቻ ለሚተረጉሙ ህገ መንግስታዊ ፍርድ ቤቶች ይሰጣሉ።

በእኛም አገር የፌዴሪሽን ምክር ቤት የላይኛው ምክር ቤት ከሕግ ባለሙያ በመታገዝ በሕገ መንግሥት ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ይሰጣል። ወይንም የመተርጐም ስልጣን ተሰጥቶታል። በመሆኑም የህገ መንግስትን ትርጉም ለፍርድ ቤት መተውም ሆነ ለፍርድ ቤት ያለመተው እንደተዓምር የሚቆጠር ሳይሆን በዓለማችን አገሮች ልምድ

ተቀባይነት ያገኘ ጉዳይ ነው፡፡ ይልቁንም መሠረታዊው ነገር ከሌላኛው አንዱ ሲመረጥ ምክንያቶቹ፣ የአገራት የታሪክ እድገት፣ የህገ መንግሥት ትርጉም ታሪካዊ አመጣጥን እና የህገ መንግስቱን የተለዩ ባህሪ ከግምት ማስገባትን ይጠይቃል፡፡

ከዚህ አነፃር የኢፌድሪን ህገ መንገሥት በመተርጐም ሂደት የፍርድ ቤቶችን ሚና በአጭሩ እንደሚከተለው ማየት ይቻላል፡፡

1. ፍርድ ቤቶች በአንቀጽ 9(1) ስር የተጠቀሰው የህገ መንግሥት የበላይነት የማረጋገጥ ግዴታ እና ሕገ መንግስቱን በአንቀጽ 9(2) ስር እንደተጠቀሰው የማክበርና የማስከበር ግዴታ ተጥሎባቸዋል፡፡

   ይህ ደግሞ እንዲሁ አይመጣም፡፡ ፍርድ ቤቶች በሚሰጡት ውሳኔ ይህን ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል፡፡

   > ***ለምሳሌ*** ፡- ፍርድ ቤቶች በሚቀርቡላቸው ማንኛውም ጉዳይ ህገ መንግሥቱን የሚቃረን ውሳኔ መስጠት አይጠበቅባቸውም፡፡ ይህን ለማድረግ ደግሞ አጠቃላይ የህገ መንግስቱን መንፈስ እና ፍላጐት ወይንም ግብ ጠንቅቆ ማወት ይጠይቃል፡፡

   - ✓ በሌላ በኩል ከላይ እንደጠቀስነው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያወጣው ህግ ከህገ መንግስቱ ጋር የሚቃረን ከሆነ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ተፈፃሚነት እንዳይኖረው ማዘዝ እንደሚችል ተመልክተናል፡፡ ይህ ከመደረጉ በፊት ማለትም ከመሻሩ በፊት ይህ ህግ ለፍርድ ቤት እንዲፈፀም ቢቀርብ ፍርድ ቤት ከሕገ መንግሥቱ ጋር የሚቃረን መሆኑን ከአረጋገጡ ከመፈፀም መቆጠብ እንዳለባቸው አከራካሪ አይመስልም፡፡

2. በአንቀፅ 13(1) መሠረት በማናቸውም ደረጃ የሚገኙ የፌዴራል መንግስት የክልል የሕግ አውጪ የሕግ አስፈፃሚ እና የዳኝነት አካሎች መሠረታዊ የሰው ልጆች መብቶችና ነፃነቶች (ሰብአዊ መብቶች) የማክበርና የማስከበር ኃላፊነትና ግዴታ አለባቸው፡፡

በዚህ ድንጋጌ መሠረት ፍ/ቤቶች ሰብአዊ መብቶችን በእለት ተእለት ተግባር፣ በችሎት አመራር ፣በውሳኔ (በፍትህ) አሰጣጥ ሂደት የማክበርና የማስከበር ግዴታ አለባቸው፡፡

3. ከዚህ ባሻገር ፍ/ቤቶች በፓርላማ የወጡትን ህጐች ህገ መንግስታዊነት የማረጋገጥ ስልጣን አላቸው፡፡ ይህ ብቻም ሳይሆን የመንግስት አካላት ውሳኔ፣ የአስተዳደር ውሳኔዎችን የመዳኘት ስልጣኑ የማየት አሉአቸው፡፡ ለምሳሌ አንድ የመንግስት መ/ቤት የአንድን ሰው የሥራ ፍቃድ ቢሰርዝ እና ውሳኔው ህገ-መንግስቱን የሚቃረን ሆኖ ከተገኘ ለፍ/ቤት አመልክቶ ጉዳዮ ሊዳኝ ወይንም ውሳኔው ሊታይ (review) ሊደረግ ይችላል፡፡ በተሻሻለው የደቡብ ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 43/…. ላይ የአስተዳደር ውሳኔዎች ህገ መንግስታዊነት ማረጋገጥ የፍርድ ቤቶች ስልጣን መሆኑ በግልፅ ተደንግጓል፡፡

በህገ-መንግስት ጉዳዮች ወይንም ክርክሮች ላይ የመጨረሻ ውሳኔ የመስጠት ስልጣን የተሰጠው ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ነው፡፡

በሕገ-መንግስት ጉዳዮች ላይ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ብቻ ሳይሆን በአዋጅ ቁጥር 251/93 አንቀፅ 11(1) መሠረት በሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት እንደሚኖረው ያሳያል፡፡

ከዚህ አንፃር እንደ ማስተማሪያና የመጀመሪያ ውሳኔዎች ከሚታዩት ውስጥ የእነ ቢያድግልኝ መለስ ጉዳይ፣ በቤንሻንጉል የሚኖሩ ሌሎች ብሔረሰቦች ጉዳይ፣ የስልጤ ህዝቦች ጉዳይ፣ የባንክ ሰራተኞች የዋስትና ጥያቄ ጉዳይ እና ሌሎች ጉዳዮች በዚህ ሞጁል ለውይይት በሚያመች መልክ በክንዋኔ ንዑስ ክፍል ስር ቀርቧል፡፡

## *1.5.4.2. የህገ- መንግስት አጣሪ ጉባኤ ሚና*

የህገ-መንግስት አጣሪ ጉባኤ በኢፌዴሪ ህገ-መንግስት አንቀጽ 82 (1) ስር የተቋቋመ ጉባኤ ነው፡፡

ይህ አካል የህገ-መንግስታዊ ጉዳዮች ክርክር ሲነሳ በመመርመር ለፌዴሬሽን ምክር ቤት የውሳኔ ኃሳብ የሚያቀርብ ነው፡፡ ቢሆንም የመጨረሻ ውሳኔ የመስጠቱ ስልጣን የፌዴሬሽን ምክር ቤት ነው፡፡ ማለትም ምክር ቤቱ የቀረበለትን ሙያዊ ኃሳብ የመቀበል ፣ ያለመቀበል ወይንም የማሻሻል ስልጣን አለው፡፡

የጉባኤው ቁጥርና ስብጥር በህገ-መንግስቱ አንቀፅ 82 መሠረት አስራ አንድ አባላት ያሉት ሲሆን የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ኘሬዝዳንት እና ምክትል ኘሬዝዳንትን ጨምሮ ስምንቱ የሕግ ባለሙያዎች ሲሆኑ ፤የተቀሩት ሶስት አባላት ከፌዴሬሽኑ አባላት የሚወከሉ ናቸው፡፡

በአንቀፅ 84 ስር ጉባኤውን የሚመለከቱ ስልጣንና ተግባራት እና የውሳኔ አሰጣጥ ሥርዓት መርህ የተቀመጠ ሲሆን ዝርዝር ስልጣንና ተግባራትና ጉባኤው የሚመራበት ሥርዓት በአዋጅ ቁጥር 250/93 አንቀፅ 6፣ 17፣30 እና 31 ስር በግልፅ ሰፍሮ ይገኛል፡፡

### *1*.5.4.3 <u>የኢፊድሪ ህገ መንግስት አተረጓጐም ሂደት እና የፌዴሬሽን ምክር ቤት ሚና</u>

በኢፊድሪ ሕገ መንግስት መግቢያ ውስጥ በግልፅ እንደሰፈረው ሕገ መንግስት የኢትዮጵያ ብሔሮች፡ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች የቃል ኪዳን ሰነድ ነው፡፡

በአንቀጽ 8(1) ስር የኢትዮጵያ ብሔሮች ፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች የሉዓላዊ ስልጣን ባለቤቶች ሲሆኑ ህገ መንግስቱ የሉዓላዊነታቸው መገለጫ እንደሆነ በአንቀጽ 8(2) ስር ተጠቅሷል፡፡

በአንቀፅ 61(2) መሠረት ሕገ መንግሥትን የመተርጐም ስልጣን ያለው የፌዴሪሽን ምክር ቤት የተመሰረተው ከላይ ከተጠቀሱት የኢትዮጳያ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ህዝቦች መሆኑ በአንቀጸ 61(1) ስር ተጠቅሷል፡፡

እንደሚታወቀው ህገ መንግስት ተራ ሰነድ ወይንም ተራ ህግ ሳይሆን በኢትዮጵያ የብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች የቃል ኪዳን ሰነድና የህጐች ሁሉ የበላይ ሕግ ነው፡፡ ሕግ ቢቻም ሳይሆን የጋራ ፍላጐታቸውም መግለጫ የሕግና የፓለቲካ ሰነድ ነው፡፡

ስለሆነም በማርቀቅና በማሻሻል ሂደት የተለዩ ጥንቃቄን እንደሚጠይቅ ሁሉ የመተርጐሙም ስልጣን ተለይቶ ለተለየ አካል የተሰጠው፡፡

በአንቀጽ 84(2) መሠረት የፌዴሬሽን ምክር ቤት ሕገ መንግሥትን በመተርጐም የፌዴራሉም ሆነ የክልል ሕጐች ከህገ መንግሥቱ ጋር የማይቃረኑ መሆናቸው እና አለመሆናቸው ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ የፌዴሪሽን ምክር ቤት ስልጣንና ተግባርን ግልፅ ለማድረግ በወጣው አዋጅ ቁጥር 251/1993 ዓ.ም በትርጉም ክፍል ስር ሕግ ማለት ማናቸውም በፌዴራሉም ሆነ በክልል  አካላት የወጡትን አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ጭምር እንደሚያጠቃልል ያሳያል፡፡ ማናቸውም ቀዳሚ (Primary) እና ተከታያቸው (Subordinate) ሕጐች ከህገ መንግስቱ ጋር የማይጋጭ ስለመሆናቸውና አለመሆናቸው የማረጋገጥ ስልጣን የተሰጠው ለፌዴሪሽን ምክር ቤት ነው፡፡

በአንቀጽ 83(1) ስር ሕገ መንግስታዊ ክርክር ጉዳይ ሲነሳ በፌዴሪሽን ምክር ቤት ውሳኔ ያገኛል፡፡ የህገ መንግሥታዊ ክርክር መወሰን የህገ መንግሥታዊ ትርጉምን ይጠይቃል፡፡ በእርግጥ ህገ መንግሥተን መተርጐም ሕገ መንግሥታዊ ክርክር በመወሰን ብቻ ላይ የሚያበቃ ላይሆን ይችላል፡፡ ለአብነት ያክል የህገ መንግስት ክርክር ጉዳይ መወሰን ታሳቢ የሚያደርገው አከራካሪ ጉዳዮች  መቅረባቸው ወይንም  የተከራካሪ ወገኖችን መኖር ይጠይቃል፡፡ ይሁን እንጂ ህገ መንግሥስትን መተርጐም እነዚህ ሁኔታዎች ሳይኖሩ የህገ መንግሥት ትርጉም ሊኖር ይችላል፡፡ ይህ ሁለተኛ ሁኔታ ረቂቅ ትርጉም ወይንም “Abstract review” ተብሎ ሲታወቅ የመጀመሪያው ተጨባጭ ትርጉም “ Concrete review “ተብሎ ይታወቃል፡፡

የህገ መንግስት ትርጉም በዋንኛነት የሚያተኩረው የህገ መንግሥትን የበላይነት ማረጋገጥ ወይንም ማስፈፀም ነው፡፡  በኢፌድሪ ህገ መንግሥት አንቀጽ 9(1) ሕገ መንግሥቱ የሀገሪቱ የበላይ ህግ ነው ይላል፡፡  ስለሆነም ማንኛውም ሕግ ልማዳዊ አሰራር፣ እንዲሁም የመንግሥት አካል ወይም ባለስልጣን ውሳኔ ከሕገ መንግሥቱ ጋር የሚቃረን ከሆነ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡ በሌላ አነጋገር የሚቃረን ሆነው በተገኙበት ሰዓት ተፈፃሚነት እንዳይኖራቸው ይደረጋሉ ማለት ነው፡፡

**ለምሳሌ፦** የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ወይንም የሚንስቴሮች ምክር ቤት የሚያወጣው አዋጅ ወይንም ደንብ ከሕገ መንግስቱ ጋር የሚቃረን ከሆነ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በአንቀፅ 62(1) እና 83(1) መሠረት ተፈፃሚነት እንዳይኖረው ያዛል፡፡

- **መወያያ ጥያቄዎች**

1. በከድጃ በሽር ጉዳይ ላይ የተሰጠውን ውሳኔ በማንበብ የውሳኔውን ይዘት፣ ያለፈበትን ሂደት፣ የመጨረሻውን ውሳኔና ያለህን አስተያየት ለክፍሉ ተማሪዎች አስረዳ፡፡
2. ህገ-መንግስትን በመተርጐም ሂደት የፍ/ቤት ሚና ከሌሎች አገሮች ጋር ስናስተያይ እኛ አገር ምን ይመስላል፡፡
3. በአዋጅ ቁጥር 250/93 መሠረት የህገ-መንግስት አጣሪ ጉባኤ የሚመራበት ሥርዓት ምን ይመስላል?
4. ህገ-መንግስትን መተርጐም ለምን አስፈለገ?
5. እያንዳንዱ ተማሪ የክልሉን ወይንም የሌላ ክልል ህገ-መንግስት በማጥናት በአወጣጥ፣ በማሻሻል ፣በአተረጓጐም መርህ ላይ ከሌሎች ጋር በማነፃፀር ጠንካራ እና ደካማ ጐኑንን ለክፍል ተማሪዎች ያቀርባሉ፡፡

## 1.6. ስለህገመንግስታዊነት ምንነትና ህገመንግስታዊነትን ስለማስረጽ

### 1.6.1. የህገመንግስታዊነት ምንነት/ትርጉም

ከዘመናችን ሁለት መቶ የሚሆኑ ሉዓላዊ አገሮች እንዳሉና ከነዚህም በጣም የበዙት የተፃፈ ህገ መንግስት እንዳላቸው በጣት የሚቆጠሩ ደግሞ ያልተፃፈ ህገ መንግስት እንዳላቸው በዚህ ዙሪያ የተሰበሰቡ መረጃዎች ያሣያሉ፡፡

**የትምህርቱ ዝርዝርዓላማ፡**

**ከዚህ ክፍል ትምህርት በኃላ፡**

☐ ህገ መንግስታዊነት (Constitutionalism) የሚለውን ፅንሰ ሀሳብ ይተረጉማሉ፣

☐ በአንዲት አገር ለህገ መንግስታዊነት እድገት መሠረቱ ምን እነደሆነ ይገልጻሉ፡፡

**ውድ ሰልጣኞች፣**

☐ ህገ መንግስት ባለበት አገር ሁሉ ህገ መንግስታዊነት አለ ?

☐ ሆኖም በዓለማችን ውስጥ ባሉት አገሮች ሁሉ ህገ መንግስታዊነት ሰፍኗል?

ወይ የሚሉት ጥያቄዎች ሲነሱ መልሱ ቀላል አይደለም፡፡ ለዚህም ምክንያቱ ህገ መንግስታዊነት በአንዲት አገር የሰፈነ መሆኑን ለመረዳት አገሪቱ ህገ መንግስት ያወጀችው ህግ መኖሩን ከማረጋገጥ በላይ ሌሎች ነገሮችን ማመዛዘንና መመርመር ስለሚጠይቅ ነው፡፡

ህገ መንግስታዊነት (Constitutionalism) የሚለውን ፅንሰ ሀሳብ የተለያዩ ፍችና ትርጓሜ በተለያዩ መፅሐፎች ውስጥ ተሰጥቶ እናገኛለን፡፡ ከሥነ ቃል ፍችው ለመጀመር የኦክስፎርድ የእንግሊዘኛ መዝገበ ቃላት “Constitutionalism is a belief in the constitution” የሚል ፍች ይሰጠዋል፡፡ ከዚህ የሥነ ቃል ፍች የምንረዳው ህገ መንግስተዊነት ለአንዲት አገር ህገ መንግስት ያለው ታማኝነት እና እምነት የሚገልፅ ፅንሰ ሀሳብ ነው፡፡ በመሆኑም ህገ መንግስታዊነት በአንድ በኩል የመንግስት አካላት እና የመንግስት ባለሥልጣናት በህገ መነግስቱ የተደነገጉ መሠረታዊ መርሆች እና እሴቶች በሙሉ ልብ በመቀበል እነዚህን ህገ መንግስታዊ መርሆች እሴቶችና ድንጋጌዎች ከእለት ዕለት ሥራቸው መመሪያቸው አድርገው ሲገለገሉበትና ተግባራዊ ሲያደርጉት እንደዚሁም ህገ መንግስቱን ለማስከበር ያለማንም ቀስቃሽነት በዕምነትና በቁርጠኝነት የሚሠሩ መሆናቸውን የሚገልፅ ፅንሰ ሀሳብ ነው፡፡

በሌላ በኩል ህገ መንግስታዊነት እያንዳንዱ ዜጋ ማህበር፣ የፖለቲካ ድርጅት የህገ መንግስቱን መርሆች እሴቶችና ድንጋጌዎች በሙሉ ህገ መንግስቱን በማክበር ሲንቀሳቀሱና ህገ መንግስቱን የሚጥስ ማናቸውም በመንግስት አካላት ወይም ሌላ ግለሰብ፣ ማህበር ወይም ድርጅት እንዲገታ እና እንዲቆም ለማድረግ በዕምነትና በቁርጠኝነት ከሚንቀሣቀሱበት ደረጃ ላይ የደረሱ መሆኑን ለመግለፅ የምንጠቀምበት

ፅንሰ ሀሳብ ነው፡፡ በአጠቃላይ ሲታይ ህገ መንግስታዊነት ማለት የህገ መንግስት የበላይነት በአንዱት አገር በተሟላ ሁኔታ በተግባር ሲውልና አብዛኛው ህዝብ የህገ መንግስቱ ተከላካይና ጠባቂ ለመሆን በሙሉ ፍላጎትና የሀሳብ ዝግጅት የሚገኝ መሆኑን ለመግለፅ የምንጠቀምበት ፅነሰ ሀሳብ ነው፡፡

ህገ መንግስታዊነት የሚለው ሀሳብ (ኬሪ እና አብረሀም) የተባሉ ፀሐፊዎች በበኩላቸው 'The Phenomenon of government conforming to the dictates of a settled constitution is known as constitutionalism' በማለት ይገልፁታል ፡፡ እንደነዚህ ፀሐፊዎች አገላለፅ መንግስት የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች እና መርሆች በማክበረና በህገ መንግስቱ በተቀመጠለት ወሰን ሥልጣኑን በመገደብ በተግባር የሚንቀሣቀስበት አጋጣሚ (ሒደት) ነው፡፡ ህገ መንግስታዊነት የሚባለው፡ ህገ መንግስታዊነት የአንዱት አገር ህዝብ የሚተዳደረባቸውን ህገ መንግስታዊ ህግጋት ብቻ የሚመለከት አይደለም፡፡ በአንፃሩ ህዝብ የመንግስትን እንቅስቃሴ በህገ መንግስቱ መሠረት የሚቆጣጠርበትና የሚያረጋግጥበት ሥርዓት መፈጠሩን የሚመለከት ነው፡፡ ከህግ አንፃር ህገ መንግስታዊነት በአንድ በኩል መንግስታት ለህገ መንግስቱ ያላቸውን ታማኝነትና ተገዥነት በሌለ በኩል ህዝቡ ህገ መንግስቱን ለማስከበር እና መንግስት በህገ መንግስቱ መሠረት እንዲመራ ለማስገደድ ያለውን እምነትና የሚያደርገውን እንቅሰቃሴ ያመለክታል፡፡

ሌላው ፀሐፊ ደግሞ "Constitutionalism emphasizes obedience to constitutional principles and respect the authority of the fundamental law" በማለት ይተረጉመዋል፡፡ ይኸም ተርጓሜ ከላይ ካየናቸው ሁለት መሠረታዊ ተርጓሜዎች በይዘቱ የተለየ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ህገ መንግስቱ በአገሪቱ ውስጥ የመንግስት ስልጣን ምንጭና መሠረት መሆኑና መንግስት ዜጎችና ሌሎች ተቋማት ለምሣሌ ማህብራት የፖለቲካ ድርጅች ገዥ የሆነ የአገሪቱ የበላይ ህግ መሆኑን በመቀበል ለህገ መንግስቱ ተገዥ ሆኖ መገኘትና ህገ መንግስቱም እንዲከበር የበኩላቸውን ኃላፊነት በመወጣት ነው፡፡ የመንግስት አካላት ባለሥልጣኖቻቸው ማህበሮችና የማህበራት መሪዎች ፣ የፖለቲካ ድርጅቶችና የፖለቲካ ድርጅት መሪዎችና አባላቶቻቸው ለህገ መንግስቱ "obedience" ያላቸው ወይም በህገ መንግስቱ ተገዥ መሆናቸውንና ታማኝ መሆናቸውን የሚያረጋግጡት በህገ መንግስቱ እንዲካተት

ወይም እንደወጣ የሚፈልጉት ሀሳብ እንኳን ቢኖር ለህገ መንግስቱ ተገዥ መሆንና ሀሳባቸውን ለማካተተ ህገ መንግስቱ የሚፈቅደው ሥርዓት አክበረው መንቀሣቀስ ነው፡፡ በመሆኑም ህገ መንግስታዊነት ስንል የተለያየ ሀሳብና ፍላጉት ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ድርጅቶች ያሏቸውን ልዩነቶች አንደያዙ በህገ መንግስቱ ጥላ ሥር ተሰባስበው የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች መሠረት አድርገው ለመፍታት ያላቸውን እምነትና ቁርጠኝነት ሁሉ የሚመለከት ፅንሰ ሀሳብ ነው፡፡

ህገ መንግስታዊነት በአንዲት አገር በህገ መንግስትነት የታወጀ ሰነድ ከመኖሩ ባሻገር መንግስት የተለያዩ ማህበሮችና የፖለቲካ ድርጅቶች ህብረተሰቡ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች ለማክበርና ለህገ መንግስቱ ተገዥ ሆነው መገኘታቸውን ይመለከታል፡፡ ህገ መንግስታዊነት ህገ መንግስቱ በፅሁፍ ብቻ ሣይሆን በአገሪቱ በተግባር ዕውን የመሆኑን ሁኔታ ያመለክታል፡፡ ይኸ ከሆነ ህገ መንግስት ባለበት አገር ሁሉ ህገ መንግስታዊነት አለ ወይ? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ የሌሎች አገሮችና የእኛን አገር ተመክሮ በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡

## *ሀ. <u>የተፃፉ ህገ መንግስትና ህገ መንግስታዊነት</u>*

ከላይ ከተገለፀው ሀሳብ አንፃር በአንዲት አገር ህገ መንግስታዊነት ለማስፈን የተፃፈ ህገ መንግስት መኖሩ የግድ አስፈላጊ ነው ወይ? የሚለው ጥያቄ ይነሣል፡፡ በዓለማችን ብዙ የተፃፈ ህገ መንግስት ያላቸው አገሮች ህገ መንግስታዊነትን እንዳላሰፈኑ በመስኩ ጥናት ያደረጉ ሙሁራን ይገልፃሉ፡፡ ለምሥሌ ድክታቶሪያልሽፕ (**dictatorship**) በነገሰባቸው በብዙዎቹ አገሮች ህገ መነግስት ቢኖርም ህገ መንግስታዊነት እንደማይሰፋን በቀድሞ ሶቭየት ህብረት ህገ መንግስት ውስጥ የተካተቱ የሰብዓዊ መብቶችና ነፃነቶች በተደጋጋሚ በመንግሰት አካላት የሚጣሱበት እና የማይከበርበት ሁኔታ እንደነበር ታይቷል፡፡ በአብዛኞቹ የአፍሪካ አገሮች ህገ መንግስት ያላቸው መሆኑን ለሌላው ዓለም ለማሣየት ከሚገለገሉበት በስተቀር ለህገ መንግስቱ ድንጋጌዎች ተገዥ እንደማይሆኑ በዚህ መስክ ጥናት ያደረጉ ሙሁራን ይገልፃሉ፡፡

ስለ ህገ መንግስታዊነት ሲነሣ በእኛም አገር ትምህርት ልንወስድባቸው የሚገባቸው ከበቂ በላይ የሆኑ ገጠመኖች ይኖራሉ፡፡ ለምሣሌ የኤርትራ ፌዴሬሽን ፈርሶ ከኢትዮጲያ ጋር እንድትዋሀድ የኤርትሪ ህገ አውጭ ምክር ቤት የወሰነው በወቅቱ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት በፀደቀውና ኤርትራዊያን በተቀበሉት ህገ መነግስት ምክር ቤቱ ይህንን ውሣኔ ለመወሰን የሚያስችለው ሥልጣን ሣይኖረው ነው የሚል መከራከሪያ የሚያቀረቡ አሉ፡፡ ይኸ እንዳለ ሆኖ በተለይ በደርግ ዘመን 1980 ዓ.ም ህገ መንግስት ከፀደቀ በኃላ ህገ መንግስቱ ለይስሙላ የፀደቀ ሰነድና ባለሥልጣናቱ  እንደማያምኑበት የሚያረጋግጡ በርካታ ክስተቶች ታይተዋል፡፡ ሆኖም ሁሉንም ለመዘርዘር ስለማይቻል አንድ የዞን ዐቃቤ ህግ ገጠመኝ አቅርቦናል፡፡

በ1980ዓ.ም አዲስ አበባ ዮንቨርስቲ ተመርቆ 1981 የዞን ዐቃቤ ህግ ሆኖ የተመደበ አንድ ወጣት የህግ ባለሙያ የዞኑን ማረሚያ ቤት ሲጎበኝ 60 ሰዎች ያለ ፍርድ ቤት ትዕዛንዝ ታስረው ከሶስት ወር በላይ እንደቆዩ ያረጋግጠል፡፡ በመሆኑም በወቅቱ የዐቃቤ ህግ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 11/80 እና የደርግ ህገ መንግስት በመጥቀስ የታሰሩት ሰዎች በአስቸኳይ እንደፈቱ በፅሑፈ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡ የዐቃቤ ህግ ትዕዛዝ በፅሁፍ የደረሰው ማረማያ ቤት ለክፍለ ሀገር ኢሠፖ አንደኛ ፀሐፊ ሪፖረት ያደርጋል፡፡ የፖርቲው ባለሥልጣን ዐቃቤ ህጉን አስጠርቶ ሲጠይቀው በህገ መንግስቱ ድንጋጌ መሠረት ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ መታሰር ስለሌባቸው እኔ ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 11/80 ህገ ወጥ እስር የማስቆም ስልጣን ስላለኝ ነው ትዕዛዝ የሰጠሁት በማለት የስረዳዎል፡፡ የክፍለ ሀገር የኢሠፖ አንደኛ ፀሐፊም ይህንን አዋጅ ቁጥር 11/80 የምትለውን ቀቅለህ ብላው፡፡ ህገ መንግስቱን እኛ ያወጣነው ህገ መንግስት ያለን  መሆኑን  ለዓለም ህዝብ ለማሣየት እንጅ በውስጡ የተፃፈውን ሁሉ ለመተግበር እንዳለሆነ ማወቅ አለብህ፡፡ ሁለተኛ እንዳይለምድህ ብሎ የስናበተው ሁኔታ እንዳለ ከዐቃቤ ህጉ ዘገባ ለመረዳት ይቻላል፡፡

ይኸ ገጠመኝ በአንዲት አገር ድክታቶሪያል የሆነ መንግስት ካለ ህገ መንግስት እንጂ ህገ መንግስታዊነት እንደማይኖር ያሣያል፡፡ በመሆኑም የተፃፈ ህገ መንግስት መኖሩ በራሱ የመጨረሻ ግብ አይደለም፡፡ ህገ መንግስቱ መከበሩ በሥራ ላይ መዋሉና መንግስትን ጨምሮ ሌሎች አካላት ለህገ መንግስቱ ተገዥ እና ታማኝ

የመሆናቸው ጉዳይ በዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ውስጥ እጅግ በጣም ቁልፍ ጉዳይ ነው፡፡

ለምሣሌ ፡- ይኸ ነው ብሎና በፅሁፍ ተጠቃልሎ የተቀመጠ ህገ መንግስት በሌላት እንግሊዝ ውሰጥ ህገ መንግስታዊነት መስፈኑን ቶማስ ፔይን የተባለ ፀሐፊ 'acknowledging the constitution's authority and obeying its commands do not require that a constitution be in written form, nor is a written constitution a guarantee that constitutionalism is present' በማለት ገልፆታል፡፡ ከዚህ አንፃር እንግሊዞች ከማግና ካርታ ጀምሮ በየወቅቱ ባዳበሯቸውና ባሣደጓቸው መርሆችና የመንግስት ተቋማትና ምልዕተ ህዝቡ ተገዥ መሆናቸውን በማየት ነው ህገ መንግስታዊነትን ለማስፈን የግድ የተፃፈ ህገ መንግስት መኖር አስፈላጊ አይደለም፡፡ የተፃፈ ህገ መንግስት መኖሩ ደገሞ ህገ መንግስታዊነት ለማስፈን ዋስትና ሊሆን አይችልም የሚል ትንታኔ በመሰኩ ጥናት ያደረጉ ሙሑራን የገልፁት፡፡ ይህንን አባባል "Staying within constitutional bounds and obeying the principle of constitutionalism do not require a written constitution and other legal term since constitutionalism is the consequence of attitudes and convictions, its presence is assured in one instance by certain national tradition and in another by still other traditions" በማለት ይገልፀዎል፡፡

በአጠቃላይ ስንመከተው ህገ መንግስት ህገ መንግስቱን በተግባር ለማዋል ያለ ውስጣዊ ዕምነትና ቁርጠኝነት ለህገ መነግስቱ ተገዥና ታማኝ የመሆን ጉዳይ ነው፡፡ ስለዚህ ህገ መንግስቱ እያለ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች የሚጥሱ ተግባራት እዚህም፣ እዚያም በመንግስት ባለሥልጣናተ ወይም በሌሎች ድርጅቶች ባለሥልጣናትና ተከታዮች ሊፈፀሙ ይችላሉ፡፡ እነዚህን ህገ መንግስቱን የሚጥሱ ተግባራት ለመከልከል እና በህግ አግባብ ለመቆጣጠር በመንግስት አካላትና በህብረተሰቡ ያለው ቁርጠኝነት እና ዝግጅነት ነው በአንዲት አገር ለህገ መንግስታዊነት እድገት መሠረት የሚሆነው፡፡

## ለ. *በኢፌድሪ ህገ መንግስታዊነት ስለማስረፅ*

በአገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ  የብጥብጥ የእርስ በረስ ጦርነት ምክንያተ የሆኑ ቁልፍ የፖለቲካ የማህበሪዊና ኢኮኖሚያዊ ጥያቄዎች የሚመልስ ሰለ ወደፊቷ ኢትዮጰያ ግልፅ ራዕይ የያዞና ህገ መንግስታዊ ግቦችን የስቀመጠ በኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች የቃል ኪዳን ማተባቸውና የጋራ መመሪያቸውና መተዳደሪያቸው እንደዚሁም የሉዓላዊነታቸው መግለጫ አድርገው የፀደቁት ህገ መንግስት መኖሩ የሚያከሪክር አይደለም፡፡

ነገር ግን የኢፌድሪን ህገ መንግስታዊነት  ለማስረፅ

- ✓ በፌዴራልም ሆነ በክልል ደረጃ የተቋቋመ የመንግስት አካላት ህገ መንግስቱን የዕለት ከዕለት የሥራቸው ውስጥ አንደ መሠረት በማየት እየተንቀሣቀሡና ውሣኔዎችን እየወሰኑ  መሆኑን
- ✓ የመንግስት ባለሥልጣናት የህገ መንግስቱን ድንግጌዎች መርሆችና እሴቶች በማክበር የሚሠሩ በመሆናቸውንና ህገ መንግስቱን ለማስከበር የህገ መንግስቱን ራዕይ በመሠረታዊ ግቦችና እሴቶች በአግባቡ ተገንዝበው እየተንቀሣቀሡ መሆኑን
- ✓ ማናቸውም ማህበር የፖለቲካ ድርጅት ወይም ተቋም የህገ መንግስቱን መርሆች እሴቶችና ድንጋጌዎች በማክበረና ለህገ መንግስግስቱ ተገዥ በመሆን ልዩነታቸውን በህገ መንግስቱ ጥላ ስር ሆነው ህገ መንግስቱ በዘረጋው ስርዓት መሠረት መብታቸውን ለማስከበርና ፐሮግራማቸውን ተግባሪዊ ለማድረግ እየተንቀሣቀሱ መሆኑን፡
- ✓ ምዕላተ ህዝቡ የመንግስት አካላት ህገ መንግስቱን አክበረውና ለህገ መንግስቱ ተገዥ ሆነው እንዲሠሩ ማናቸውም ሰው ማህበር የፖለቲካ ድርጅት ወይም ባለሥልጣን ለህገ መንግስቱ ተገዥ ታማኝ  ሆኖ እንድንቀሣቀስ በተለያየ መንገድ ግፊት የሚያደርግ መሆኑንና ህገ መንግስቱን የሚፃረር ነገር ሲፈፀም የሚቃወም መሆኑን
- ✓ በአጠቃላይ የህገ መንግስቱ ራዕይና ግቦች መርሆችና ድንጋጌዎች በሁሉም የመንግስት አካላት በሌሎች ተቋማት በምዕላተ ህዝብ በዕምነት የያዛቸውና ለተፈፃሚነታቸውም ቁርጠኛ መሆኑን ለማረጋገጥ በምንችልበት ደረጃ ላይ ካልደረሰን ህገ መንግስታዊነትን በተሟላ ሁኔታ አስረፀናል ማለት እንችልም፡፡ በመሆኑም በኢፊድሪ ህገ መንግስታዊነት ለማስረፅ የፍትህ አካላት የበኩላቸውን ሀላፊነት መወጣት አለባቸው፡፡

- *የመወያያ ጥያቄዎች*

1. የህገ መንግስት የበላይነት ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ፣ የህግ የበላይነትና ለዕልና ማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓት መገንባት ይቻላል ብለው ያስባሉ?
2. መንግስት ብቻውን ለሕገመንግስቱ በሚኖረው ተገዥነት ሕገመንግስታዊነትን ማስፈን ይቻላል?

## 1.6.2. ህገመንግስታዊነትን ማስፈንን በተመለከተ የተወሰኑ አገራት ተሞክሮ

የምሥራቅ አፍሪካ አገሮች ከቅኝ አገዛዝ ነፃ ከወጡ በኃላ ሕዝብ አሳታፊ የሚያደርግና ያልተማከለ የመንግስት አስተዳደርን የሚያሰፍን ህገ መንግስታዊ ሥርዓት ተዘርግቶ ነበር፡፡ ቢሆንም አዲስ የተጀመረው ፌዴራል ሥርዓት ወይም ራስን በራስ ማስተዳደር የሚያጎናፅፈው ህገመንግስታዊ ሥርዓት ለሥርዓቱ ተገዢ በማይሆኑ ፍጹማዊ ሥልጣን ባለቤት በሆኑ በአንድ ሰው አመራር እጅ ወደቀ፡፡
ለምሳሌ በታንዛንያው ፕሬዚደንት ነይሬሬ፣ በኡጋንዳው በጠቅላይ ሚንስተር ኦቦቴ፣ በኬንያው ፕሬዚዳንት ጆሞ ኬንያታለስልጣን ባደርጉት ሽኩቻ ሥልጣኑን ጠቅልለው ወደ ማዕከል ማሰባሰብ ቻሉ፡፡ ይህም ሥልጣንን በተለያዩ አካላት መካከል የሚያከፋፍል ለነበረው ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት ተቃራኒ አሠራር ነው፡፡ ሥልጣንን ለተለያዩ አካላት ማከፋፈል መለያየትንና ኃላም የግዛት አንድነቷን አደጋ ላይ ይጥላታል ከሚል ስጋት የመነጨ ነው፡፡

ለአሜርካን ህገመንግስታዊንት መስፈን በዋናነት ትልቁን ሚና የሚጫዎተው ፍርድቤቶች ህገመንግስቱን በመተርጎም ህገመንግስታዊነቱን እንዲተብቁት መደረጉ ነው፡ ፡ የአሜርካ ህገመንስት ከፀደቀበጽ ጊዜ ጀምሮ በተለያዩ ጊዜ ዳኞች ይከተሉዋቸው የነበሩ የህገ መንግስት ትርጉም መርሆዎችን በዚህ ክፍል እንዳስሳለን፡፡ በአሜርካን ዳኝነት ታሪክ ለዘመናት በተርጉም ላይ ከፍተኛ የሆነ ክርክር ይደረጋል፡፡ ይም የሆነበት ምክንያት በሕገ መንግስቱን የመተርጎም ሥልጣን ስለተሰጣቸው ነው፡፡ የሚደረገው

ትርጉም በጣም ምናባዊ በመሆኑ ዳኝነቱ አካል ህገምንግስቱን በመተርጎም ሚና ላይ ቀጣይ ክርክር እያስነሳ ይገኛል፡፡

Tectualism,""Orginalism""Doctrinalism",Developmentalism","philosophic approach", "Systemic" እና,"Balancing"የሚባሉ ሲሆን እንደ አማራጭ የሚወስዱት ደግሞ "Strict vs Liberal," "Judical activism vs Judical self-restraint", substance vs procedure እና "Interpretive vs Non Interpretive"ይባላሉ፡፡

በአጠቃላይ ስድስት የህገመንግስት ትርጉም ሥርዓቶች ቢኖሩከነዚህ ውስጥ የተወሰኑትን ለምየት እንሞክራለን፡፡

# ቴክስቿሊስት (Textualism)

ፎርማሊስት ትዎሪ በመባል የሚታወቅ ሲሆን የሕግ አውጪው ያወጣው ሕግ ግልፅ ትርጉም በመከተል የሚሰጥ ትርጉም ነው፡፡ ተክስ ሊስት ትርጉም የሚከተሉ ዳኞች የሕግ አውጪውን የውይይት ቃለ ጉባኤ በሁለት ምክንያቶች ለትርጉማቸው መሰረት አያደርጉም፡፡የመጀመሪያው ሁሉም የፓርላማ አባላት አንድን ህግ ለማውጣት ተመሳሳይ ወይም አንድ ዓይነት ሀሳብ አይኖራቸውም፡፡ የህግ አውጪው ህጉን ሲያወጣ የነበረውን ሀሳብ መፈለግ ሁለት የተለያዩ ሕግ አውጪ ምክርቤት (ለምሳሌ፤በአሜርካ Senate እና ህዝብ ተወካዩች ምክር ቤት) መኖራቸውን መርሳት ስለሚሆን ነው፡፡

# ኦሪጂናሊስት (Originalism)

የተባፊ ህግ ትርጉም ህግ አርቀቂውና አፅዳቂው ለማለት ካሰቡት ጋር ተመሳሳይ፣ ትርጉሙ መሰረት ማድረግ ያለበት ህጉ በጸደቀበት ዘመን የነበረ ትክክለኛ አዕምሮ የነበረው ሰው የሚሰጠው ትርጉም ነው፡፡ በአሜርካ ይህንን ላገኘት ሕገ መንግስቱን መስራች አባቶች የፃፉትን ጽሁፍ ማንበብ ነው፡፡ ያሁኑ ዘመን ሰውም የህገ መንግስቱን ቃላትና ዐ.ነገሮችን ስተረጉም መከተል ያለበት መርህ ሕገምንግስቱ ስረቀቅ ልኖራቸው የሚችለውን ትርጉም በመከተል ነው፡፡ ዘመናዊው ሰው ለቋንቋው የተለያየ ትርጉም ቢኖረውም መከተል ያለበት ትርጉም የፀደቀበትን ዓላማ፣አደረጃጀቱና የህገመንግስቱን ታሪካዊ አመጣጥ መሰረት ያደረገውን ትርጉም ነው፡፡

J

**ድብሎፕመንታል (The developmentalist approach)**

ድብሎፕመንታል መርህ በዶክትሪናል መርህ ላይ የተመሰረተ ቢሆንም ዳኛ ሰራሽ ቀኖናን ይቀበላል። በዚህ ሁኔታ ታሪክን፣መደበኛ እና መደበኛ ያልሆኑ አሰራሮችንና የፖለቲካ ባህልን እስከማካተት ይደርሳል። ሕገ መንግስቱን በትርጉም ህይወት እንዲኖረው በማድረግ ከዘመኑ ጋር እንድራመድ ማድረግ አለብን የሚል ነው።

**በዶክትሪናል (The doctrinalist approach)**

በቀደሙ ዳኞች ለተመሳሳይ ጉዳይ የተሰጠውን ትርጉም በማፈላለግ በእጃቸው ያለውን ችግር የሚፈቱበት ሥርዓት ነው። ለ*stare decisis* *ትልቅ ቦታ የሚሰጥ ነው። የህንን በማድረግ የልማድ ህግ (*common law) ቀጣይነት ያስጠብቃሉ። እነ ዳኛ አንቶንን ስካሊያ ዶክትሪናሊስት ለዳኛ ሰፊ ምርጫ በመስጠቱ ይንን ቀኖና ይተቹታል።

## የኢፌዲሪ ህገ-መንግሥት ከፀደቀበት ጊዜ ጀምሮ በአገርቱ ህገ-መንግሥታዊነትን ለማስፈን የተደረጉ ጥረቶችና የተገኙ ውጤቶች

### 1. የኢፌዲሪን ህገ-መንግሥት በላይነት ለማረጋገጥ የተደረጉ ጥረቶች

**የትምህርቱ ዝርዝር ዓላማ፡**

**ከዚህ ክፍል ትምህርት በኃላ፡**

- ☐ ህገ-መንግሥታዊነትን ለማስፈን የተደረጉ ጥረቶችንና የተገኘውን ውጤት አንድ በአንድ ይዘረዝራሉ።

**ውድ ሰልጣኞች፡**

- ☐ በብዙዎች ክልል መንግስታት የታወጁ ህግጋተመንግስታት ብዙም በሥራ ላይ ሳይቆዩ እንዲሻሻሉ የተደረጉበት ምክንያት ምን ይመስላችኋል?

በእርግጥ ለክልል ሕግጋተመንግስታት መሻሻል አንድ ብቻ ምክንያት ነበረው ማለት አይቻልም። በየክልሉ የተለያዩ ምክንያቶች ሊኖሩ እንደሚችሉ ቢታወቅም ከመዘርዝር ታቅበን ለሪዕሳችን አግባብነት ያለውን የአንድ ክልል ብቻ ለመየት እንሞክራለን።

1987 የደቡብ ክልል ሕገመንግሥት የከፍተኛ ፍርድቤት ዳኞችን ሹመት በተመለከተ በዞኑ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ አቅራቢነት በዞኑ ምክርቤት ሹመታቸው እንደምፀድቅ ይደነግግ ነበር። ይህም የኢፌዲሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 81(4)የክልሉ ከፍተኛ

ፍርድቤት ዳኞች ሹመት በክልሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ አቅራቢነት በክልሉ ምክርቤት እንደምሾሙ የተደነገገውን የኒቃረን ነበር፡፡ በእነ ጸጥሮስ ጎዳና መ/ቁ---- በሆነ የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድቤት ዳኞች በሰጡት የጥፋተኛና ቅጣት ውሳኔ ላይ ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድቤት ሲቀርብ ከቀረቡት ቅረታ ነጥቦች አንዱ የዳኞች ሹመት ሕገመንግስታዊ አይደለም የሚል ነበር፡፡ ይህ ለክልሉ ሕገመንግስት መሻሻል አንዱ ምክንያት እንደነበረ የተሻሻለውን የ1994ዓ.ም አንቀጽ126 በመመልከት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ቀደም ሲል ለተሠሩ ሥራዎች ዋጋ ለመስጠት ሲባል በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰበችና ሕዝቦች ክልል ሕገ መንግስት አዋጅ ቁጥር 1/1987 ዓ.ም መሠረት የተሾሙ ዳኞች በዚህ ሕገመንግስት እንደተሸሙ ይቆጠራል በማለት ጊዜያዊ አግልግሎት ያለው ድንጋጌ በሕገመንግስቱ ውስጥ እንዲካተት ተደርጓል፡፡

ሌላው የማሻሻያው ምክንያት የነበረው በሕግ አውጪውና በሕግ አስፈፃሚው መካከል የሥልጣን ክፍፍል ለማበጀት ነው፡፡ ከፍ ብሎ በትምህርታችን ክፍል እንደተመለከትነው ፓርላሜንታዊ ሥርዓተ መንግስት ባላቸው አገራት የሥልጣን ክፍፍሉ ፍፁማዊ ባይሆንም ሕግ የማውጣትና የማስፈፀም ስልጣኑ የተለያዩ አካላት ተግባር ነው፡፡ የፌዴራል ህገመንግስቱም ሆነ ህገመንግስቱ ያቋቋማቸው ሕግ አውጭ እና ሕግ አስፈፃሚ አካላት በፌዴራል ደረጃ በግልጽ ራሳቸውን ችለው የቆሙ ናቸው፡፡ ነገር ግን በደቡብ ክልል እነዚህ ሁለቱ ተግባራት በአንድ መክር ቤት በሚባላ አካል ሲፈፀሙ ነበር፡፡

ነገር ግን የተደረገው ማሻሻያ ርዕሰ መስተዳደሩን የክልሉ ርዕሰ ብሄርና የአስፈፃሚው የበላይ አዛዥ፤አፌጉባኤውን የሕግ አውጪው ምክር ቤት ሰብሳቢ በማድረግ ከፌዴራል ሕገ መንግስት ጋር በማጣጣም ማሻሻያ ተደርጓል፡፡

ሌሎችም ክልል ሕግጋተመንግስታት ተመሳሳይ ሰዓት በሕገመንግስታቸው ላይ ማሻሻያ ሲያደርጉ ምክንያቱ ይለያይ እንጂ ከፈዴራል ሕገመንግስት ጋር የማጣጣሙ ጉዳይ ዋነኛ አጀንዳ ነበር፡፡

ሕገመንግስቱ ብቻ ሳይሆን ሌሎች የፌዴራል መንግስት ሕጎች የበላይ ለመሆናቸው ሌሎች አገር ህገ መንግስታት በግልጽ ይደነግጋሉ፡፡ የአሜርካ ሕገ መንግስት የፌዴራል ህጎች የበላይነት (supremacy clause) በመያዝ በምሳሌነት የሚጠቀስ ነው፡፡ የኢፌዲሪ ሕገ መንግስት የፌደራል ሕጎች የበላይ ስለመሆናቸው የሚያወሳ የሕገ መንግስታዊ ድንጋጌ አላካተተም፡፡ ይሁን እንጂ የክልል መንግስታት አዋጆች

የኢፌዲሪን ሕግ መቃረን እንደሌለባቸው በክልሎች ደረጃ የታመነ ጉዳይ ነው፡፡ ክልሎች የሚያወጣቸውን ማናቸውንም ሕጎች ከፌዴራል ሕጎች ጋር መጣጣማቸውን ማረጋገጥ የመጀመሪያ ተግባራቸው ነው፡፡ ክልሎች የሚያወጣቸው ህጎች ከፌዴራል ሕጎች ጋር መቃረን ከታየም የክልል ፍጎች ዋጋ እንደሚያጡ በፌዴሬሽን ምክር ቤት ተወስኗል፡፡ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው የፌዴሬሽን ምክር ቤት በእነ ቢያድግልኝ መለስ ከአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት መካከል ባለው ክርክር የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ያወጣው የመሬት አዋጅ ከፌዴራል መንግስት የመሬት አዋጅ ጋር እስካልተቃረነ ጊዜ ብቻ ተፈፃሚነት እንደሚያገኝ የሠጠው ውሳኔ የፌዴራል ህጎችን የበላይነት በማስጠበቅ ሕገመንግስታዊ እሴቶች አንዱና ዋነኛ የሆነው ፌዴራል ሥርዓቱ የፀና መሠረት ላይ እንዲቆም በማድረግ የአንድ ኢኮኖሚ ማህበረሰብ ለመፍጠር ወሳኝነት አለው፡፡

## 2. ሕገመንግስቱ በትርጉም እየዳበረ መገኘቱ፡

የተለያዩ ሕገመንግስታዊ ጥያቄዎች በፌዴሬሽን ምክርቤት እየተወሰኑ ሕገመንግስታዊነቱ በመጠናከር ላይ ይገኛል፡፡ ለአብነት የሚከተሉትን ማየት ይቻላል፡፡

### ሀ. በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል በመምረጥና መመረጥ መብት ዙሪያ ለቀረበው ሕገመንግስታዊ ጥያቄ በፌዴሬሽን ም/ቤት የሰጠው ውሳኔ፡

የአማራ፣የኦሮሞ፣የትግራይና ሌሎች ብሔሮች ተወላጆች ዜጎች በ1992 ዓ.ም.በመላው አገርቱ በተደረገው ምርጫ ለቤንሻንጉል ክልል ም/ቤት ለመወዳደር በአሶሳና በባንቢሲ የምርጫ ክልል ለመሳተፍ እጩ ተወዳዳሪዎች ሲቀርብ በክልሉ ከሚገኙ አምስቱ ብሔረሰቦች ማለትም የበርታ፣የጉሙዝ፣የሽናሻ፣የኮሞና ማኦ ብሔረሰቦች ፖለቲካ ድርጅቶች መካከል የበርታ ብሔር የፖለቲካ ድርጅት አመራሮች በስተቀር በሌሎች 4ቱ የተደገፈ ነበር ፡፡ በዚህም መሰረት በዕጩ ተወዳዳሪዎች ከአምስቱ ብሔር አንዱ የሆነውነ የባርታ ብሔረሰብ ቋንቋን መናገር ስለማይችሉ ከተወዳዳሪነት እንዲሰረዙ የበርታ ፖለቲካ ድርጅት ለኢትጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ አቤቱታ አቀረበ፡፡ የምርጫ ቦርድም እጩ ተወዳዳሪዎች የበርታ ብሔረሰብ ቋንቋን መናገር አይችሉም በማለት ከምርጫው እንዲሰረዙ ወሰነ፡፡

የአማራ፣የኦሮሞ፣የትግራይና የሌሎች ነን የሚሉ አቤት ባዮች በኢፌዲሪ ሕገመንግስት ማናኛውም ኢትዮጵያዊ በቀለም፣በዘር፣በሀይማኖት፣በብሔር ብሔረሰብ፣በፆታ፣ በቋንቋ በፖለቲካ ወይም በሌላ አመለካከትና አቋም ላይ የተመሰረተ ልዩነት ሳይደረግበት በቀጥታና በነፃነት በመረጣቸው ተወካዮች አማከይነት በሕዝብ ጉዳይ አስተዳደር የመሳተፍ እንዲሁም በቋንቋው የመናገር፣የመፃፍ፣ ቋንቋን የማሳደግ፣ባህሉን የመግለፅ የማዳበርና የማስፋፋት እንዲሁም በሰፈረበት መልካዓምድር ራሱን የሚያስተዳድርበት መንግስታዊ ተቋማት የማቋንቋም እንዲሁም በየደረጃው በሚገኙ አስተዳደሮች ውስጥ ሚዛናዊ ውክልና የማግኘት መብት እንዳለው የተመለከተውን ህገመንግስታዊ መብታችን የጣሰ የምርጫ ቦርድ ውሳኔ በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 9 መሰረት ይሻርልን በማለት በ27/6/92 አቤቱታ ለፌዴሬሽን ም/ቤት አቅርበዋል፡፡

በጉዳዩ ላይ የውሳኔ ሀሳብ እንዲያቀርብ የተመራለት የህገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ አብዛኛው ድምፅ ሕገመንግስቱ አንቀጽ 38 ዜጎች ምንም አይነት ልዩነት ሳይደረግባቸው በቀጥታ በነፃነት በመረጣቸው ተወካዮቻቸው በኩል በሕዝብ አስተዳደር ጉዳዩ ላይ የመሳተፍ መብት ያላቸው መሆኑን ሲደነግግ በአንፃሩ ደግሞ የምርጫ ሕጉ አዋጅ ቁጥር 111/87 በአንቀጽ 38/1/ለ/ ስር ማንኛውም በእጩነት የሚቀርብ ተወዳዳሪ የሚወዳደርበትን ብሄራዊ ክልል ቋንቋ ማወቅ አለበት በሚል የተደነገገው የአንድን ክልል ቋንቋ የማያውቁ ነዋሪዎችን መብት የሚገድብ በመሆኑ የምርጫ ሕግ አዋጅ ከሕገመንግስቱ ጋር የሚቃረን በመሆኑ የሕገመንግስት ትርጉም ያሻል የሚል ነው፡፡

በ1993 ዓ.ም.1ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 1ኛ መደበኛ ጉባኤው በውሳኔ ሀሳብ ብቻ ሳይወሰን የፌዴሬሽን ም/ቤትን ለማተናከር ስልጣንና ተግባሩን ለመዘርዘር በወጣው አዋጅ ቁጥር 251/1993 አንቀጽ 8 መሠረት ተጨማሪ የባለሙያዎች አስተያየት እንዲያቀርቡ አድርጓል፡፡

ህገ መንግስቱ የዜጎችና የብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች መሰረታዊ መብቶች የተደነገጉበት፣የመንግስት አወቃቀር ከነስልጣንና ኃላፊነታቸው እንዲሁም የአሰራር ስርዓታቸው የሰፈረበት፣አገርቱ የምትመራበት መሰረታዊ የሆኑ የፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና የማህበራዊ ፖሊሲዎች የተቀመሩበት ሲሆን የሕዝቦች የወደፊት ራእይ ቃል ኪዳን ማሰሪያ በመሆኑ በሕገመንግስቱ አንቀጽ 9 እንደተደነገገው የአገርቱ የበላይ ህግ እንደመሆኑ መጠን ማናቸውም ህግ፣ልማዳዊ አሰራር እንዲሁም የመንግስት አካል ወይም ባለስልጣን ውሳኔ ከህገ መንግስቱ ጋር መጣጣምና እንዳለበትና ከህገ መንግስቱ

ጋር የሚቃረን ከሆነም የፌዴሬሽን ም/ቤት በህገ መንግስቱ አንቀጽ 9 መሰረት ህገመንግስቱን በመተርጎም ህጉ ተፈጻሚነት እንዳይኖር የማድረግ ግዴታ ተጥሎበታል፡፡ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሳዊ ሪፐብሊክ መንግስት በክልሎች የተዋቀረ ሲሆን በሕዝብ አሰፋፈር፣ ቋንቋ፣ማንነት፣እና ፈቃድ ላይ መሰረት ባደረገ አወቃቀር 9 ክልሎች አሉት፡፡ይህ ማለት ግን በእያንዳንዱ ክልል የሚኖረው ህዝብ ሁሉ አንድ አይነት ቋንቋ የሚናገርና አንድ አይነት ባህል አለው ማለት አይደለም፡፡ ይህ አይነት የመንግስት አወቃቀር የተመረጠው በአገራችን ኢትዮጵያ ደም ሶያፋስስና ለውድመት የዳረገንን የብሔሮችና ብሔረሰቦች እራስን በራስ የማስተዳደር፣በቋንቋ የመጠቀም፣የመማርና ባህልንና ታሪክን የማዳደርና የመንከባከብ መብቶች ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት ነው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ዴሞክራሲያዊ መንግስት ስንል በዋነኝነት ከላይ እስከታች ያሉ የፌደተራሉም ሆነ የክልል መንግስት አካላት ሁሉ አቀፍ፣ፍትሀዊ፣ነፃ፣በእኩልነት ላይ የተመሰረትና ድምፅ በሚስጢር በሚሰጥበት ስነ ስርዓት በሚካሄድ ምርጫ በሕዝብ የሚመረጡበት እና የግለሰቦችና የቡድኖች ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ሙሉ በሙሉ የሚከበሩበት ስርአት ነው፡፡ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ህዝቦች የኢትዮጵያ ሉአላዊ ስልጣን ባለቤት መሆናቸው በሕገመንግስቱ አንቀጽ 8 ሰፍሯል፡፡ በመሆኑም ማናቸውም ስልጣን የሚመነጨው ከሕዝብ ነው፡፡ ሕዝብ የሉአላዊ ስልጣን ባለቤት በሆነቤት ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ደግሞ የዘጎች የመምረጥና የመመረጥ መብት ሙሉ በሙሉ የተጠበቀ ነው፡፡ የመምረጥና የመመረጥ መብት አይነተኛ ግቡ የዜጎች መሪዎቻቸውንና አስተዳዳሪዎቻቸውን ራሳቸው እንዲመርጡና እንዲሽሩ ላስቻል ነው፡፡ ዜጎች የመምረጥና የመመረጥ መብታቸው ሲከበር በሕዝብ አስተዳደር ማለትም በፖለቲካ ጉዳይ ሙሉና ቀጥተኛ ተሳትፎ ይኖራቸዋል፡፡የዚህ መብት መረጋገጥ አማራጭ የሌለው ዋስትናን ይሰጣል፡፡ በመሆኑም በሕገመንግስታችን አንቀጽ 38 መሰረት ማናኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ በቀለም፣በባሔር፣ብሔረሰብ፣በፆታ፣ በቋንቋ፣ በሀይማኖት፣በፖለቲካ ወይም በሌላ የግል አመለካከቱና እምነቱ ላይ የተመሰረተ ልዩነት ሳይደረግበት በማናቸውም የመንግስት ደረጃ የተመሰረተ ልዩነት ሳደደረግበት በማናቸውም የመንግስት ደረጃ በየጊዜው በሚካሄድ ምርጫ የመምረጥና የመመረጥ መብት አለው፡፡

በህገ መንግስቱ አንቀጽ 25 መሠረት ሁሉም ሰዎች በህግ ፊት እኩል ናቸው፡፡ በሁሉም ደረጃ የሚገኝ የመንግስት አካል ማንኛውንም ህግ በሚያወጣበት ጊዜ በሰዎች መካከል

ማናቸውንም ዓይነት ልዩነት ሳደርግ ሁሉንም በእኩል አይን የሚያይ እና ለሁሉም በእኩልነት ዋስትናና አለኝታ መሆኑን ማስመስከርና ማረጋገጥ ይኖርበታል፡

በተመሳሳይ ሁኔታ የሕግ መንግስታችን አንቀጽ 39 ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 ሁሉም ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በቋንቋቸው የመጠቀምና ቋንቋን የማዳበር፣ባህላቸውን የመግለፅና የማዳበር የማስፋፋት ታሪካቸውን የመንከባከብ ራሳቸውን የማስተዳደር እና በጋራ ተቋሞች ሚዛናዊ በሆነ መልኩ በእኩልነት የመወከል መብት እንዳላቸው ይደነግጋል፡፡ ከነዚህ ድንጋጌዎች መረዳት የምንችለው የግለሰቦችና የብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች የተሳሰሩ፣ የማይነጣጠሉና እኩል እንደሆኑ፣ አንዱ ከሌላ የማይበልጥ ወይም የማያንስ እንደሆነ እንዲሁም አንዱ ለሌላው ሲባል መብቱና ነፃነቱ እንደማይሸራረፉና ገደብ እንደማይጣልበት ነው፡፡

ሕገመንግስታችን ሁሉም ብሔር፣ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች በቋንቋቸው የመጠቀም መብት አላቸው ሲል አንዱ የሌላውን ቋንቋ ማወቅና መማር የለባቸውም ማለት እንዳልሆነ ሊሰመርበት የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ በዓለምም ሆነ ባገር ደረጃ እየተጠናከረ በነሄድ ላይ ካለው ኢኮኖሚያዊ፣ማህበራዊና ፖለቲካዊ ግንኙነትና ተስስር አንፃር የአለምም ሆነ የአገራችን ሕዝቦች በነጻ ፍላጎታቸው በተለያየ ደረጃ እርስ በርሳቸው የሚያገናኛቸው የጋራ መግባቢያ ቋንቋ ወይም ቋንቋዎች በሂደት መዳበራቸው አይቀሬ ጉዳይ ነው፡፡

ብሔር፣ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች የራሳቸውን የሥራ ቋንቋ ሲወስኑ በዜጎችመካከል ልዩነትን፣ አድሎንና መገለልን ለመፍጠር አይደለም፡፡ ለሁሉም በእኩልነት እንዲያገለግል በማሰብ ነው፡፡ አንድ ቋንቋ አብዛኛውን ህዝብ ያግባባል በሚል የሥራ ቋንቋ ሆኖ ሲመረጥ ሌሎች ቋንቋዎችን ማዳበር ወይም በተለያየ ደረጃ መጠቀም አይቻልም ማለት አይደለም፡፡ በክልሉ የሥራ ቋንቋ አማርኛ ነው፡፡ የምርጫ ሕግ አዋጅ 111/87 አንቀጽ 38/1/ለ/ ቋንቋ ለመመረጥ ከሚያበቁ መመዘኛዎች አንዱ አድርጎ መደንገጉ በራሱ የሕገመንግስት አንቀጽ 38 ይቃረናል የሚል ድምዳሜ ላይ መድረስ አይቻልም፡፡ ሆኖም ግን በፌዴራል ፓርላማ ለመመረጥ የሚቀርብ እጩ ተመራጭ የክልሉን ቋንቋ ማወቅን እንደመመዘኛ ማስቀመጥ ተገቢ አይደለም፡፡ እጩ ተወዳዳሪዎች የክልሉ ነባር ብሔረሰቦች ቋንቋ ከሆነው አንዱን የባርታ ቋንቋ አትችልም በማለት ከምርጫ እንዲታገዱ የሰጠው ውሳኔ የኢፌዲሪ ሕገመንግስትን የሚቃረን በመሆኑ የምርጫ

ቦርዱ ውሳኔ ህገመናግስትና የሚቃረን ስለሆነ ይውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ወደፊት ቢደረጉ ምርጫዎች ላይ ተፈፃምነት አይኖረውም ሲል ወስኗል፡፡

**ለ.** <u>በአመልካች ወ/ሮ ከድጃ በሽር የሕግ መንግስታዊ መብት መከበር አቤቱታ ላይ በፌዴሬሽን ምክር ቤት የተሰጠ ውሳኔ</u>

ለአቤቱታው መነሻ የሆነው የህገመንግስቱን አንቀጽ 34/5/በመጥቀስ በሸርያ ህግና ፍረድበት መዳነት እንደማይፈልጉ ገልፀው እያሉ ይህን ችላ ብሎ በሽሪያ ፍርድ ቤት አይቶ መወሰኑና የጠቅላይ ሸሪያ ፍርድ ቤትም የረግባኝ ቀርቦለት ውሳኔውን ያፀደቀው በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 13/1/ መሰረት የፍትህ አካላት የሕገመንግስቱን መሠረታዊ መርሆዎች ማስከበር ሲገባቸው ሕገመንግስቱን የሚፃረር ልማዳዊ አሠራር በሚኖርበት ጊዜ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 9/1/ …ማናኛውም ለማዳዊ አሰራር፣ እንዲሁም የመንግሥት አካል ውሳኔ ከሕገመንግስቱ ጋር የመቃረን ከሆነ ተፈፃሚነት አይኖረውም …በሚል መንገድ ተከትሎ ህገ መንግስቱ ያስቀመጠላቸውን ፈቃዳቸውን ገልፀው ለመዳኘት የመችሉበትን ሁኔታ ማመቻቸት ሲገባው አስገድዶ ውሳኔውን እንዲቀበሉ ማድረግ ሕገመንግስቱን የሚፃረር ስለሆነ ውድቅ ተደርጓል፡፡

ሐ. <u>በሲልጤ ህዝብ ማንነት ጥያቄ ላይ የፌዴሬሽን ምክርቤት የሰጠው ውሳኔ</u>

የሲልጤ ብሔረሰብ ብሔር ለመባል የሚፈለጉትን መስፈርቶች ያሟላሁ ስለሆነ እውቅና ይሰጠኝ እንዲሁም ከዚህ ጋር የተያያዙ መብቶች ይከበሩልኝ የሚል ጥያቄ ለፌዴሬሽን ምክርቤት ቀርቧል፡፡ ጥያቄው የቀረበለት ፌደዴሬሽን ምክር ቤት የአንድን ማህበረሰብ የማንነት ጥያቄ መወሰን ያለበት ማን ነው? በምንስ ሥነሥርዓት ይወሰናል? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ አስተያየት አሰባስቧል ውይይትም አድርጓል፡፡ ጥያቄውን በቀጥታና በግልጽ የሚመልስ ሕገመንግስታዊ ድንጋጌ የሌለ መሆኑን ግንዛቤ ተወስዷል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ የሕገመንግስት ድንጋጌዎችን አንድበአንድ ምክርቤቱ የመረመረ ሲሆን የሕገመንግስቱ ድንጋጌ አንቀጽ 39/4/ ብሔር ብሔረሰቦች የሚያነሱትን የመገንጠል ጥያቄ የሚመለከት እንጂ አንድ ማህበረሰብ ለሚያነሳው የማንነት ጥያቄ መልስ

የሚመልስ ሆኖ አላገኙትም፡፡ በመቀጠልም የሕገመንግስቱን አንቀጽ 47 የተመለከቱ ሲሆን በብሔር ብሔረሰብነት ማንነታቸው ታውቆ በክልሉ ውስጥ የቆዩ ሆነው ነገር ግን የራሳችንን ክልል እናቋቁማለን የሚል ጥያቄ ለክልል ምክርቤት ቀርቦ በዚያው የሚፈፀም መሆኑን ስለሚደነግግ ምክርቤቱ ለተያዘው ጭብጥ ምላሽ የሚሰጥ ሆኖ አላገኘውም፡፡

ሕገመንግስቱ ድንጋጌ አንቀጽ 52/2/ሀ/ የማንነትን ጉዳይ የመወሰን ሥልጣን የማን እንደሆነ በግልፅ ባያስቀምጥም የክልሎች ሥልጣን ተብለው ከተዘረዘሩት ውስጥ ተካቷል፡፡ ስለዚህ ክልሎች ራስን በራስ ማስተዳደር አላማው ያደረገ ክልላዊ መስተዳደር በሚያዋቅሩበት ጊዜ በቅድሚያ የማንነትን ጥያቄ መወሰን የሚጠበቅባቸው ይሆናል፡፡ በተጨማሪም ሕገመንግስቱ የተከተለው ፌደራላዊ የአወቃቀር ስርዓት ለክልሎች በውስጣዊ ጉዳዮች ላይ የመወሰን ስልጣን የሚሰጥ በመሆኑ የማንነት ጥያቄ በክልሉ ውስጥ የሚነሳ ጉዳይ እንደመሆኑ መጠን የክልሉን ውሳኔ ማግኘት የግድ ይሆናል፡፡

ማንነቴ ይታወቅልኝ በማለት በአንድ ማህበረሰብ የሚቀርብ ጥያቄ በቅድሚያ ቀርቦ መስተናገድ የሚገባው ጥያቄው በተነሳበት ክልል ምክር ቤት ሆኖ በክልሉ የነበረውን የአፈጻፀም ሂደት ጉድለት አለበት ወይም ህገመንግስቱን መሰረት አድርጎ አልተፈፀመም የሚል ቅሬታ ሲነሳና በዚህ እና ተመሳሳይ ምክንያቶች ጥያቄውን በአቀረበው ማህበረሰብ እና በክልሉ ምክር ቤት መካከል ልዩነት ሲኖር በሕገ መንግስቱ ድንጋጌ አንቀጽ 62/3/ መሰረት ጉዳዩ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ቀርቦ የመጨረሻ እልባት ማግኘት እንዳለበት ተመልክቷል፡፡

የምክርቤቱ ሚና ጥያቄው ቀርቦ ፍፃሜ እስኪያገኝ ድረስ ያለው ሂደት ህገ መንግስቱን ተከትሎ እንዲፈፀም ማድረግ ሆኖ ማንነቴ ይታወቅልኝ በማለት በሚቀርብ ጥያቄ ላይ ውሳኔ ሰጪው ጥያቄ አቅራቢው ማህረሰብ ራሱ ነው፡፡ የማንነትን ጥያቄ አስመልክቶ በሚነሳ ጥያቄ አስመልክቶ በሚነሳ ጉዳይ ላይ ውሳኔ ሲሰጥ ውሳኔው ህገ መንግስቱ የተቀረፀበትን መንፈስ እና ህገመንግስታዊ መርሆዎቹን በመከተል ይፈፀም ዘንድ የሚቀርበው ጥያቄ የማህበረሰቡ ትክክለኛ ጥያቄ መሆኑን ማሳየት እንዲቻል በአንቀጽ 39/5/ የተመለከቱት መስፈርቶች የተሟሉ መሆኑን ማሳየት ጥያቄው በፅሑፍ መቅረብ ያለበት ሲሆን ጥያቄው የቀረበለት የክልል ምክርቤት ጉዳዩን ተቀብሎ አንቀጽ 39/5/ መስፈርቶችን ያገናዘበ ጥናትን መሰረት በማድረግ ለህዝብ ውሳኔ እንዲያቀርብ ይጠበቅበታል፡፡ህዝብ ውሳኔው ዲሞክራሲያዊ እና ፍትሃዊ እንዲሆን ጥያቄውን ያቀረበው

ማህረሰብ አባላት በቀጥታ የሚሳተፉበት፣ነፃ በሆነና ድምፅ በሚስጥር በሚሰጥበት ስርዓት እንዲሁም ገለልተኛ ታዛቢዎች በተገኙበት አግባብ ሊከናወን ይገባል፡፡

የማንነቱ ይታወቅ ጥያቄ ጥያቄውን ያቀረበው ማህበረሰብ አባላት በሚያደርጉት ቀጥተኛ ተሳትፎ በህዝብ ውሳኔ መወሰን ይገባል የተባለበት ዋነኛ ምክንያቶች፡-

የማንነት ጥያቄ የብሔር ብሔረሰቦች ወይም ህዝቦች መብቶች መሠረትና ምንጭ በመሆኑ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ጥያቄ ስለሆነ፤መሰል ከፍተኛ ግምት የሚሰጣቸው የመገንጠልና ክልልን የመመስረት ጥያቄዎች የሚወሰኑት ህዝቡ በሚያደርገው ቀጥተኛ ተሳትፎ በህዝብ ውሳኔ እንደሆነ የህገ መንግስቱ አንቀጽ 39/4/ እና 47/4/ ስለሚደነግግ ነው፡፡

የማንነት ጥያቄ የእያንዳንዱን የማህበረሰብ አባል ማንነት የሚነካና የሚመለከት በመሆኑ የአብዛኛውን የማህበረሰብ ፍላጎት በትክክልና በዘስተማማኝ መልኩ ለማወቅ የሚያስችለን ስርዓት ነው፡፡ በመሆኑም የስልጤ ማህበረሰብ ማንነት  የማህረሰብ አባላት በቀጥታ የሚሳተፉበት፣ነፃ በሆነና ድምፅ በሚስጥር በሚሰጥበት ስርዓት እንዲሁም ገለልተኛ ታዛቢዎች በተገኙበት በህዝብ ውሳኔ መወሰን አለበት በሚል በአብላጫ ድምፅ ተወስኗል፡ ፡የሀሳብ ልዩነቱ ክልሎች የውስጥ ጉዳያቸውን በራሳቸው መፍታት አለባቸው እየተባለ በሌላ በኩል ደግሞ የማንነት ጥያቄ ሲነሳ ፈታት ያለበት በዚህ መንገድ ነው በማለት ለክልሎች ማስተላለፍ የክልሎችን ሥልጣን መጋፋት እንደሚሆን፤ህገመንግስቱ የህዝብ ውሳኔ የግድ የሚለው በተወሰኑ ተለይተው በተቀመጡ ጉዳዩች ላይ ብቻ ነው(አንቀጽ 47 እና 39ን ይመለከታል)፡፡ ከዚህ ውጪ የሚነሱ ጥያቄዎች መፈታት የሚኖርባቸው በሕገ መንግስቱ በራሱ ነው፡፡ በሕገ መንግስቱ ደግሞ ሕዝብ መብቱን በቀጥታ ወይም በተወካዩቹ አማካይነት ተግባራዊ ማድረግ እንደሚቻል ይደነግጋል፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው የማንነት ጥያቄ ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ ምላሽ እንዲያገኝ ማድረግ የህገመንግስቱን መርህ የተከተለ መሆኑን ነው፡፡ ከህዝብ ውሳኔ በመለስ ያለው አፈፃፀም ሕገመንግስቱን የሚጥስ ነው ማለት የሚቻል አይመስለንም፡፡ ስለዚህ የማንነት ጥያቄ በሕዝብ ውሳኔ እልባት ሊያገኝ ይገባል የሚለው የአብዛኛው ድምፅ አስተያየት ሌሎች ዴሞክራሲያዊ አካሄዶችን ግምት ውስጥ ያላስገባ ስለሆነ በድምፅ ተለይተናል የሚል ነው፡፡

## 3. ማጠቃለያ

መንግስት የጤና የትምህርትና ሌሎች የማኅበራዊ አገልግሎቶችን ለሕዝብ ለማቅረብ በየጊዜው እየጨመረ የሚሄድ ሀብት በመመደብ ሕዝቡን የመኖሪያቤት፣ጤና፣ትምህርት አገልግሎት ተጠቃሚ እያደረገ መገኘቱ፣ነጻ የምርጫ ሥርዓት በመዘርጋትና ጠንካራ የፍትህ ተቋም በመገንባት የህዝቡ ሰባአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች እንዲከበሩለት እያደረገ ያለው ጥረት፣የፌዴራልና የክልሉን ስልጣን ክፍፍል አክብሮ መንቀሳቀስ፣ የፌዴራል መንግስቱ ኃላ የቀሩ ክልሎችን ለመደገፍ እና ጠንካራ መንግስት ሆነው በሁለት እግራቸው እንዲቆሙ ለማስቻል የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስተር በማቋቋም በበጀትም ሆነ በሰው ኃይል የሚያደርግላቸው ድጋፍ፣የሰባአዊ መብትና እምባ ጠባቂ ኮሚሽን በማቋቋም በህገመንግስቱ የተደነገጉ የሰባአዊ መብት ድንጋጌዎችን በአግባቡ በስራ ላይ ለማዋል የሚደረጉ ጥረቶች፣ በፌዴራል ደረጃ በሚዘጋጁ ፖሊሲዎች ክልሎችን በበቂ ሁኔታ በማሰተፍ፣እና ሕዝብ የሥልጣን ባለቤት ለመሆኑ ማረጋገጫ የሆነውን የመንግስት ሥልጣን ከምርጫ ሳጥን ብቻ የሚገኝበትን ባህል ለማዳበር የሚያደርገው ትግልና ሌሎችም በአጠቃላይ ጠንካራ ህገመንግስታዊ ስርዓት በአገርቱ ለማስፈን በሚደረጉ ዙሪያ መለስ ጥረቶች ለውጥ እየታየ ነው፡፡

- <u>የመወያያ ጥያቄ</u>

1. የአንድን ማህበረሰብ የማንነት ጥያቄ መወሰን ያለበት ማን ነው?
2. የአንድን ማህበረሰብ የማንነት ጥያቄ በምን ሥነሥርዓት ይወሰናል?
3. በምርጫ ሕጉ የሚወዳደርበትን ብሔራዊ ወይም የአከባቢውን የሥራ ቋንቋ ማወቅ ለእጩነት የሚያበቃ መመዘኛ ተደርጓል፡፡ ይህ የአዋጁ ድንጋጌ በሕገ መኖግስቱ አንቀጽ 38 ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በቋንቋ ልዩነት ሳይደረግበት የመመረጥ መብት እንዳለው የተቀመጠውን የሕገመንግስት ድንጋጌ ይቃረናል የሚል አቤቱታ ቀርቧል፡፡ CCI ሆነ አስተያየት ሰጪው አዋጁ ሕገመንግስቱን አይቃረንም ለማለት የሰጠው ምክንት አግባብ ነው ብለው ያምናሉ?